

## ሰላም የራቀው ቅኝት ለውጥ

**ብሄርተኝነት ከታሪክና ከንድፈ ሃሳብ አኳያ**

ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

**“የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፈርሶ፤ ታየ ዘረኝነት ዳር እስከ ዳር ነግሶ!”**

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 40 ጥር 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




## “የኢትዮጵያዊነት እንጂ የኦሮሞ፣የአማራ፣የትግሬ የሚባል ደም የለም”

“የትኛውም ሕዝብ የሚኖርበትን ክልል ጠፍጥፎ አልሰራውም”

ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው



# ኦነግ የማን ነው?


“የኦሮሞ ብሔርና ኦነግ ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው”

“ኦነግ መሰንጠቅ ከጀመረ እረጅም ጊዜው ነው”

አቶ ሌንጮ ለታ

ግዮን

ቅጽ 1 ቁጥር 40 ቅዳሜ ጥር 11 2011 ዓ.ም




ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ጥር 18
ይጠብቁን!




ቁጥር 39 ዕትም

# ኦነግ የማን ነው? አቶ ሌንጮ ለታ

4 ተስፋ እና ሥጋት
የተዳበሉበት የሀገሪቱ
ዕጣፈንታ

5 ሰላም የራቀው ለውጥ
መለክ ቢ.

7 ብሄርተኝነት ከታሪክና
ከንድፈ ሃሳብ አኳያ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

11 “የዜግነት ክብር
በኢትዮጵያችን ፈርሶ፤
ታየ ዘረኝነት ዳር እስከ
ዳር ነግሶ!”
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

17 በሁለት ሲኦሎች
መካከል ገነት አለ
ደረጀ ይመር

19 ወያኔ ማን ነው?
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

21 ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል
ሳንፎርድ
የሚሺን 101 ዋና አዛዥ
በኢትዮጵያ
ብሩክ መኮንን

28 በኢትዮጵያ የውጪ
ባንኮች የጎንዮሽ ጉዳት
እና ጥቅም ሲመዘን
ተስፋዬ ሽብሩ




## “የኢትዮጵያዊነት እንጂ
## የኦሮሞ፣የአማራ፣የትግሬ የሚባል ደም የለም”

ሬ/ፐ/ር አበባው አያሌው

# ፓትርያርክ መርቆርዮስ ከ26 ዓመት በኋላ ጥምቀትን ያከብራሉ

**በተስፋዬ ሽብሩ**

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከ27 ዓመት የስደት ሕይወት በኂላ በጎንደር፣ በባህርዳር እና በደብረ ታቦር ጉብኝት በማድረግ እና ሕዝበ ክርስቲያኑን በመባረክ የአንድ ሳምንት ቆይታ አድርገው ተመልሰዋል::

ቅዱስ ፓትርያርኩን ለመቀበል ከጎንደር አፄ ቴዎድሮስ አየር ማረፊያ ጀምሮ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በርካታ ሕዝበ ክርስቲያን እና ካህናት እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ታጅበው አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: በአቀባበል ሥነ ሥርዓቱ ላይ የጎንደር ሁሉም አድባራት፣ የአድባራቱ አስተዳዳሪዎች፣ ካህናት፣ የሰንበት ት/ቤት መዘምራን፣ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት የመንግሥት ኃላፊዎች ተቀብለዋቸዋል::

ቅዱስ ፓትርያርኩ ለረጅም ዘመን የተለያቸውን ሕዝበ ክርስቲያን አግኝተው መባረካቸው ደስታ ፈጥሮላቸው ማለፉን በስፍራው ያሉት ምንጮቻችን አድርሰውናል:: ሕዝበ ክርስቲያኑም ቅዱስነታቸውን በማግኘቱ በከፍተኛ መንፈሳዊ አቀባበል በእንባ ጭምር እንደተቀበላቸው ታውቋል::

ቅዱስ ፓትርያርኩ በአርምሞ (በዝምታ) ላይ በመሆናቸው እጃቸውን አንስተው በመስቀል በመባረክ ከሕዝበ ክርስቲያኑ ጋር ለመገናኘት መብቃታቸው ከፍተኛ እርካታ እንደሰጣቸው ከስፍራው ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡ ምዕመናን ገልጸዋል::

ከጎንደር ቆይታቸው በኂላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በዓለ ጥምቀትን በጃንሜዳ የሚያከብሩት ቅዱስነታቸው ሕዝቡን በመስቀል ከመባረክ ውጭ አሁንም በአርምሞ ይቀጥላሉ ተብሎ ይጠበቃል::

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ከመሆናቸው በፊት የጎንደር ሊቀ ጳጳስ በነበሩ ጊዜ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸውና በሰሯቸው በርካታ የልማት ሥራዎች በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እንደነበራቸው ይታወቃል::

ቅዱስነታቸው ከደርግ መንግሥት ውድቀት በኂላ በኢሕአዴግ መንግሥት በተደረገባቸው ጫና ከአገር ተሰደው ላለፉት 26 ዓመታት ኑሯቸውን በሰሜን አሜሪካ አድርገው የነበር ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን መምጣታቸውን ተከትሎ ወደ አገራቸው መመለሳቸው ይታወሳል:: በአሁኑ ሰዐት በመልካም የጤንነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል::

# በስድስተኛው ጉዞ አድዋ አዳዲስ ነገሮች ተከስተዋል

**በሮቤል ምትኩ**

ለስድስተኛ ጊዜ እየተካሄደ ባለው “ጉዞ አድዋ” ላይ ከዚህ በፊት ያልታዩ አዳዲስ ነገሮች እየተስተዋሉ መሆናቸውን የጉዞው አስተባባሪ ያሬድ ሹመቴ ለግዮን መጽሔት ገልጿል::

የኢትዮጵያና የአፍሪካ ኩራት የሆነው የአድዋ ድልን ለመዘከር በተጀመረው ስድስተኛው (የዘንድሮ) ጉዞ ላይ በአጠቃላይ አርባ ስምንት ተጓዦች የተሳተፉ ሲሆን፣ አራቱ ተጓዦች ከሐረር ከተማ መምጣታቸው ታውቋል:: ታህሳስ 22 ቀን በመነሳት 536 ኪሎ ሜትር በእግር አቋርጠው ጥር አምስት ቀን አዲስ አበባ የገቡት አራቱ የሐረር ተጓዦች፣ ከቴዎድሮስ አደባባይ እስከ ጣይቱ ሆቴል ድረስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል::

ጉዞው ከዜሮ ኪሎ ሜትር የጀመረው ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በመነሳት እንደሆነ የገለፀው ያሬድ ሹመቴ፣ የጉዞ አድዋ አባላት ጥር ስድስት ቀን 2011 ዓ.ም ለጉዞ ሲነሱ የሽኝት ፕሮግራም ተዘጋጅቶላቸዋል ብሏል:: ማክሰኞ ለገጣፎ፣ ረቡዕ ሰንዳፋ ያደረው የጉዞ አድዋ ቡድን አባላት በደብረ ብርሃን፣ በደሴ፣ ወልድያ፣ ማይጨው፣ መቀሌ፣ ውቅሮ፣ ሐውዜን፣ ጢሃ በኩል አድርገው አድዋ ይደርሳሉ ተብሎ ይጠበቃል::

በአርባ ሰባት ቀናት ጉዞ ሃያ ስምንት ከተሞችን ጨምሮ፣ በርካታ ጥቃቅን የገጠር መንደሮችን የሚያቋርጠው ቡድን እስካሁን ድረስ በየደረሰበት አካባቢ ሕዝቡ ደማቅ አቀባበል እያደረገለት ሲሆን፤ ለተወሰነ መንገድ የሚያገለግሉ ምግብ፣ ውሃ፣ የሕክምና ቁሳቁሶችና ጫማ የመሳሰሉትን ኅብረተሰቡ እየረዳቸው በመሆኑ እስካሁን ድረስ ችግር እንዳልገጠማቸው የገለፀልን አስተባባሪው ያሬድ ሹመቴ፣ የጉዞውን ሙሉ ወጪ የአዲስ አበባ መስተዳድር እንደሚሸፍን ቃል የገባላቸው ቢሆንም እስካሁን ድረስ ግን ሁሉንም ነገር ርግጠኛ ሆኖ መናገር እንደማይቻልና ሂደቱ ሙሉ ለሙሉ እንዳልተጠናቀቀም ጨምሮ ገልጿል::

ባለፈው ዓመት ሃያ አምስት አባላት ብቻ የነበሩ ጉዞ አድዋ ዘንድሮ ወደ 48 ከፍ ያለ ሲሆን ዘንድሮ ከሌላው ጊዜ ከፍ ባለ መልኩ ስድስት ሴቶች ከተጓዦች መሀል እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል::

## “የአማራ ሕዝብ ግጭት ጀማሪ አይሆንም” ገዱ አንደርጋቸው

**ተስፋዬ ሽብሩ**

የአማራና የትግራይ ክልል ርዕሰነ መስተዳድሮች በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ከሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ጋር ተወያዩ:: የአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ገዱ አንዳርጋቸውና የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ም/ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል የሁለቱን ክልል ሕዝቦች በመወከል ንግግር አድርገዋል::

ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን የምንመኘው ስለሆነ አካል ብለን ሳይሆን ለሁሉም መሰረት ስለሆነ ነው በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ ገዱ ትንሽ ጊዜ እንኳን ግጭቶች ሲኖሩ ጉዳቱ ምን ያህል እንዲሆን እያየን ነው ብለዋል:: የአማራ ሕዝብ ከወንድሞቹና ከጎረቤት ክልሎች ከትግራይ ሕዝብ ጋር ሰላም መሆን እንደሚፈልግ የገለፁት ርዕሰ መስተዳሩ የአማራ ሕዝብ ለመስራት፣ ለመኖር፣ ለመሻሻል የሚፈልግ ሕዝብ ነው:: ሕዝቡ ለሰላም ዝግጁ መሆኑን በተደጋጋሚ መናገሩን ጠቅሰው የተጀመረው ለውጥ እንዳይቀለበስ የሚሰጋና ከፍተኛ ጉጉት ያለው መሆኑንም ተናግረዋል::

“እኔ የምመራው ሕዝብ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ውጪ ብሄድ ይጠይቀኛል:: ከክልሎች ጋር በሰላም መኖር ይፈልጋል በማለት የአማራ ሕዝብ ለሰላም ያለውን ፍላጎት አስረድተዋል::

የአማራ ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ግጭት ጀማሪ አይሆንም፤ ያሉት አቶ ገዱ ከወንድሞቻችን ከትግራይ አመራሮችና ከትግራይ ሕዝብ ጋር በውይይት መፍታት እንችላለን፤ ለዚህም ቃሌ ፊርማዬ ነው በማለት ለሰላም እንደሚሠሩ አቶ ገዱ አስገንዝበዋል::

የትግራይ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረፅዮን ገብረ ሚካኤል በበኩላቸው የአገር ሽማግሌዎችንና የሃይማኖት አባቶች አመስግነዋል::

የፖለቲካ መሪዎች መሥራት የሚገባንን ሥራ በሰራንና ስለ ተጨነቃችሁ ማመስገን እፈልጋለሁ በማለት የሽማግሌዎቹንና የሃይማኖት አባቶቹን ጥረት አወድሰዋል::

ግንኙነታችን ከወንድምነትም በላይ ነው፤ የፖለቲካ ጓዶች ነን ያሉት ፣ዶ/ር ደብረጽዮን የአገራችን እሴቶች ብቻ ሳይሆን የድርጅታችንም እሴቶች መሸርሸር እየታየ ነው ብለዋል::

የድንበርም ሆነ የሰላም ጉዳይ በድርድር መሆን አለበት፤ ያሉት ም/ርዕሰ መስተዳድሩ “መገዳደል ኂላ ቀርነት ነው፤ የአራዊት ሥራና ኃጢአትም ነው:: የአመራሩ አካል ስለሆንን የችግሩ አካል ነን:: የተበላሸ ፖለቲካ ስላለ ወደ ኂላ ትተን ተደጋግፈን መስራት እንዳለብን አምናለሁ በማለት ልዩነቶች አስወግዶ መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል:: በአማራ ሕዝብ ላይ የሚያነሱት የተለየ ጥያቄ እንደሌለ የጠቀሱት ዶ/ር ደብረጽዮን መሬት ሄደ አልሄደ ለእነርሱ አጀንዳ አለመሆኑን፤ ጉዳዩም ሊያጋጭ የሚገባው አይደለም ብለዋል::

“ሕዝቡ ወደ ግጭት አታስገቡን እያለ ነው፤ በእኛ በኩልም እንደ አመራር ለመጋጨት አንፈልግም” ብለዋል ም/ርዕሰ መስተዳድሩ:: ከትግራይ የሚተኮስ ነገር አይኖርም፤ ግፊቶች ግን አሉ በማለት ግጭቶችን ለማስወገድ ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ መስራት እንደሚጠበቅበት አስረድተዋል::

# አሁድ ጥር 12 "ኢትዮጵያዊነት" የሙዚቃ ኮንሰርት በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል

**በሮቤል ምትክ**

በኢትዮጵያ ውስጥ ካለፉት አስር ወራት ወዲህ የተገኘውን የለውጥ እንቅስቃሴ ምክንያት በማድረግ ባለፈው ዓመት መገባደጃ ጳጉሜ ወር ላይ ወደ ሀገር ቤት የገባው አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ የሚከተለውን የዜግነት ፖለቲካ በሕዝብ ዘንድ ለማስረጽ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ ቀጥሏል::

በቅርቡ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ለመዋሃድ ከስምምነት የደረሰው፣ኢትዮጵያዊነትን የሚያስፋፋ ብሎም በቀጣዩ ምርጫ ስርዓቱን የሚገዳደር እና በምርጫ ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ የሚቀርብ የፖለቲካ ድርጅት ለመመስረት ከጫፍ ላይ የደረሰው፣ አርበኞች ግንቦት ሰባት የፊታችን እሁድ ጥር 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያተኩር ታላቅ የሙዚቃ ኮንሰርት አዘጋጅቷል::

በማንነት ላይ ከተመረኮዘ፣ ብሔርተኝነት ላይ ከተንጠላጠለ ፖለቲካ በራቀ መልኩ አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን በማፅናት ረገድ በዚህ ወቅት እንደ አሸን ከፈሉት የብሔር ድርጅቶች በራቀ መልኩ፣ ሕዝባዊና ሀገራዊ ግዴታውን እየተወጣ የሚገኘው አርበኞች ግንቦት ሰባት ይህንን የሙዚቃ ኮንሰርት ለማዘጋጀት የተነሳው በሁለት ምክንያቶች እንደሆነ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አቶ ቸኮል ጌታነህ ለግዮን መጽሔት ገልፀዋል::

የኮንሰርቱ ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያዊነትን ማወደስ፣ የዜግነት ፖለቲካ የሚደግፉ የኅብረተሰቡ አካላትን ማበረታትና ማነቃቃት፣ አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያ በዚህ ትውልድም ሆነ በቀጣዩ ትውልድ ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዲኖራት ማድረግ እንደሆነ የገለፁት አቶ ቸኮል፣ በተጨማሪም ፓርቲያቸው በቅርቡ ከሌሎች ሶስት ድርጅቶች ጋር ውህደት ለመፍጠር በመወሰኑና በዛ መሰረት በሁሉም ወረዳዎች ከስር አባላትን የማዋሃድና የመዋቅር ስራ ሰርቶ አዲስ ምስረታ የሚያካሄድ በመሆኑ፣ ይህን ለማድረግ ከሚያስፈልገው ከፍተኛ ወጪ አንፃር ድርጅቱን በገቢ ለማጠናከር ኮንሰርቱን ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ አስታውቀዋል::

ጥር 12 ቀን ከቀኑ ስምንት ሰዓት ጀምሮ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ በሚዘልቀው ልዩ የኢትዮጵያዊነት የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ አለማየሁ እሸቴ፣ ፀጋዬ እሸቱና ዳን አድማሱን ጨምሮ በርካታ የሀገራችን ስመ ጥር ድምፃውያን ለታዳሚዎቻቸው ሥራዎቻቸውን ያቀርባሉ:: አክሱማይት ባንድና ጃኖ ባንድን ጨምሮ ኢትዮጵያዊነትን ፈልጎ የማግኘት እንቅስቃሴን የሚያሳዩ የዳንስ ግሩፖችና የተለያዩ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች በዕለቱ እንደሚገኙ ለዝግጅት ክፍላችን የጠቆሙት አቶ ቸኮል ጌታነህ፣በኮንሰርቱ ላይ የአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራሮች ፕ/ር ብርሃኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ንግግር እንደሚያደርጉ ገልፀው፤ ከፕሮግራሙ የሚገኘው ገንዘብ በቀጣይ ለሚመሰረተው አዲስ ፓርቲ ገቢ እንዲውል መግባባት ላይ መደረሱን ይፋ አድርገዋል::

ከበርካታ ዓመታት በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ ኢትዮጵያዊነት ይሰበክበታል የተባለው ኮንሰርት መግቢያ ዋጋ 300 ብር ሲሆን፣ ቪ. አይ ፒ 500 ብር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: በኮንሰርቱ ላይ ይለበሳል የተባለው ቲሸርትም ከተማው ውስጥ በሁለት መቶ ብር እየተሸጠ ይገኛል::



# ከአፋር ቀውስ ጀርባ "አልሸባብና ጅቡቲ" ሊኖሩ ይችላሉ ተባለ

**በሮቤል ምትኩ**

ለሁለት ሳምንት በኢትዮ ሶማሌ ኢሳ ጎሳ አባላትና በአፋር አርብቶ አደር መሀል የተካሄደው ጦርነት ከሁለቱም ወገን ብዛት ያላቸው ሰዎችን ሕይወት ቢቀጠፍም አሁንም በአንዳንድ የአፋር ክልል ከተሞች የተነሳው ግጭትና አመጽ ሙሉ ለሙሉ እንዳልቆመ ለማወቅ ተችሏል፡፡

አዳይቱ፣ ገዳማይቱና፣ አንዳፍሮ በተሰኙ ሦስት ከተሞች ላይ በሁለቱ ጎሳዎች መሀል የተካሄደው ጦርነት የጠነከረና ከጀርባው ሌላ አጋዥ ኃይል እንዳለበት አመላካች ነው እየተባለ ይገኛል፡፡በተጠቀሱት ከተሞች የሚኖሩ የሶማሌ ኢሳዎች ምድሩ የአፋር መሬት መሆኑን እያወቁ የክልሉን ባንዲራ አውርደው በእሳት በማቃጠል የሶማሌን ሰንደቅ ዓላማ በመስቀላቸው ምክንያት ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ እስከያዝነው ሳምንት አጋማሽ ድረስ ትልቅ ጦርነት መካሄዱን የደረሰን መረጃ ያመላክታል፡፡

የኢሳዎች ጦር በጣም የተደራጀና ሙሉ የጦር መሳሪያ የታጠቀ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የገለፁትና ስለ ሁኔታው ለማወቅ ወደ ስፍራው አቅንተው የነበሩት የአፋር ሰብኣዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሊ/መንበር አቶ ጋአስ መሀመድ የመከላከያ ሠራዊት ወደ ቦታው ቢገባም ሁለቱ ሕዝቦች ቀኑን ሙሉ ሲጋደሉና ሲተላለቁ ከማየት ውጪ መሀል ገብቶ ለማስቆም እንዳልሞከረና ምሽት ላይ ብቻ አንድ ጊዜ የተኩስ ድምጽ ማሰማቱን አስታውቀዋል፡፡

ጋላፊ፣ ቢሾፍቱ፣ ሰመራ፣ አዋሽ አርባ የተሰኙ ከተሞችን ጨምሮ በአጠቃላይ ዘጠኝ ከተሞች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የተነሳው ጦርነት ፣ አድማሱን አስፍቶ ማክሰኞ ጥር 7 ቀን 2011 ዓ.ም ብቻ ከአፋር ሃያ አምስት ሰዎች ከሶማሌ ኢሳ ጎሳ ደግሞ 60 ያህል ሰዎች መሞታቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች የደረሳቸው መሆኑን የሚናገሩት አቶ ጋአስ፣ በአፋር ክልል ላይ የሶማሌ ኢሳ ጎሳ አባላት መኖራቸውን ደግፈውና አምነው የሚቀበሉት የአፋር ወጣቶች፣ እነሱን ተጠቃሚ ባላደረገ መልኩ በገዛ የትውልድ ቦታቸው ላይ ከሌላ ቦታ በመጡ ኃይሎች በጣልቃ ገብነት የሚያደርሱትን የፍትሕና የሥራ መጓደል በእጅጉ በማውገዝ፣ ተቃውሞቻቸውን ከማሰማታቸው በተጨማሪ መንገዶችን ለ24 ሰዓት ዘግተው እንደቆዩም ተናግረዋል፡፡

ሰኞ ጥር 6 ቀን ወጣቶቹ መንግሥት በ15 ቀን ውስጥ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጥሪ በማቅረብ የዘጉትን መንገድ የከፈቱ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን ከዚህ የከፋ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ ማሳወቃቸውን ለግዮን መጽሔት የገለፁት አቶ ጋአስ መሀመድ አሁን ከሚታየው ግጭት ጀርባ የታላቋ የሱማሊያ የተስፋፊነት ፖለቲካና እሳቤ፣ እንዲሁም ከአብዲ ኢሌ ጦር የተባረሩ ወታደሮችና የጅቡቲ መንግሥት (ጅቡቲ አብላጫውን ስልጣን የያዘው የኢሳ ጎሳ መሆኑ ይታወቃል) እጅ ሊኖርበት እንደሚችል ግምት የሚያሳድሩ ፍንጮች መታየታቸውን በመግለፅ፤ ከተገደሉ የሶማሌ ወታደሮች መሀል የአልሸባብን አለባበስ የተጠቀሙና የጅቡቲ ወታደር መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ ጭምር መገኘቱን ይፋ አድርገዋል፡፡

# ተስፋ እና ሥጋት የተዳበሉበት የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአራቱም ማእዘናት የሰላም ዓየር መተንፈስ ከናፈቃት ሰንበትበት ብላለች::በዘር ማንነት ላይ የተቀለሰው ሥርዓት የቆመበት ጠንቀኛ መደላድል ቀስ በቀስ እየተናደ ዳፋው ለሁሉም የሀገራችን ሕዝቦች እየተረፈ ነው::ብዙዎች ተስፋ ያደረጉበት የለውጥ ሥርዓት ተቀልብሶ ወደባሰ አዘቅጥ ውስጥ እንዳይመለስ ሥጋታቸውን እየገለጹ ይገኛል::የግጭቶቹ ባሕሪያት በተለያየ ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቁ ናቸው::

በምእራብ ወለጋ የተፈጠረው ሥርዓት አልበኝት የመንግሥትን የታችኛውን መዋቅር እስከማፈራረስ ደርሷል::ይህ የጥፋት ኃይል ከቤተመንግሥት ከተባረረው፣ከተሸነፈው ቡድን ጋር ግንባር ሊፈጥር እንደሚችል ታዛቢዎች አስቀድመው መላምታቸውን ሰንዝረው ነበር::በአማራ ክልልም ምዕራብ ጎንደር አካባቢ ከተፈጠረው ቀውስ ጀርባ የፀረ ለውጡ ኃይል አሻራ እንደማይጠፋ ይገመታል::ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ አራቱም አቅጣጫ ማንነት ላይ የተነጣጠሩ ግድያዎች፣መፈናቀሎች እና የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ዐይን አዋጅ ሆነዋል::

በዚህም የተነሳ አዲሱ የዶ/ር ዐቢይ አሕመድ አስተዳደር ሀገሪቱን ለሁለት ዐሥርተ ዓመታት ሲዘርፍ እና ሲበድል የኖረው ቡድን በሚጎነጉነው ሴራ የሚፈጠረውን ቀውስ በማብረድ ተጠምዷል:: ከዚህ ኃይል ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንባር የፈጠሩ የጥፋት ቡድኖች በየአቅጣጫው እሳት መጫራቸውን ቀጥለዋል::ከዚሁ ጎን ለጎን ለፓለቲካ ትርፍ ሲባል ማንነት ላይ ተንጠላጥሎ ገቢራዊ የሆነው የዘር ፌዴራሊዝም እየፈጠረ ያለው ሳንካ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠነከረ ነው:: በመሆኑም የለውጥ አስተዳደሩ ሁለቱን ተገዳዳሪ ፈተናዎች በተገቢው መልኩ ምላሽ ለመስጠት የሚላበሰው ፓለቲካዊ ቁርጠኝነት የሀገሪቱን የወደፊት እጣፈንታ በመወሰኑ ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡

የተሸነፈውን የፀረ ለውጥ ኃይል ወደ ሰላም ማእቀፍ በማምጣት በሕግ የሚዳኝበት አሠራርን መከተል አንዱ አማራጭ ሊሆን ይችላል::በርግጥ በዚህ ረገድ መንግሥት ከመጠን በላይ ስክነት የተሞላበት ፓለቲካዊ አቅጣጫን እየተከተለ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም::የትዕግስቱ ዳር ድንበር እስከምንድረስ እንደሚዘልቅ ግን ለብዙ የፓለቲካ ታዛቢዎች ግራ ነው::መቀሌ የመሸገውን ቡድን ለማንበርከክ መንግሥት ጥቂት እርምጃዎችን ቢራመድ ተስፋ በተጣለበት አዲሱ አስተዳደር ላይ መጠነኛ ስንጥቅ ይፈጠራል ብለው የሚሰጉ ብዙዎች ናቸው::ስንጥቁ ተባብሶ ሀገሪቱን ከአስፈሪ ጎሬ ውስጥ እንዳይጨምራት መንግሥት ስክነት የተሞላበት ፓለቲካዊ ውሳኔዎች እያሳለፈ ቢሄድ ትርፍ እንጂ የሚያጎደለው ነገር እንደማይኖር ገሀድ እውነታዎችን እያስተዋልን ነው::መንግሥት በየአቅጣጫው የተከሰቱትን ፓለቲካዊ ምስቅልቅሎችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የሚሄድበትን ጥበብ ፈጥኖ መኮነን አመክኖዋዊ ሊሆን አይችለም::

ኦነግ ሸኔ ላይ የተካለበ እርምጃ እንዲወሰድ ሲወተውቱ የነበሩት ወገኖች አሁን ላይ ቆመው አቋማቸውን እንዲከለሱ ሳያስገድዳቸው አልቀረም::የዳውድ ኢብሳው ኦነግ ሸኔ በሕዝብ ዘንድ ያለው ቅቡልነት በከፍተኛ ደረጃ እንዳሽቆለቆለ ለመገንዘብ ደርጅቱ እየፈጠረ ያለውን ነውጥ ዋቢ ማድረግ ብቻ በቂ ይሆናል::ይህ የኦነግ አንጃ ጊዜ በሄደ ቁጥር እውነተኛ ባሕሪው እየተገለጠ መጥቷል::በአንድ እጁ ዘንባባ በሌላ እጁ ክላሽ ይዞ ስለሰላማዊ ትግል ጥብቅና ለመቆም እንደሚዳዳው የድርጅቱ ቱባ ሹማምንቶች ከሚሰጡት እርስ በርሱ ከሚጣረስ መግለጫ እያስተዋልን ነው:: በግንባሩ የአመጻ አካሄድ በምእራብ ወለጋ ላይ ያደረሰው ውድመት ምንም እንኳን ብዙ የሕይወት መስዋእትነት እና የንብረት መጥፋትን ቢያስከትልም ፣ሰፊው ሕዝብ የድርጅቱን ፍላጎት ከወዲሁ ለመገንዘብ በመቻሉ በመንግሥት ዘንድ የነበረው እርጋታ ፍሬ እያፈራ እንደመጣ አንዱ ማሳያ ነው::

ሀገራችን የቆመችበት መስቀልኛ መንገድ በተስፋ እና በሥጋት የተሞላ ነው::በተዘረጋው አስተዳደራዊ አሻጥር ምክንያት የሚመነጩትን ግጭቶችን በተመለከተ የመንግሥት ሚና ሊሆን የሚችለው እሳት ማጥፋት ብቻ ነው::ምክንያቱም አስተዳደራዊው መዋቅር ሥርነቀል በሆነ መልኩ ካልተቀየረ ማንነትን የተንተራሱ ግጭቶች በየአካባቢው ብልጭ ድርግም ማለታቸው አይቀርም::

ሀገራችን ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ፀሐይን ለመሞቅ ከአፋፍ ላይ ቆማ አሻግራ ማማተር ጀምራለች::የነገው ፓለቲካዊ ድባብ በመንታ እና ተጻራሪ እውነታ የታጀለ ነው::ሲነጋጋ ሲል ይጨልማል እንዲሉ ወደ አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚደረገው ትግል ፈተናው ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፋ ሆኗል::የተገኘው አበረታች የለውጥ ሥርዓት ተቀልብሶ ፍጹም ገሀነማዊ፣ የእርስ በርስ እልቂት ውስጥ እንዳንገባ፣ ሥልጣን ላይ ካለው አስተዳደር በተጨማሪ የሁሉም ዜጋ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል::


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ደረጀ ይመር

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ተስፋዬ ሽብሩ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ
ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# ሰላም የራቀው ለውጥ

መላክ ቢ.



ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከተሾሙ ወዲህ በሀገሪቱ ከዚህ ቀደም ይሆናሉ ተብለው ያልተገመቱ በርካታ ፈጣን ለውጦች ተካሂደዋል።እነዚህ ለውጦች ብዙኃኑን ሊባል በሚችል ደረጃ አስደስተዋል። በነዚህ ለውጦች በጠቅላላ በሚባል ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ተጠቃሚ ሆኗል። የተከለከሉ የፖለቲካ እና የዴሞክራሲ መብቶች መፈቀዳቸው ብዙኃኑን የልቡ ተናጋሪ አድርጎታል። ይህ ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ለሰው ልጅ የላቀው ጥቅም ነው። በሌላ በኩልም በማግለል ፖለቲካ የተገለሉ እና በዚህ ሳቢያም በደረሰባቸው ወከባ ሃገር ጥለው የወጡ ዜጎች እናት ምድራቸውን ዳግም ማየት ችለዋል። ይህ ምን ያህል አስደሳች ነገር እንደሆነ ከነዚህ ሃገራቸው በዐይናቸው ትዞር ከነበረች ዜጎች በላይ የሚረዳው ማንም የለም። በአንድ በኩል በፖለቲካ አመለካከታቸው ሳቢያ በየእስር ቤቶች ታጉረው የነጻነት ቀናቸው ጋዙ እንዳለቀ ኩራዝ ጭል ጭል እያለ ተስፋ ሊያስቆርጣቸው የተቃረበ ዜጎች ዳግም የሰላም አየር መተንፈስ ችለዋል። ራሳቸውን ለመርሳት የተቃረቡ ዜጎች ከታጎሩበት እስር ቤት ወጥተው ወደቀደመው ሰላማዊ ሀይወታቸው ተመልሰዋል። የናፈቋቸውን ዘመዶቻቸውን አይተዋል። ልጅና ባለቤታቸውን አግኝተው ሃሴት ጠግበዋል። የዚህን ታስሮ የመፈታት፣ ተስፋ ቆርጦ ድንገት በተስፋ ውስጥ የመኖር ትርጉምን ከነዚህ ዜጎች በላይ የሚያውቀው የለም። አገዛዙ በማይፈልገው የተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ በመገኘታቸው ምክንያት ታስረው በነበሩ ዜጎች ምክንያት በነጻው አየር ውስጥ ሆነው በቁማቸው የታሰሩ ደግሞ ብዙሃን ናቸው። አንዱ ታሳሪ ሲፈታ የጀመረውን ትግል ሊቀጥል የተሰጠው መብት በራሱ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የዘራው ተስፋ ቀላል አይደለም።

ከዶክተር ዐቢይ በፊት በነበረው ኢሕአዴግ (አሁንም ያለው ኢሕአዴግ በመሆኑ) ሳቢያ የተፈጸሙ ግፎች እና ጭቆናዎች በአሁኑ ኢሕአዴግ ቢያንስ በግልጽ አለመታየታቸው የለውጡ አንዱ ምልክት ነው። በሌላ በኩልም ዓለም ሽንጡን ይዞ ሲሟገትላቸው የነበሩ፣ ነገር ግን የቀደመው ኢሕአዴግ በእስር ቤቱ እንዲህ አይነት ሰዎች የሉም ያላቸው የፖለቲካ እሥረኞችን እና ጋዜጠኞችን መፍታቱ፣ በአሸባሪነት ተጠርጥረው የተያዙ በርካታ ግለሰቦችን መልቀቁ መጣ ለተባለው ለውጥ በርግጥም መምጣት ምልክት ብቻ ሳይሆን ማረጋገጫ ሆኗል። ከግለሰቦች ባሻገር በአሸባሪነት ተፈርጀው የነበሩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን እና መገናኛ ብዙሀንን ክስ ማንሳት እና የተለጠፈባቸውን ፍረጃ መሰረዝም የዚሁ መልካም አጋጣሚ አንዱ ማሳያ ነው።

የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ለውጡን ሲጀምር አዕማድ ያደረጋቸው ይቅርታ፣ ሰላም እና ፍቅር በአብዛኛው አጠቃቀም ላይ ባሉ ግድፈቶች ሳቢያ ያለውላቸው እየገቡ የንትርክ አጀንዳ ሆኑ እንጂ በመሰረተ ሃቃቸው ግን በዚህች ሃገር የኖረ ጥምዝ ፖለቲካ ላይ ነፍስ ዘርተው መረጋጋትን ለመፍጠር ኃይል ያላቸው ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

በኢኮኖሚው ረገድ በኢትዮጵያ ኢሕአዴግ በሬሳዬ ላይ ►

ይላቸው የነበሩ አቋሞች ተቀይረው አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ ሪፎርሞችም ቢያንስ በውጥን ደረጃ አየር ላይ ውለዋል። ከለውጦቹ ውስጥ ትላላቅ እና መለስተኛ የመንግሥት ድርጅቶችን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለግል ባለሃብቶች የማዛወር እቅድ አንዱና ተጠቃሹ ሆኖ እናገኘዋለን።

ለኢትዮ ኤርትራ የድንበር ግጭት እልባት ለመስጠት የተላለፈው ውሳኔ እና ውሳኔውን ተከትሎም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለቱ ሀገራት አዲስ ግንኙነት መጀመራቸው ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው የለውጡ መገለጫዎች አንዱ ነው። ያ ሁሉ ሆኖ ለውጡ ግን እንደሚታየው በስኬት ብቻ የተሞላ ለውጥ አይደለም። ለምን?

## የለውጥ ተጎታቾች

በኢትዮጵያ ፖለቲካ አንዳንዶች ትንግርት ነው የሚሉት እና ከ ኢሕአዴግ ውስጥ የተፈለቀቀው ለውጥ ሕዝቡ በታሪኩ አይቶት የማያውቅ ሰው ሰው የሚሸት መሪ ይዞ ብቅ ሲል ብዙዎች በየዋህነት ይህን ለውጥ ለማርከስም ይሁን ለማኮሰስ አንድም አፍ አይከፈትም አንድም ብዕር ቀለም አይተፋም የሚል ግምት ነበራቸው። ነገር ግን ብዙም ሳይዘልቅ በሰኔ 16ቱ የሕዝብ ድጋፍ ሰልፍ ላይ የተከሰተው ዶክተር ዐቢይ ን የመግደል ሙከራ ለዚህ ለውጥ መደናቀፍ የሚሰሩ ብዙዎች መኖራቸውን ማሳያ ምልክት ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ጋብ ከማለቱ በሶማሌ እና ኦሮሚያ ድንበር ላይ የተቀሰቀሰው ግጭት ለቁጥር የሚያታክቱ የኦሮሞ ተወላጆችን ከሶማሌ ሲያሰድድ በዚህ መጠን የሚቀሰቀስ የሕዝብ ለሕዝብ ጸብ ይኖራል ብሎ የገመተ አልነበረም። በቤኒሻንጉል በኩል በበርታ ብሄር ወጣቶች በኩል ተነስቷል የተባለ ጸብ ብዙሃን የክልሉን ነዋሪ አማሮች ሲያፈናቅል እና የኦሮሞ ብሄር ተወላጆችንም በዚያው መጠን ሲያባርር በክልሉ ይህንን የእሳት ማቀጣጠል ሚና ተጫወቱ የተባሉ የሕወሓት ባለስልጣናት ላይ እርግማን ሲወርድ ነበር።

ከዚህ ቀደም ሕገመንግስቱን መናድ የሚባለው ፍረጃ አሁን ለውጡን ማደናቀፍ ወደሚል አዲስ ቃል ብቅ ያለውም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በመላው ሃገሪቱ የተከሰቱትን የሰላም መደፍረስ ሙከራዎች ብቻ ሳይሆን መሬት የረገጡ መገለጫዎችን በማየትም ነው። በርግጥም የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር በሙስና እና በሰብኣዊ መብት ጥሰት ፈጻሚዎች ላይ የወሰዳቸው እርምጃዎች የትግራይን ተወላጆች ብቻ ለይቶ ያጠቃ ነው በሚል ምክንያት የተቃወሙት የዚያው ክልል ተወላጅ የሆኑ አክቲቪስቶች እና የቀድሞ የፌዴራል አዛዠ ናዛዠ የነበሩ ፣ አሁን ግን መቀሌ ለይ መሸገው ያለስራ የተቀመጡ የሕወሓት ባለስልጣናት ናቸው።

በወንጀል የሚፈለጉ ከያሉበት ተለቃቅመው ወደፍርድ ይቀርባሉ መባሉን ተከትለው መቀሌ ላይ የከተቱት የሕወሓት ባለሥልጣናት በኢትዮጵያ ውስጥ አለመረጋጋት እንዲፈጠር ከኂላ ሆነው ሴራ ይሸርባሉ መባልን ተከትሎ ዶክተር ዐቢይም ይሁኑ ሌሎች የፌዴራሉ መንግስት ባለስልጣናት የለውጥ አደናቃፊ ኃይሎች በማለት ማስጠንቀቂያ ቢጤ ሲወረውሩላቸው ቆይተዋል። በፌዴራል ደረጃ በወንጀል ተጠርጥረው የሚፈለጉት የቀድሞ የደህንነት ባለስልጣን በመቀሌ ተሸሽገው ከዐቃቢ ሕግ ጋር ሌባና ፖሊስ ሲጫወቱ አንዳንድ ጊዜም ትግራይ የሃገሪቱ አንድ አካል መሆኗን ፌዴራል የማይደፍራት ክልል እስክትመስል ድረስ ወንጀለኛን አሳልፈህ ስጥ አልሰጥም ክርክር ውስጥ ሲገባ የለውጡ ተቀባይ እና ተገዳዳሪ ማን እንደሆነ በግልጽ ያሳየ ክስተት ሆኗል።በሌላ በኩል በሰላም ለመታገል ወስኖ ሃገር ውስጥ የገባው ኦነግ በትጥቅ ትግል ዳግም የሰላም መደፍረስ ምክንያት ሲሆን አሁንም የነዐቢይ ን ለውጥ ከልብ ሊቀበል ቀርቶ ለመቀልበስ እንደሚሰራ አሳይቷል። በተደጋጋሚ መግለጫው የነለማን ቡድን ሲከስስ እና የኦሮሞን ጥቅም የማያስከብር እያለ ሲወቅስ የቆየው ኦነግ ጭራሹን ጭልጥ ወዳለ ጦርነት ገብቶ ማወዛገቡን ቀጥሏል።

## ለውጡ ያጣው ሰላም

ፕሮፌሰር ህዝቅያስ አሰፋ “የሰላም እና የእርቅ ትርጉምና መንገዶች” በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ ላይ እንዳሉት ሰላም ጦርነትን ወይም በገሃድ የሚታይ ሁከትን ማስቆም ነው ብለው በሚያምኑ ወገኖች ዘንድ የሕግና የሥርዓት መጠበቅ ለምሳሌም ውንብድና፣ ግድያ፣ ኀብረተሰባዊ ብጥብጥና ረብሻ አለመኖር የሰላምን መኖር የሚያመለክቱ መገለጫዎች ናቸው ።ይህንን አይነቱን ሰላም በሃገር ውስጥ ለማስፈን ፍርድ ቤት እና የፖሊስ ኃይል እንዲሁም የጦር ሃይሎችና እስር ቤቶች አስፈላጊ ናቸው ይላሉ ፕሮፌሰር ህዝቅያስ። ነገር ግን በኃይል የሚመጣ ሰላም ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ አይደለም ባይ ናቸው።

በኢትዮጵያ ሰላም የሚመጣበት መንገድ ከዚህ አሰራር አያልፍም የሚሉ ብዙዎች ሰላምን ለማስፈን ኃይል መጠቀም አማራጭ መሆኑን ያሰምሩበታል። ለምሳሌም በኦነግ እና በማዕከላዊው መንግስት በኩል ያለው ፍጥጫ እንዲፈታ እስካሁን ለምን ኃይል አልተጠቀመም በማለት ማዕከላዊ መንግስቱን ይከስሳሉ።

በሌላ በኩል እስከግጭት እና ጦርነት ለደረሰ የሰላም መደፍረስ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች ለይቶ ማከም ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ያስችላል የሚሉት ፕሮፌሰር ህዝቅያስ በጠንካራ መሰራት ላይ የሚገነባ ሰላም ለማምጣት የበሽታውን ምልክቶች ዐይቶ ኪኒን መዋጥ ብቻ ሳይሆን የበሽታውን ምንነት ለይቶ ከስሩ ማድረቅ ጠቃሚ መሆኑን በመጽሐፋቸው ይገልጹታል።

የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ሰላምን ለማምጣት ከግጭት ሳይሆን ከመነጋገር በሚጀምር መልኩ አብሮ መስራት ተገቢ ነው ፣የሚል መነሻ ይዞ ሰላምን ፍለጋ የተሰማራ አካል ነው ብለን ብንሰይመው በዚህ ሂደት ሰላምን ማስፈን ይችላል ወይ የሚል ጥያቄም አብሮ ይነሳል። በርግጥም ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ከዚህ የተሻለ መስመር የለም። ነገር ግን ጊዜ መፍጀቱ ግልጽ ነው።

ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ሰላም የዚህች ሃገር ዋና ጥያቄ ሆኖ ወደመድረኩ ብቅ እያለ ነው። ባሳለፍነው ሳምንት የትግራይ እና አማራ ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች በሃይማኖት አባቶች እና የሃገር ሽማግሌዎች ተከብበው በሂልተን ሆቴል ባደረጉት ዝግ ድርድር ለሰላም በአንድ ሃሳብ ለመስራት ቃል ገብተዋል። አቶ ገዱም ይሁኑ አቶ ደብረጽዮን “የሚተኮስ ጥይት የለም” በማለታቸው ይህ ቃላቸው እንደፊርማ ይያዝላቸው ተብሏል።የሁለቱ ክልል ህዝቦች በተለይ በራያ እና በወልቃይት ግዛቶች የይገባኛል ጥያቄ ምክንያት መኳረፍ ውስጥ መግባታቸው የሚዘነጋ አይደለም። ከዚያም ባለፈ በጎንደር የትግራይ ነዋሪዎች ላይ ማሳደድ ተደርጓል በሚል በድንበር አካባቢ ባሉ ሰፈሮች በሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን እስከመሃል ትግራይ በዘለቀ ቅሬታ ከጎንደር ነዋሪዎች ጋር የገቡበት ኩርፊያም ያንኑ ያጠናክራል። በምዕራብ ወለጋ የኦነግ ሰራዊት በሰላም ለመታገል የገባውን ቃል አክብሮ ወታደሮቹ ከሽምቅ ውጊያ እንዲቆጠቡ በኦነግ አመራሮች ላይ ሽማግሌዎች አባታዊ ቁጣቸውን ገልጸው ነበር። በዚህም የጉጂ አካባቢ የኦነግ ጦር መሪን ጨምሮ ብዙዎች የአሸማጋዮቹን ቃል አክብረው መግባታቸው አንድ የሰላም የተስፋ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር በአየር ድብደባ ታግዞ በኦነግ ካምፖች ላይ የከፈተው ጥቃት የታለመውን ሰላም ማጣት ይችላል ወይ የሚለው ጥያቄ የብዙሃኑ ነው። ምክንያቱም ሁሌም ጦርነቶች ጦርነትን፣ አመጾች አመጽን እንጂ ሰላምን ሲወልዱ አልታየምና።

በዚህ በኩል በንግግር ሰላም ያልፈለገ ኃይል

**ለውጥ በባህሪው የሁሉንም ወገን ተቀባይነት ማግኘት የሚችል ሂደት አይደለም። በለውጥ አብዛኛው ቢጠቀም ጥቂቱ ግን ጥቅም የቀረበት ነው። ብዙው ቢያመሰግነው ጥቂቱ ደግሞ የሚያኮስሰው ሂደት ነው። የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ከላይ እንዳልነው ሁሉንም ሊባል በሚችል መልኩ ሕዝቡን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ ያደረጉ ለውጦችን ቢተገብርም በዚያው መጠን የረካ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ቅሬታ የገባው ማኅበረሰብም የተፈጠረ መስሏል**

ቀሪውን በ ገጽ 12 ይመልከቱ

# ብሄርተኝነት ከታሪክና ከንድፈ ሃሳብ አኳያ



ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

ባለፉት ሃምሳ ዓመታት የሀገራችንን እጣፈንታ የወሰነው ዋነኛ ጉዳይ ምንድነው ቢባል አፍን ሞልቶ ብሄርተኝነት ነው ማለት ይቻላል:: በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተፀንሶ ፣ በዘውጌ አማፂያን ድርጅቶች አማካኝነት የተወለደውና ያደገው ‹‹የብሄረሰቦች ጥያቄ›› አንድ አብዮታዊ ትውልድ ሀገርንና ህዝብን ይዞ የወደቀበት ሰፊ ገድል ነው:: በተለይ ባለፉት 27 ዓመታት በሀገራችን የማንነት ፖለቲካ የረገጠው ፅንፍ ከአህጉረ አፍሪካ ይልቅ ከቀድሞዎቹ ሶቭየት ህብረትና ዩጎዝላቪያ ተርታ አሰልፎናል::

ከተሞክሮ እንዳየነው የብሄርተኝነት ፖለቲካ ፍትህና ርትዕ ፣ ነፃነትና እኩልነት አላመጣም:: ሀገራዊ ሰላምና ወንድማማችነትን አላሰፈነም:: ይልቁንስ በሀገራዊና በብሄረሰባዊ ማንነት መካከል ባላንጣነት በመፍጠር በማህበረሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የእርስ በርስ መጠራጠር ፣ አለመረጋጋት ፣ ግጭትና ደም መፋሰስን አባብሷል:: ሀገሪቱን ከብተና አፋፍ አድርሷታል::

ነገር ግን ብሄርተኝነት በተግባር ያሳደረብንን ተፅእኖ የሚመጣጠን ትኩረት አልተሰጠውም:: በጠመንጃ አፈሙዝ ተጫነብን እንጂ በአግባቡ ተገንዝበንና አምነን አልተቀበልነውም:: በየመገናኛ ብዙሃኑ ስለብሄርተኝነት የሚደረጉ ውይይቶችን የምንከታተል ከሆነ በምሁራኖቻችን ፣ በፖለቲከኞቻችንና ፣ በሌላውም ህዝብ መካከል ስለ ርዕሰ ጉዳዩ እጅግ የተዛባና የተዘበራረቀ ግንዛቤ መኖሩን እናስተውላለን:: ምናልባት ለውይይት ከረዳ በሚል በዚህ ፅሁፍ ስለ ብሄርተኝነት ምንነት ከታሪክና ከንድፈ ሃሳብ አኳያ ጥቂት መነሻ ሃሳቦች ለማቅረብ እሞክራለሁ::

## 1. ለመሆኑ ብሄርተኝነት ምንድነው?

ብሄርተኝነት ሰፊ ትርጉም ያለው መልከ ዝንጉርጉር ግንዛቤ ነው:: የሀገር ፍቅርና የአርበኝነት ስሜት ነው:: ባህል ፣ ታሪክና ቅርስ ጠባቂነት ነው:: ዘውጋዊ ተቆርቋሪነትና ትግል ነው:: ስሜት ፣ ድርጊት ፣ እምነት ፣ አስተምህሮን ያዛነቀ ጉዳይ ነው:: የብሄርተኝነት መሥራች ቃል የሆነው ‹‹ብሄር›› የማህበረሰቦችን አሃዳዊነት የሚያመለክት አስተሳሰብ ነው:: አሃዳዊነቱ የመንግሥትን ፖለቲካዊ ባህሪ ፣ የህዝብን ባህላዊ ባህሪ ወይም ሁለቱንም ያጣመረ ሊሆን ይችላል:: ሀገራዊና ዘውጋዊ መልኮችም አሉት:: እነዚህን ሁሉ በማዳመር ብሄርተኝነትን በፖለቲካዊ ርዕዮትነትና ማህበራዊ ንቅናቄነት በሁለት ልንከፍለው እንችላለን::

ብሄርተኝነት እግሮቹን በድሮና ዘንድሮ አድማሶች ላይ አንፈራጦ የቆመ በሁለት አቅጣጫ ተመልካች እሳቤ ነው:: በአንድ ወገን የጥንታዊውን ማህበረሰብ አፈጣጠር ፣ እምነት ፣ ማንነትና የህይወት ውጣ ውረድ የሚያቅፍ ታሪካዊ ፍልስፍና ነው:: በሌላ ወገን በዘመናዊነት ሂደት ውስጥ የሚነሱ (እንደ ዴሞክራሲ ፣ ፍትህና ልማት የመሳሰሉ) ትግሎችና ሙግቶች አካል በመሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ ማህበረሰቦችን ፣ ተቋማትን ፣ መደባትን ፍላጎቶችና ርዕዮቶች ያንጸባርቃል:: ስለሆነም ብሄርተኝነትን በተሟላ ሁኔታ ለመረዳት ከታሪክና ከንድፈ ሃሳብ አኳያ መመልከት ይኖርብናል::

## 2. ብሄርተኝነት ከታሪክ አኳያ

የብሄርተኝነትን ታሪካዊ አነሳስና እድገት ያጠኑ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶች ያቀርባሉ:: አንዳንዶች ግዛታዊ መልክ ያላቸውና በሥርወ መንግሥታዊ መርህ (dynastic principle) ላይ የቆሙ ብሄራዊ ማህበረሰቦች በተለያዩ ክፍለዓለማት በተለያዩ ዘመናት የታዩ መሆናቸውን ያምናሉ:: ለምሳሌ በአርመንያና በኢትዮጵያ የተመሰረቱትን ዓይነት ታሪካዊ ብሄሮች በጥንታዊና ማዕከላዊው የታሪክ ዘመናት ተከስተዋል ይላሉ:: ሆኖም አብዛኞቹ የመስኩ ምሁራን ብሄርተኝነትን ከዘመናዊው ዓለም አፈጣጠርና ባህሪ ጋር ያቆራኙታል:: በአጠቃላይ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ቅርፃችና ባህሪያት ያላቸውን ሶስት የብሄርተኝነት ታሪካዊ እድገቶችን መለየት ይቻላል::

### ሀ. ግዛታዊ ብሄርተኝነት

በሰው ልጆች ረዥም ታሪክ መንግሥታት በጎሳዊ ፣ ነገዳዊ ፣ ኃይማኖታዊ ፣ አፄያዊ ፣ ሥርወ መንግሥታዊና ከተማዊ ፣ ወዘተ ቅርጾች ተከስተዋል:: ነገር ግን ዘመናዊው ብሄራዊ መንግሥት በ16ኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዝ ሲያቆጠቁጥና በፍጥነት በምዕራብ አውሮፓ ሲስፋፋ ፣ ከዚያ ቀደም ከታዩት ፖለቲካዊ ማህበራት በቅርፁም ፣ በይዘቱም ፣ በማህበራዊ ግቡም የተለየ ሆነ:: አዲሱ መንግሥት ፊውዳላዊ ጎጦችና አውራጃዎችን በመጨፍለቅ ፣ ድንበራቸው በውል ወደተከለለ ጠንካራ የፖለቲካ አሃድነት አሰባሰባቸው::

እያደርም ማዕከላዊ መንግሥቱ የሥልጣን ፣ የሃይልና ሉዓላዊነት ዘርፎችን በመጠቅለል ብሄራዊ አቋም ያዘ:: ይህ ሂደት መንግሥት በዜጎቹ ሁለንተናዊ ህይወት ውስጥ ይበልጥ ሰርጎ እንዲገባና የአንድነት መንፈስ እንዲያነቃቃ አስቻለው:: ምንም እንኳን አነሳሱ መደባዊ ፣ ሃይማኖታዊ ፣ ዘውጋዊና ሌሎችም ማህበራዊ ውጥንቅጦች ቢኖሩትም መንግሥት ፖለቲካዊና ባህላዊ ድንበሮቹ እንዲሰናኙ መጣጣርና ራሱን እንደ አሃዳዊ ብሄር መቁጠር ጀመረ:: ስለዚህም ብሄራዊ መንግሥት ተባለ::

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው የወቅቱ የብሄራዊ አንድነት ግንዛቤ ጭፍልቅነት አልነበረም:: ባህላዊና ማህበራዊ እርከኖችን ደምስሶ በአዲስ ለመቀየር አልተነሳም:: ይልቁን ብሄራዊ አቋሙን የሚገልፅ ሳዕላይ መንፈስ በጋራ ታሪክ ፣ ባህል ፣ እሴቶችና ተቋማት ላይ ለመገንባት ሞከረ እንጂ:: የብሄራዊ አንድነቱም እሳቤ ከሁሉም በላይ በትዕምርታዊነት የሚገለፅ ነበር:: ስለዚህም የገዥ መደቡ ታሪካዊና ባህላዊ ሃብት በተለይ ቋንቋና ሃይማኖት ለአዲሱ ሀገራዊ ማንነት ጥሬ ዕቃ ሆነ:: ሥርወ መንግሥታዊው ዘውድ ደግሞ አንድነቱን የሚያስተሳስር ምልክት ተደረገ::

በአጠቃላይ ‹‹በቅይጥነት ውስጥ ያለ አንድነት›› ወይም ብሄራዊነት እንደ መደበኛ የመንግሥት ተልእኮ በመቆጠሩ ፣ ብሄራዊ መንግሥት ባህላዊ አንድነት ያላቸው ህዝቦች የሚመሰርቱት ፖለቲካዊ አስተዳደር ሆነ:: ይህ በሥርወ መንግሥታዊ መርህ ላይ የተመሰረተ የብሄርተኝነት እድገት ደረጃ ግዛታዊ ብሄርተኝነት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ፣ በአንድ አገር ፖለቲካዊ ቅርፅ ውስጥ የጋራ ማንነት ፣ ስሜትና ራዕይ ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚፈልግ ዘይቤ ነው::

### ለ. ዜግነታዊ ብሄርተኝነት

መንግሥታዊነት የፈጠረው ግዛታዊ ብሄርተኝነት ከአንድ የታሪክ ዘመን ወደሌላኛው መሸጋገሪያ ድልድይ እንደመሆኑ መጠን ፣ ከፊል ፊውዳላዊና ከፊል ዘመናዊ ባህርያትን አዳቅሎ የያዘ ነበር:: ከዚህ የቀጠለው የብሄርተኝነት ታሪካዊ እድገት በአውሮፓ ዘመናዊነት በከፍተኛ ደረጃ በፈካበት በ18ኛው ምዕት ዓመት የተነሳው የአብርሆት ፍልስፍና ባቀነቀናቸው እንደ ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ሰብአዊነትና ዓለማቀፋዊነት በመሳሰሉ ፅንሰ ሃሣቦች ላይ የተመሰረተ ነበር:: በተለይ ታላቁ የፈረንሳይ አብዮት እ.ኤ.አ በ1789 ሲፈነዳ እነዚህን እሳቤዎች ለብሄራዊ መንግሥት ምሶሶነት በማዋል በብሄርተኝነት ግንዛቤ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ አስከተለ::

ነፃነትና እኩልነት የአብዮታዊው የብሄርተኝነት መርህ (revolutionary principle) ሁለት ቁልፍ እሳቤዎች ናቸው:: ብሄራዊ መንግሥት ነፃ ህዝቦች ወይም ዜጎች በውዴታ የሚመሰርቱት በራስ የመወሰን አስተዳደር ነው:: ብሄራዊ መንግሥት ዜጎቹን በይስሙላ ሳይሆን በተጨባጭ እኩልነት የሚያቅፍና በዜጎቹም የሚወከል አስተዳደር ነው:: በስመጥሩ ምሁር ኤሊ ኬዱሬ አባባል ‹‹ለፈረንሳይ አብዮተኞች ብሄር ማለት አስተዳደራቸውን በመፈቃቀድ ያቆሙ ግለሰቦች ስብስብ›› ነው:: በዚህ መንገድ አብዮቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ብሄራዊውን ማህበር በህዝባዊ ሉዓላዊነት መርህ ላይ በመገንባትና ለሰፊው ተርታ ህዝብ ሙሉ የዜግነት ክብር በማጎናፀፍ ‹‹የህዝባዊ ብሄር›› ዘመን የተባለውን ተሞክሮ አበሰረ::

ይህ ታሪካዊ እድገት በብሄራዊ መንግሥት ግንዛቤና ተግባር ላይ አንድ እርከን እመርታ አስከተለ:: ብሄራዊ መንግሥት ከታሪካዊ ክስተትነት በተጨማሪ ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤ ሆነ:: በአንድ በኩል ይህ ግንዛቤ የቀድሞው ቀጣይ በመሆኑ ፣ በፖለቲካዊው መንግሥትና በባህላዊው ብሄር መካከል የአንድ ለአንድ ጥምረትን መርህ አጠናከረው:: ምንም እንኳን መንግሥት ከገዥ መደቦች እጅ ወጥቶ በህዝብ ባለቤትነት ሥር ቢውልም ፣ አውቆና አቅዶ ወጥ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር የመጣጣር ግዳጁን አፀና:: በመሆኑም የቋንቋ ▶

፣ የባህልና ሃይማኖት ልዩነቶች እንደ ብሄራዊ ተግዳሮት መታየታቸው ከናካቴው አልቀረም:: ነገር ግን አዲሱ ርዕዮት የብሄርን ጭብጥና መለኪያ ከነዚህ ጉዳዮች ይልቅ በአሃዳዊ የፖለቲካ ሥልጣንና በጋራ ዜግነት ላይ እንዲወሰን አደረገ:: በዚህም ምክንያት ‹‹ዜግነታዊ ብሄርተኝነት›› የሚል ስያሜ አገኘ::

### ሐ. ዘውጌ ብሄርተኝነት

ሶስተኛውና በዘውጌ መርህ (ethnic principle) ላይ የቆመው የብሄርተኝነት ግንዛቤ ርዕዮታዊ መሰረቱ በ18ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃና በ19ኛው መባቻ የተነሳው ልብ ወለዳዊነት/ሮማንቲሲዝም/ የተባለው ሰፊ ንቅናቄ ባራመዳቸው ተፈጥሮአዊነት ፣ ግላዊነት ፣ ጥንታዊነት በመሳሰሉት ፅንሰ ሃሳቦች ላይ ነበር:: በተለይ በጀርመን ፈላስፎች የተቀነቀነው የዚህ እሳቤ አበይት መለያዎች ብሄርን ደመነፍሳዊ አንድነት በሚያላብሱ ሥነህይወታዊ ተምሳሌቶች (አካል ፣ ቤተሰብ ፣ ዘር ፣ ደም ፣ ውልደት ፣ ተፈጥሮ) መግለፁ ፤ ከፖለቲካዊው መንግሥት ወደ ባህላዊው ብሄረሰብ ወይም ዘውግ ትኩረቱን ማዞሩ ፤ ልሂቃን በህብረተሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ማጉላቱና ዘውጌ ማህበረሰቦች የየራሳቸውን ‹‹ድንግል ተፈጥሮና ወርቃማ ዘመናት›› እንዲመረምሩ መገፋፋቱ ናቸው::

በዚህ አመለካከት መሰረት ብሄር ልዩ ተፈጥሮአዊ ማህበረሰብ ወይም ‹‹አምላክ የግሉ ባህሪ የቸረው የሰብአዊ ዝርያ ክፍል ነው››:: ስለዚህም ብሄሮች በተፈጥሮ ይወለዳሉ እንጂ በሰው ልጅ አይሰሩም:: ተፈጥሮ የምትገለፀው በግላዊነት ስለሆነ ፣ የብሄሮች ማንነታቸው መገለጫ ልዩነታቸው እንጂ ሁሉን አቀፍነታቸው አይደለም:: ቋንቋ ደግሞ ዋነኛው የተፈጥሮ መለያቸው ነው:: ዘውግ ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ከሁሉ የላቀ አግባብነት ያለው የፖለቲካ ማህበር መሰረት ነው:: ብሄርን የሚወስነውና የሚፈጥረው ሰው ሰራሹ መንግሥት አይደለም:: በተገላቢጦሽ መንግሥትን መመስረትና መወከል ያለበት ተፈጥሮአዊው ዘውግ ነው::

ይህ ሥር ነቀል እሳቤ ዘውግን ከባህላዊነት በቀጥታ ወደ ፖለቲካዊነት አሳደገው:: ብሄራዊነት ከፖለቲካ አንድነት ወደ ባህል አንድነት መሆኑ ቀርቶ ፣ ከባህል አንድነት ወደ ፖለቲካ አንድነት መንዝዝ ማለት ሆነ:: የብሄራዊ አሃድነት ግንዛቤ በአንፃራዊነት ሰፋ ካለው ታሪካዊና ባህላዊ ተመሳስሎ ወይም ግዛታዊና ዜግነታዊ ቋጠሮ ወደጥሬ ደመነፍሳዊ የደም ፣ ቋንቋና ዘልማድ ድንበሮች ጠበበ:: ህዝባዊ ሉዓላዊነት ወደዳር ተገፍትሮ በምትኩ ህዝባዊ ልዩነት ገነነ:: ዘውግ የብሄርተኝነት አልፋና ኦሜጋ ሆነ:: ብሄርተኝነት ማለት ለዘውጌ ማህበረሰብ የሚኖር ታማኝነት ወይም ቀናኢነትና ከሌላ ማናቸውም (ባዕዳዊ) አገዛዝ ሃርነት የመውጣት ፍላጎት ተደርጎ ተወሰደ:: ይህ በዘውግ መርህ ላይ የተመሰረተ ከላሽ አስተምህሮ ውሎ አድሮ ዘውጋዊ ወይም ልሣናዊ ብሄርተኝነት ለመባል በቃ::

### 3. የብሄርተኝነት ንድፈ ሃሳቦች

የብሄርተኝነት ጥናት በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ጉልህ ስፍራ መያዝ የጀመረው ከ1960ዎቹ ወዲህ ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የተከናወኑት ሰፊ ጥናቶች በብሄሮችና ብሄርተኝነት መሰረታዊ ተፈጥሮ ፣ መገለጫ ባህሪያትና ማህበራዊ ፋይዳዎች ረገድ የተለያዩ እሳቤዎችን ፣ ፈርጆችን ፣ ንድፈ ሃሳቦችንና ሥነዘዴዎችን አበርክተዋል:: በአጠቃላይ በመስኩ ምሁራን የሚደረጉት ታሪካዊና ንድፈ ሃሳባዊ ሙግቶች ማጠንጠኛ ከሆኑት ብሄሮች ‹‹ጥንታዊ ናቸው ዘመናዊ ?›› ፣ ‹‹ሰው ሰራሽ ወይስ ተፈጥሮአዊ ?›› ፣ ‹‹አውሮጳዊ ወይስ አለማቀፋዊ ?›› በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ሦስት ዐበይት አስተምህሮዎች ተንፀባርቀዋል::

### ሀ. ደመነፍሳዊነት

በታሪካዊ ሂደቱ እንዳየነው ደመነፍሳዊነት በአብዛኛው በዘውጌ ብሄርተኞች ዘንድ የሚቀነቀን አስተሳሰብ ነው:: ይሁን እንጂ እንደ ክሊፎርድ ጊርት ፣ ፒየር ቫንደንበርግ ፣ ኤድዋርድ ሺልስ ያሉ አንዳንድ የማህበራዊ ሳይንስ ሊቃውንትም የደመነፍሳዊነትን ማህበራዊ ምንጭ በመተንተን አስተሳሰቡን ሳይንሳዊ መሰረት ለማስያዝ ሞክረዋል:: ደመነፍሰኞች ብሄርን እንደ ተፈጥሮአዊ ፣ ሥነህይወታዊና ዝንተ ዓለማዊ ክስተት ይመለከታሉ:: በዋነኝነት ደም ፣ ቋንቋ ፣ ዝምድናና ዘልማድን ለብሄር ማንነት ወሳኝ አድርገው ይደመድማሉ:: ይህ ማለት ብሄሮች እንደ ቤተሰባዊ የተፈጥሮ ማህበረሰቦች ወይም እንደ ‹‹ሰፊ ዝምድና›› ይቆጠራሉ::

በዚህ እይታ መሰረት ብሄሮች በየትም ሥፍራ ፣ በማንኛውም ማህበረሰብና ዘመነ ታሪክ ሊገኙ ይችላሉ:: ስለዚህም ለብሄሮች አውሮጳዊ መነሻ የሚሰጠው የዘመነኝነት አመለካከት ውድቅ ነው:: ነገር ግን የብሄሮች ተፈጥሮአዊነት የሚገለጠው በታሪካዊ ሂደቶች በመሆኑ በተለያዩ ዘመናት ይታያሉ:: አብዛኞቹ ዘመናዊ ብሄሮች ጥንታዊ ባህላዊ መሰረቶች ቢኖራቸውም ለረዥም ዘመናት ፖለቲካዊ ንቃት ሳይፈጥሩ ሊኖሩ ይችላሉ:: በዚህ ምክንያት በየዘመናቱ አዳዲስ የብሄር ንቅናቄዎች መፈጠርና የብሄሮች መከሰት የሚቆጠረው ‹‹ካሸለቡበት እንደመንቃት›› ተደርጎ ነው::

ደመነፍሳዊነት በተለይ በ19ኛው ምዕት ዓመት ሰፊ ተቀባይነትን ለማግኘት ችሎ ነበር:: ሆኖም ዛሬ በማህበራዊ ሳይንቲስቶች ዘንድ እምብዛም ተቀባይነት የለውም:: ምክንያቱም ይህ አመለካከት ለሰው ልጅ ባህሪ ህንፀት ከባቢያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ያላቸውን አስተዋጽኦ ከማሳነሱ በተረፈ ፣ ብሄርተኝነትን በዘረ መላችን የተደነገገና ሊያመልጡት የማይቻል የተፈጥሮ እጣ ፈንታ አድርጎ ይደመድማል:: በሌላ አነጋገር በሥነዘዴ ረገድ የብሄርተኝነትን ጥናት ከታሪካዊና ህብረተሰባዊ ምርምር ቅጥር ውጭ ያደርገዋል::

### ለ. ግንባታዊነት ወይም ዘመናዊነት

በአብዛኞች የማህበራዊ ሳይንስ ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው የግንባታዊነት አስተምህሮ የደመነፍሳዊነትን ተፈጥሮአዊነት ፣ ሥነ ህይወታዊነትና ዝንተ ዓለማዊነት ውድቅ ያደርጋቸዋል:: ብሄሮችን በታሪክ ሂደት የሚፈጠሩና የሚያድጉ ሰብአዊ ቡድኖች አድርጎ በማየት ከተፈጥሮአዊ ይልቅ ምጣኔ ሀብታዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበረ-ባህላዊ ገለፃዎችን ይመርጣል:: ብሄሮችም ሆነ ብሄርተኝነት የተወሰነ የሰው ልጅ ማህበራዊ እድገት ደረጃ ውጤቶች ናቸው:: ይህም ኢንዱስትሪያዊ ከበርቴ ማህበረሰብ በመባል ይታወቃል:: ብሄራዊ መንግሥታት የዚህ ሥርዓተ ማህበር ፖለቲካዊ ምሶሶዎች ናቸው ይለናል::

በዘመነኝነት እሳቤ መሰረት ብሄርተኝነት በአውሮፓ በ16ኛው መቶ የተነሳው የዘመናዊው ዓለም ሳይንስና ፍልስፍና እያደር በልማዳዊ ማህበረሰቦች ላይ ላስከተለው ሁለገብ ሥርዓታዊና ማህበረ-ባህላዊ ውጥረትና ቀውስ የተሰጠ አደላዳይ ግብረ መልስ ነው:: ስለሆነም ከአውሮፓ ውጭ ባለው ዓለምና በቅድመ ዘመናዊነት ጊዜ የረባ ፋይዳ አልነበረውም:: ታዲያ ለብሄርተኝነትና ብሄሮች አፈጣጠር ወሳኝ የሆኑት የዘመነኝነት መልኮች ምንድን ናቸው? ይህን አስመልክቶ በምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ረገድ ለሚከሰቱ ላዕላይ ኃይሎች የበለጠ ድርሻ የሚሰጡ ሊቃውንት ‹‹ሥርዓት አደላዳዮች›› በመባል ይታወቃሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ከህብረተሰብ ታህታዊ መሰረት ለሚነሱ ታሪካዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ኃይሎች ቅድሚያ የሚሰጡ ‹‹ማህበረ-ባህላዊ አደላዳዮች›› የሚል ስያሜ አግኝተዋል::

### ሐ. ዘውጌ ትዕምርታዊነት

ለደመነፍሳዊነትና ዘመናዊነት እሳቤዎች አስታራቂ በመሆን በብሄርተኝነት ጥናት መስክ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ የመጣው አስተምህሮ ዘውጌ ትዕምርታዊነት ይባላል:: በዘውጌ ትዕምርታዊነት እምነት ብሄርተኝነት እንደተሟላ ፖለቲካዊ ርዕዮትና ማህበራዊ ንቅናቄ ዘመነኛ ክስተት ነው:: ያምሆኖ አብዛኞቹ ብሄርተኛ ንቅናቄዎች ቅድመ ዘመናዊ ዘውጌ መሰረቶች አላቸው:: በዚህም ምክንያት በርካታ ዘመናዊ ብሄራዊ መንግሥታት የታሪካዊው ብሄር ቅሪት የሆኑ አስኳል ወይም በኩራዊ ዘውጎች ይስተዋልባቸዋል:: እነዚህ ታሪካዊና ባህላዊ ቅሪቶች ቅድመ ብሄሮች ወይም ዘውጌ ብሄሮች ሲባሉ ፣ የጋራ/አስተሳሳሪ ስሜታቸውም ቅድመ ብሄራዊ ወይም ዘውግ ተኮል ሊባል ይችላል::

በጥልቅ ታሪካዊ ትንተና ላይ የተመሰረተው የዘውጌ ትዕምርታዊነት አቀራረብ በብሄሮች አፈጣጠርና ዘላቂነትም ሆነ መለያ ጠባያቸውን በመተንተን ረገድ ትዕምርታዊ ጉዳዮች በሚኖራቸው ማዕከላዊነት ላይ ያተኮረ ነው:: የብሄራዊ ባህልን ዘልማዳዊና ቅድመ ዘመናዊ ይዘቶች ፣ ለምሳሌ ትውፊቶችን ፣ ገድሎችን ፣ ትዕምርቶችን ፣ ጀግኖችን ፣ ወዘተ በመለየት ሚናቸውን ለማብራራት ይጥራል:: ዘውጌ ትዕምርታውያን ብሄሮችን በታሪክ ራቅ አድርገው በመግፋት የአብዛኞቹን ብሄርተኝነቶች መንታ ባህሪ ማለትም ዘውጌነት ከዜግነታዊነት ፣ ዓለማዊነት ከኃይማኖታዊነት ፣ አሃዳዊነት ከብዝሃዊነት ፣ ዘመናዊነት ከጥንታዊነት በቅጡ ለማስረዳት ይሞክራሉ::

እንደ መደምደሚያ ብሄርተኝነት የታሪካዊ ለውጦች ነፀብራቅ እንጂ ከየትኛውም ዘመን ፣ ክፍለ ዓለም ፣ ማህበራዊ መደብና ርዕዮተ ዓለም ጋር ለዝንታለሙ የተቆራኘ ክስተት አይደለም:: በባህሪው አዳዲስ መንግሥታትን ገንቢ ወይም ነባሮችን አፍራሽ ፣ ነፃነትን ገፋፊ ወይም አጎናፃፊ ፣ ሰላማዊ ወይም ፀባጫሪ ፣ አካታች ወይም አግላይ ፣ ህገ መንግሥታዊ ወይም ህገወጥ ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል::

ከስልት ረገድ አንዳንዶቹ ብሄርተኛ ንቅናቄዎች በህጋዊነት ፣ በግልፅ ግባቸውን በማስቀመጥና ራሳቸውን በማስተዋወቅ ሲንቀሳቀሱ ሌሎች ደግሞ ህገወጥ ፣ ድብቅብቅና ሴረኛ አካሄድ ሊከተሉ ይችላሉ:: አንዳንዶች ለዘብተኛ ጥገናዊ አቋም በመያዝ በነባራዊው ማዕቀፍ ውስጥ መታገልን ሲመርጡ ሌሎች በአብዮታዊ ፅንፈኝነት ነፃ መንግሥትነት እስከመጠየቅ ይሄዳሉ:: በደምሳሳው ብሄርተኝነት በፖለቲካዊና ማህበራዊ ግቡ ፣ በተዋናዩ ፣ በመርሁና በባህሪው ዝንቅነት ምክንያት ‹‹መንግሥት ገንቢ›› ፣ ‹ዳራዊ›› ፣ ‹‹ገንጣይ›› ፣ ‹‹ውህደታዊ›› ፣ ‹‹ተስፋፊ›› ፣ ‹‹ግዛታዊ›› ፣ ‹‹ዘውጋዊ›› ፣ ‹‹ይፋዊ›› ፣ ‹‹ልሣናዊ›› ፣ ወዘተ በመባል በተለያዩ ፈርጆች ይመደባል::



# “የኢትዮጵያዊነት አንጂ የኦሮሞ፣የአማራ፣የትግሬ የሚባል ደም የለም”

## “የትኛውም ሕዝብ የሚኖርበትን ክልል ጠፍጥፎ አልሰራውም”

## ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው

*ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በሚሰጧቸው በሳል አስተያየቶችና በሚያቀርቧቸው ጥናታዊ ፅሁፎች በህዝብ ዘንድ በስፋት ይታወቃሉ፡፡ ካለፉት 27 ዓመታት ወዲህ እንደ አዲስ መስተጋባት የጀመረውን “ኢትዮጵያዊነት” በተመለከተ፣ እንዲሁም ወጣቱ ትውልድና ሀገራዊ መስተጋብሮቹን በተመለከተ ሰፋ ያለ ትንታኔ እንዲሰጡን ባነጋገርናቸው መሰረት፤ የኢትዮጵያን የዘመናት ትርክትና የአሁን ችግሮቿን እንዲህ ባለ መልኩ ነግረውናል፡፡ መልካም ቆይታ*

**ግዮን፡- ዋነኛ የመወያያ አጀንዳችን ኢትዮጵያዊነት እንደመሆኑ መጠን እርስዎ ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ይገልፁታል?**

**ረ/ፕ/ር፡ አበባው-** ኢትዮጵያዊነት እንግዲህ አንድ ረዥም ዘመን ታሪክ ያለው፣ በረዥም ዘመን የታሪክ ሂደት ውስጥ ያለፈና የተሳሰረ ሕዝብ የፈጠረው ማንነት ነው። ኢትዮጵያዊነት ማንነት ነው፣ ከሁሉ አስቀድሞ።ያ ማንነት በምንድን ነው የሚገለፀው? ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? ስንል፣ አነሰ ቢባል በአራት ነገሮች ይገለፃል።

**ግዮን፡- በምን በምን?**

**ረ/ፕ/ር አበባው፡-** አንደኛው ታሪክ ነው። ታሪክ የአንድን ሕዝብ ማንነት አጉልቶ የሚያሳይ ትልቅ የጊዜ ሂደት ነው። ታሪክ የኢትዮጵያዊነት አንድ ትልቅ መገለጫ ነው ▶

ካልን በዚህ ውስጥ ሁለት ነገሮችን እናያለን ማለት ነው:: የመጀመሪያው ኢትዮጵያ የሚለውን ሀገረ መንግስትና (ህዝቡን ጨምሮ ማለት ነው) ለረዥም ጊዜ የተገነባ፣ ረዥም ዘመናት የቆየ የመንግስትን ታሪክ ::

በጥቂቱ ወደ ሶስት ሺህ አራት መቶ አመት አካባቢ ያልተቋረጠ መንግስታዊ ታሪክ አለን:: ያ ከየት ነው የሚነሳው? ፑንት ከሚባለውና ለመጀመሪያ ጊዜ ሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት አለ፣ በአንድ ንጉስ የሚተዳደር ተብሎ ከሚነገረው ጊዜ:: የዚህን ምንጭ የምናገኘው ደግሞ ከግብፅ ሄሎግሎፊክስ ጽሑፎች ነው:: ግብፆች በተለያዩ ዘመናት የንግድ መርከቦቻቸውን ወደ ቀይ ባህር ዳርቻ በተለይም የአሁኑ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ይልኩ ነበር::

በንግስት አፄ ብሱት ጊዜ አንድ ኒሃሰም የሚባል የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪና መልኩም እንዲዚሁ ጥቁር የሆነ የንግድ መርከቦችን ይዞ መጥቷል:: ሲመጣ የተገናኘው ከፑንት ንጉስ ጋር ነበር፤ ያ ንጉስ ደግሞ ኬረሩ ይባላል:: ንጉስ ካለ፣ በንጉስ ሥር የሚተዳደር ሕዝብ አለ ማለት ነው:: እንግዲህ ከዛ ጀምሮ ሥርዎ መንግስታት ይቀያየራሉ፣ ገዢዎች ይቀያየራሉ:: ከፑንት ወደ ዳማት፣ ከዳማት ወደ አክሱም፣ ከአክሱም ወደ ዛጉዌ፣ ከዛጉዌ እንደገና ወደ ሰለሞናዊው:: ሰለሞናዊው ደግሞ በውስጡ የመካከለኛው ዘመን ነበር ከዛ፤ የጎንደር ዘመን ነበር፣ በዘመነ መሳፍንትም ቢሆን መንግስት ነበር::

እንዲያው ዝም ብሎ የነገስታቱ የገዢነት ሚና ቀነሰ እንጂ ሲገዙ ግን መንግስት ነበረ:: ከቴዎድሮስ መነሳት ጋር ተያይዞ ደግሞ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ታሪክ እየቀጠለ ረዥም ተጓዘ:: የመንግስት ታሪክ አንድ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው::

***ግዮን፡- ሁለተኛው የኢትዮጵያዊነት መገለጫችንስ ምንድን ነው?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** ወደ እሱ ልመጣ ነው:: ሁለተኛው የህዝቡ ታሪክ ነው፤ የመንግስቱ ሊሰፋም ሊጠብም ይችላል:: እንደ የወቅቱ ማለት ነው:: እየሰፋም እየጠበበም ነው አሁን ዘመን ላይ የደረስነው:: ህዝቡ ግን በዛ ሂደት ላይ በመንግስት ታቀፈም፣ ለማዕከላዊ መንግስት ገበረም አልገበረም፣ የራሱ መስተጋብር ነበረው::

የኢትዮጵያን አካባቢ ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው ካስት ሲስተም የለውም፤ ሁሉም በጋብቻ ይተሳሰራል:: አንዱ ሕዝብ ከአንድ አካባቢ ይንቀሳቀሳል፣ በግለሰብ ደረጃም ይሁን እንዲሁ በገፍ አንድ ላይ ሊሄድ ይቻላል:: በባህል ይዋሃዳል፣ በቋንቋ ይዋሃዳል፣ በደም ይዛመዳል:: ይሄ የረዥም ዘመን የሕዝቡ መስተጋብር እንግዲህ አንድ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው::

በሌላ መልኩ ባህልን ደግሞ ስንወስደው አንደኛውና ትልቁ ነገር ኢትዮጵያውያን የመከባበር ባህል አለን:: አንዱ አንዱን ዝም ብሎ ሄዶ ልውጋህ፣ ልውረርህ አይደለም ባህሉ:: በርግጥ ጦርነቶች ነበሩ፣ እነዛ ጦርነቶች ግን "ገብር፣ አልገብርም" ነው መነሻቸው:: ሕዝቡ ግን በባህሉ የተዋሃደ ነው:: አሁን በትግራይ ሕዝብና በአማራ ሕዝብ ባህል መሀል ምኑን ትለየዋለህ?

የአርጎባው፣ የኦሮሞው ወይም የአማራው ደግሞ የሚወራረሳቸው ባህሎች አሉ:: እነዚህ የባህል ውርርሶች አንድ ላይ ሆነው የኢትዮጵያዊ ባህል እንለዋለን፤ በአለባበሳቸው ደረጃ ፣በአስተራረሳችን ብዙ የምንለያይ አንሆንም:: የቤት ቁሶቻችንን እንውሰድ፤ ሁሉም የኑሮ ሁኔታችን በአርብቶ አደሩና አርሶ በሚኖረው መሀከል የኑሮ ዘይቤ ልዩነት ይኖራል እንጂ፣ ከዛ ውጪ ግን ያለው በአብዛኛው ብትወስደው አኗኗራችን ተመሳሳይ ነው:: የሚያገናኘንም ይሄ ነው::

ከዛ አልፎ ተርፎ የኢትዮጵያ ባህል ምልክት ነው ብለን የምንወስደው የሀበሻ ጥበብ ልብስ አንዱ ብቻ ነው የሚጠቀምበት? ትግሬው ወይም አማራው ብቻ ነው የሚጠቀምበት? ወላይታውም፣ ሌላውም ብሔር የሚጋራው ነው:: ለምሳሌ ከምግብ ብንወስድ አንዳንዴ የቱሪስቶች ፕሮግራምና ምርጫ ላይ የምናያቸው ምግቦች ራሳቸው እኮ ከሞላ ጎደል ሁሉንም የሚወክሉ ስለሆነ ነው:: ባህላችን ራሱ አንድ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው::

***ግዮን፡- ወደ ሶስተኛው የማንነት መገለጫ እንሸጋገር?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** መልካም:: አሁንም "ኢትዮጵያ የኩሩዎች ሀገር የአናብስት ምድር" እየተባለ የሚጠራው ነገር "አትንኩኝ ባይነት" ነው:: ህዝባችን መደፈርን፣ መጠቃትን አይወድም:: በውጭ ወራሪ ብቻ አይደለም፣ መንግስትም ያድርስበት በሌላ መንገድ ኩሩና ጀግና ሕዝብ ነው:: በዛው ልክም የሰውም አይወድም:: ዘልሎ ሄዶ ሳጥቃ፣ ልበዝበዝ፣ ልጨቁን አይልም::

እንደ ድህነቱም ይሁን፣ እንደ አኗኗሩ ይሁን ኮርቶ የራሱን ደህንነት የሚጠብቅ ሕዝብ ነው:: በታሪክ እንኳ ብንወስድ ኢትዮጵያ ራሷን ትከላከላለች ጥቃት ሲደርስበት፣ እንጂ (ኢትዮጵያ ስንል ሕዝብን ነው) ሌላውን ሄዶ አይነካም:: ሶማሌ ተንበዛብዛለችና አሁን ምንም መንግስት ስለሌለ ሄደን እናጥቃ የሚል መሪ የለም:: ህዝቡም እንደዛ ዓይነት ስሜት የለውም:: ለተወሰነ ጊዜ በአክሱማውያን ዘመን ከመርዌን ጋር በንግድ የተነሳ ቁርንቁስ ነበር:: ከዛ ውጭ ሌላውን ነክታ አታውቅም:: ይሄ ትልቅ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው::

አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ኢትዮጵያዊ በባህሉም፣በእምነቱም ለየት ይላል:: ኢትዮጵያ ከአይሁድ እምነት ጀምሮ እስልምናን፣ ክርስትናን እንደገና ደግሞ ማንኛውም ትውፊታዊ ዕምነት፣ እንደ ዋቄ ፈታና ዋቄ ፈናን ጨምሮ ብዙ እምነቶችን ያስተናገደች ሀገር ናት:: አንዱ ተነስቶ አንዱን ሳጥፋ አይልም:: ክርስትና ሲነሳ በግድ ተጠመቅ አይልም፤ "ክርስቲያን ብትሆን ይሻላል" ነው የሚልህ:: እስልምና ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድና በተለያየ መንገድ ተስፋፋ እንጂ በግድ አልነበረም:: የኢማም መሀመድ ዘመን ነች የተለየች፣ ያቺ ደግሞ የፖለቲካ ጦርነት ናት:: የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ጦርነት እስልምናውን በተወሰነ መልኩ አስፋፍቶ ይሆናል፤ ተመልሶ ደግሞ ይጠባል::

ትልቁ ነገር ፈሪሃ እግዚአብሄር ያደረበት ሕዝብ፣ እምነቱን አጥብቆ የሚይዝ ሕዝብ፣ የእኔ እምነት የአንተም ዕምነት መሆን አለበት ብሎ የማይጫን፣ ሁሉን አቻችሎ የሚኖር ነው:: የእውነት ሀገር፣ ባህሉ ጠንካራ፣ ቁሳዊ ባህሉን ከመንፈሳዊ ባህሉ ጋራ አጣምሮ የያዘ ነው:: የግሪክ አማልክት ዘ ኦዲሴይ ላይ እንደምናነበው ዕረፍት ሲፈልጉ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ::የዕውነት ሀገር ስለሆነ ነው አማልክቱ የሚወዱት:: በግብፃውያን እምነት በድሮው ዘንድ፤ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት አካባቢ በእውነት ላይ የተመሰረተ፣ ትልቅ ሕዝብ የሚኖርበት ነው ብለው ይወስዳሉ:: ይሄ በሃይማኖት ፅንቶ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ተላብሶ፣ በእውነትና በሀቅ ላይ የተመሰረተ ባህልና እምነት አንዱ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው:: በእኔ ዕምነት እነዚህ አራት ነገሮች ኢትዮጵያዊነት ሲነሳ በመግለጫነት የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው::

***ግዮን፡- የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሀሳቡስ ምንድን ነው?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሀሳብ ከአራቱ ነጥቦች የሚመዘዝ ነው:: አራቱ አንድ ላይ ተደምረው የፈጠሩት እሴት ነው፣ ባህል ነው:: ዝም ብለን ኢትዮጵያዊነት ስንል ሕገ መንግሥት ስላለ ወደን፣ ፈቅደን... የሚለው ነገር አይደለም:: አራቱ አንድ ላይ ሆነው በሕዝቡ ላይ ያመጡት ማኅበራዊና የምንጋራው ሥነ - ልቦና ነው ኢትዮጵያዊነት:: እንደ ጽንሰ ሀሳብ "ኢፌክቲቪሊ" ልንወስደው አንችልም::

ወደ ደቡብ አፈሪካ ብንሄድ ከአድዋ በኋላ "ኢትዮጵያኒዝም" ብለው እንደ አንድ ትግል ተነስተዋል እኮ:: ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ይሄ እሴት ነው::

***ግዮን፡- ኢትዮጵያዊነት ስሜት ነው ግብር?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** ግብርም፣ ስሜትም ነው:: ግብር ስንል ሀቅ ሲሆን፤ ሰው እንዴት ይበደላል? ለምሳሌ በዚህ በኩል አንድ የእግዜር እንግዳ ያልፋል ይግባ እንጂ ሁሉንም ነገር ያገኛል:: አሁን አሁን ነው እንጂ በፊት እኮ ሐብታሙ ብቻውን ቁጭ ብሎ አይበላም፤ የፈለገ ባላባት፣ ያሻውን ባለፀጋ ይሁን፤ የሚካኤል፣ የማርያም እያለ ግብር ሲያበላ መሰል ጓደኞቹን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነው የሚጠራው:: ይሄ ግብር ነው::

"እከሌ የእከሌን ፍየል ወሰደ፣ በረት ሰበረ" ተብሎ ሲከሰስ "አንተ ጥፋተኛ ነህና ካሰው" የሚለው ይሄኛው መንገድ ራሱ ግብር ነው:: በአንድ በኩል በግብር ኢትዮጵያዊነት በጣም ይገለፃል ማለት ነው::

ስሜት ነው ስንል ደግሞ "እንዲህ እንዲህ የሚባል ጠላት ተነስቶብሃል" ሲባል እንዴ? በሚል ያንቀጠቅጠዋል፣ ይሸንጠዋል:: የማይችል ህመምተኛ ወይም አንካሳ ሆኖ ዘመቻ ቢቀር እንኳን "እንዴት ሳልዘምት ቀረሁ?" ብሎ ይፀፀትዋል:: ይሄ ስሜት ነው:: በህዝቡ ውስጥ ለዘመናት ብዙ ነገሮች ተደምረው ያመጡት ስነ ልቦናዊ ስሜትም ነው በውስጡ የምናገኘው::

***ግዮን፡- አሁን ያለው ትውልድና ኢትዮጵያዊነት ተገናኝተዋል?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** በብዙ መንገድ ይሄ ትውልድ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ብዙም ቁርኝት የለውም:: በአንድ በኩል ስሜቱ አለ፤ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያን ያህል የሚረግመውም አይደለም:: በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ምን ትጠቅማለች? ብሎም ያስባል::

***ግዮን፡- ይሄ ክፍተት እንዴት ተፈጠረ?***

***ሬ/ፕ/ር አበባው፡-*** ድሮ 1950ዎቹ እና 60ዎቹ ላይ፤ ከዛም በፊት የነበረው ወጣት

*ቀሪውን ቃለ ምልልስ በ ገጽ 24 ይመልከቱ*



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# “የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፈርሶ፤ ታየ ዘረኝነት ዳር እስከ ዳር ነግሶ!”

እግዚኦ! …ለወራት ወደ ጠፋሁበት መጠጥ ቤት ድንገት ብቅ ብል የቀድሞ ወዳጆቼ በአንድ ድምፅ እንዲህ ባለ መዝሙር ተቀበሉኝ፡፡ …ክፋቱ እኔን በመዝሙር መቀበላቸው አልነበረም፤ ክፋቱ የምንወደው የአገራችን ብሔራዊ መዝሙር እንዲህ ተጣሞ መቅረቡም አይደለም፤ ክፋቱ፣ ‹‹ስንዘምር የግድ አብረኸን በመቆም መዘመር አለብህ!›› መባሌ እንጂ፡፡

ከመግቢያው ልጀምር፡፡ በቅድሚያ የቤቱን ደንበኛ በሙሉ ሞቅ ያለ ሰላምታ እየሰጠሁ ገባሁ፡፡ ‹‹እንዲህ የጠፋኸው በሰላም ነው?›› ለሚለው የቤቱ ጥያቄ፣ ‹‹በሰላም ነው!›› እያልኩ መልስ እየሰጠኹ (‹ኤጭ! ምን ሰላም አለ?› ብዬ ብሶት ላለማሰማት)፣ ወደ መቀመጫዬ ሳመራ ጮኽ ያለ የአንድ ሰው ጭብጨባ ተሰማ፡፡ …ቤቱ ፀጥ አለ፡፡

‹‹የጠፋው ወንድማችን ሲመጣማ ዝም ብለን አንቀበለውም!›› አለ ያው አጨብጫቢ፡፡

‹‹በምን እንቀበለው!?›› የቤቱ ሰው ጠየቀ፡፡

‹‹በሰሞኑ ብሔራዊ መዝሙር!››

‹‹እሺ!›› ተባብለው፤ ሁሉም ቆሙ፤ እኔም የግድ ‹ቁም› ተባልኩ፡፡ ‹ለአገሩ ብሔራዊ መዝሙር ማን የማይቆም አለ?› ብዬ ትዕዛዛቸውን ተቀብዬ ብቆም፣ መዝሙሩ ‹የተቀሸበ› ሆኖ ተገኘ፡፡

‹‹የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፈርሶ፤
ታየ ዘረኝነት ዳር እስከ ዳር ነግሶ!››

…ተበሳጨሁ፤ የራሳቸው አጀንዳ ማስፈፀሚያ ስላደረጉኝ በጣም ተበሳጨሁ፡፡ ለነገሩ መጀመሪያውኑ ነበር፣ ይኼ ሁሉ አምታች፣ ‹‹ስንደመር ያምርብናል!›› ሲለኝ መጠርጠር የነበረብኝ፡፡

ወይ ጉድ! ይኼ ቢራ ምን ሆኖ ነው ዛሬ መልዕክት የሌለው!? ለነገሩ ዘንድሮ ከቢራው ይልቅ ማስታወቂያው ነው የሚያሰክረው፡፡ (ነይ እስኪ አንቺ አንድ ማስታወቂያ ድገሚኝ!? ይቅርታ አንድ ቢራ ድገሚኝ!) …እሰይ! የማይቀረው ሞቅታ መጣ፡፡ ያውም ብዙ ገንዘብ ‹ኢንቨስት› የተደረገበት ሞቅታ፡፡

‹‹ሴት እናት ናት፤ ሴት እህት ናት፤ ሴት ሚስት ናት፤ ሴት አገር ናት፤ ሴት መንግሥት ናት!›› አልኩ ጮኽ ብዬ፡፡

‹‹የገ/እግዚአብሔር ልጅ!›› አለ አንዱ ከወደ ጥግ ድምፁን ዘለግ አድርጎ፡፡

‹‹አቤት!››

‹‹መቼም የሥልጣን ነገር አይሆንላችሁም፤ በብሔር ቢያቅታችሁ ፆታ ልትቀይሩ ነው!?››

በለው! …ቤቱ በሳቅ አውካካ፡፡ አልተበሳጨሁም፡፡ ይኼ ዓይነቱን ቧልት ለምጄዋለሁ፡፡ ይልቅስ ተረቡ ከወዳጄ ከአበበ ቶላ ጋር ያደረግኩትን ጨዋታ አስታወሰኝ፡፡

የዛሬ ሦስት ወር ገደማት ነው፡፡ አበበ ቶላ (አቤ ቶኪቻው) እኔ ጋር ደወለና፣ ‹‹ምን አዲስ ነገር አለ?›› አለኝ፡፡ አገሬ ውስጥ የተከናወነ፣ ነገር ግን ውጪ አገር ለሚኖር ሰው ጆሮ የሚበቃ ነገር ስፈልግ፣ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡

‹‹ሄሎ አቤ!››

‹‹ሄሎ!››

‹‹አንድ ጭምጭምታ ግን አለ!›› አልኩት፡፡

‹‹ምን ዓይነት?›› አለ አቤ ሰፍ ብሎ፡፡

‹‹ከቀበሌ መታወቂያችን ላይ ብሔር ሊነሳ ነው!››

‹‹ይኼማ አሪፍ ዜና ነው!›› አለ አቤ በጣም ተደስቶ፡፡

‹‹ምን ዋጋ አለው አቤ፣ ብሔር ከመታወቂያ ላይ ቢነሳ!›› አልኩት በቀዘቀዘ ስሜት፡፡

‹‹እንዴት?›› አለ አቤ ግራ ተጋብቶ፡፡

‹‹ለእኔ እና ለአንተ የአባት ስም አብሮ ቢነሳ እንጂ ብሔር ብቻውን ቢነሳ ምን ዋጋ አለው!?››

አቤ ስቆ ስልኩን ዘግት፡፡ ይኼን ጨዋታ አቤ ፌስቡኩ ፔጁ ላይ ጽፎታል አሉ፡፡ …ይመቸው፡፡ (እኛ ፌስቡክ የሚሉትን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ከተውን ስድስት ወር አለፈን፡፡ ተመስገን፤ ያስቻለን አምላክ!)

‹‹በብሔር ቢያቅታችሁ ፆታ ልትቀይሩ ነው!?›› ይበለኝ ይኼ አጨብጫቢ!? (ይኼ ስሜ ግን እስከ መቼ ነው ሲያሰድበኝ የሚኖረው?)

…መቼም አንዳንድ ሞቅታ ጥሩ ነው፤ የምትናገረውን እንጂ የሚናገሩህን አትሰማም፡፡ እኔም ቀስ በቀስ ለተረቡ ጆሮባዬን ሰጥቼ ወደ ዋናው ነጥቤ ገባሁ፤

‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ መለያ ብሔራችን፣ በእናታችን ብሔር ካልተጠራ፣ ለሴቶች የተሰጠው ይኼ ሁሉ ሹመት ከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው! …አሁንም እደግመዋለሁ…››

‹‹አትድገመው!›› የሚል የቁጣ ድምፅ አቋረጠኝ፡፡

‹‹ለምን?›› አልኩ ቁጣው ወደመጣበት እየዞርኩ፡፡ …ተናጋሪው አርቲስት ቢያጡ ነው፡፡ አርቲስት ቢያጡን እዚህ ደግሞ ምን እግር ጣለው? …ግራ ተጋባሁ፡፡

‹‹በአባትህ አገሪቱን ደህና አድርገህ ገሽልጠሃታል፤ አሁን ደግሞ በእናትህ ልትደግመን ነው!?››

‹‹ምን?›› ጆሮዬን ተጠራጠርኩት፤ እውነት አሁን እየሰደበኝ ያለው፤ በንቀት እያየኝ የሚናገረው አርቲስት ቢያጡ ነው? …ግራ ተጋባሁ፡፡

‹‹የትራንስፎርሜሽኑ እቅድ፤
አምሮ ተፈፀመ በቁርጠኛው ኢሕአዴግ!››

…ብሎ የዘፈነው አርቲስት ቢያጡ ዛሬ እኔን ተቺ ሆነ!? ጉድ በል አንኮበር! ቆይ… ቆይ… ቆይ! ምን ነበር ያለኝ? ‹‹በአባትህ አገሪቱን ደህና አድርገህ ገሽልጠሃታል፤ አሁን ደግሞ በእናትህ ልትደግመን ነው!?›› …በለው!

‹‹አባይ፣ አንተ አባይ፣
በመገደብህ፤
ምን አለ ሆድህ!?››
ብሎ በዘፈነው ሙዚቃው ላይ፣
‹‹ቁርስ እና ምሳ፣ እራት ብቻ ለምን?
በታላቁ መሪ፣ በመለስ ዜናዊ፣
…መቅሰስ እንደግማለን፡፡››

ብሎ አሸሼ ገዳሜ ሲል የነበረ ሰው ነው እንግዲህ ራሱን ዋናው የለውጡ አካል አድርጎ እኔ ላይ መዘባበት የጀመረው፡፡ ‹‹ተገርሜ!›› አለ ዘፋኙ፡፡

አርቲስት ቢያጡ በአንዱ የቴሌቪዥርን ጣቢያ ቃለ መጠይቅ ሲደረግለት፣ ‹‹ሃያ ሰባት ዓመት እንዲህ ባለ ጭካኔ፣ እንዲህ ባለ ውንብድና ውስጥ መቆየታችን የዚህን ሕዝብ ቻይነት ያሳያል፡፡ ይኸው ዛሬ ያ የግፍ ቀንበር ከላያችን ላይ ተገፎ የምንፈልገው ለውጥ መጥቶ ያለ አፈና በነፃነት ለመናገር በቅተናል፡፡›› ማለቱን ሰምቼ መገረሜን ሳላበቃ፣ እኔኑ መስደብ ያዘ!? …ማመን አቃተኝ፡፡

‹‹ለመሆኑ እንዲያ የዘፈንክለት ቁርስ፣ ምሳ እና እራት የት አለ?›› ብሎ ማፋጠጥ ነበር፡፡

‹‹እነ ‹በአዲስ መልክ ሥራ ጀመረናል› ምን እያልከኝ ነው!?›› አልኩት የተናገረኝ ነገር ውስጤ እየተገላበጠ ቢያስቸግረኝ፡፡

ዝም፤ መልስ የለውም፡፡

እኔ የምለው ግን ድምጻዊ ዘሪቱ ከበደ፣ ‹‹አዝማሪ ነኝ ከያኒ›› በሚለው የሙዚቃ ሥራዋ፣ ‹‹ለተገፉ ሰዎች ድምፅ›› ብላ ያሞካሸችው የዚህ ዓይነቱን አርቲስት ነው ማለት ነው!? …(‹‹አዎ! ብላችሁ ባላሳቃችሁኝ፡፡)

በነገራችን ላይ አርቲስት ቢያጡ ሰሞኑን አንድ አዲስ ልማታዊ ነጠላ ዜማ አውጥቷል፡፡ እንዲህ የሚል፤

‹‹አገሬ አገሬ፤
ሃያ ሰባት አመት ያጠነሽ በርበሬ፤
ዛሬ በዐቢያችን፣
ዛሬ በለማችን ተወገደ ዛሬ!››

…ሰምታችሁት ይሆን?

‹‹ጠቅላይ ሚንስትሩ ራሳቸው በሌባ ተከብበው እኛን ከሌባ ራቁ ይሉናል!›› ያለው ማን ነበር!?

# ሰላም የራቀው . . .

ከገጽ 6 የዞረ

በሚፈልገው ቋንቋ የሚያናግረው ሲመጣ ያለጥያቄ ለድርድር መቀመጡ ዕድል ጠባቂ ወይም opportunist መሆኑን እንዳያጋልጥ የሚሰጉ ብዙዎች ናቸው።

እንዲህም ሆኖ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ወንጀል እና ብጥብጥ እንጂ ሰላም በሚፈለገው መልኩ ሰፍኗል ማለት ይቸግራል፤

## ሰላም፣ የተሰቀለ ዳቦ?

በዚህ ለውጥ ሰላም ምን ያህል እየራቀች በምትኩ ግጭት የእለት ከእለት ዜና መሆኑን መታዘብ ቀላል ነው። የመገናኛ ብዙሃን የፊት ገጽ እና ቀዳሚ ርዕሰ ዜና ግጭት ብቻ እየሆነ መጥቷል። በኢትዮጵያ ስለኢኮኖሚም ሆነ ማኅበራዊ ጉዳዮች ከሚወራበት ጊዜ ይልቅ ግጭትን በተመለከተ የሚነገሩ ወሬዎች አየሩን ተቆጣጥረውታል። አንዳንዴም እዚህ ሃገር ላይ ከፖለቲካ እና ፖለቲካ ተኮር አተካራዎች ባሻገር ሌላ የሕይወት እንቅስቃሴ የሌለ እስኪመስል ድረስ መድረኩን የተቆጣጠረው የግጭት ዜና ብቻ ነው።

ባለፉት ወራት በኢትዮጵያ እዚህም እዚያም በሚከሰቱ ግጭቶች አደጋዎች እና ሁከቶች ፣የሰዎች ሕይወት መጥፋቱ ንብረት መውደሙ እና የሰዎች መፈናቀሉ ቀጥሏል። ኢትዮጵያ እንደዚህ ዘመን አንድነቷ ጥያቄ ውስጥ የገባበት፣ እንደዚህ ዘመን ህዝቧ የተራኮተበት እና እንደዚህ ዘመን ሰላምና ጸጥታዋ የታወከበት ጊዜ የለም። በአራቱም አቅጣጫዎች የሰላም መደፍረስ እና አለመረጋጋት ያልነካካው ሰፍራ የለም። በደቡብ የሲዳማ ፣ ወላይታ እና ጉራጌ አካባቢ ግጭቶች፣ በሰሜን የጎንደር የአማራና ቅማንት ግጭቶች፣ በምስራቅ የሶማሌ እና ኦሮሚያ ድንበር አካባቢ ግጭቶች፣ የቤኒሻንጉል እና ኦሮሚያ ድንበር አካባቢ ግጭቶች፣ በምዕራብ የጉጂ እና ወለጋ አካባቢ ግጭቶች ፣ እነዚህ ሁሉ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ለብዙኃን ህልፈት፣ ለንብረት ውድመት እና ለከፍተኛ ሕዝብ መፈናቀል ምክንያት የሆኑ ግጭቶች ናቸው።

## ለውጥ እና ሰላም

ለውጥ በባህሪው የሁሉንም ወገን ተቀባይነት ማግኘት የሚችል ሂደት አይደለም። በለውጥ አብዛኛው ቢጠቀም ጥቂቱ ግን ጥቅም የቀረበት ነው። ብዙው ቢያመሰግነው ጥቂቱ ደግሞ የሚያኮስሰው ሂደት ነው። የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር ከላይ እንዳልነው ሁሉንም ሊባል በሚችል መልኩ ሕዝቡን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ ያደረጉ ለውጦችን ቢተገብርም በዚያው መጠን የረካ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ቅሬታ የገባው ማኅበረሰብም የተፈጠረ መስሏል። በአንድ የኢህአዴግ አገዛዝ ወቅት በተለየ ተጠቃሚነት ስር የነበረ ማህበረሰብ በአሁኑ የማግለል ፖለቲካ ሰለባ ሆኛለሁ ቢል የሚገርም አይሆንም። ምክንያቱም ለውጥ በባህሪው ሁሉንም በእኩል የሚያስደስት ሂደት አይሆንምና።

ያም ሆኖ ለውጥ ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ በሚችልበት መንገድ መጓዝ ካልቻለ አካታች አይደለም የሚል ሃሳብ ያላቸው ሰዎች በአካታች ፖለቲካ እና በስልጣን ክፍፍል መካከል የሚከሰቱ መወዛገቦች ናቸው ለውጡ በዘላቂ ሰላም እንዳይታሽ የሚያደርጉት የሚል ሃሳብ ይሰነዝራሉ።

> **የዚህች ሃገር ሰላም በእጇ ባለው እርቅ እና ሰላም ማምጫ መንገድ አንጂ በማናቸውም አካላት ጣልቃ ገብነት የሚረጋገጥ አይደለም**

## ሰላምን በእርቅ ማምጣት

በኢትዮጵያ እርቅ የሚያስፈልጋቸው የግጭት አይነቶች ብዙ ናቸው ። እርቅ ፍላጎትን እና እውቅና መስጠትን ይጠይቃል። ተበዳይ ባለበት ሃገር ሁሌም በዳይ ራሱን አውጥቶ ለበደሉ ይቅርታ መጠየቅ ግድ ይለዋል፤ ለዚህም ነው የሰላምና የእርቅ ኮሚሽን የተቋቋመው።

ያ ከመሆኑ በፊት ግን አሁን ለውጡን ተከትለው በመጡ የሰላም መደፍረስ ችግሮች በተለይም ብሄር ተኮር መቆራቆሶች ላይ የእርቅ ፕሮግራሞች ተካሂደዋል። እንደምሳሌም በቅርቡ የአማራ እና ቅማንት ማህበረሰቦች የሰላምና የእርቅ ጉባኤ ተካሂዷል። በአማራ ክልል ጎንደር ውስጥ የቅማንት ማህበረሰብ አማራ አይደለሁም በሚል ማንነት ጥያቄ ማንሳቱና ጥቂቶችም ይህንን መነሻ አድርገው አማራ ከቅማንት ይውጣ ብለው የአማራ ተወላጆችን ሆቴል መሰባበራቸው ከዚያም አልፎ ለከፋ ግጭት እና ደም መፋሰስ መዳረሳቸው አስገራሚ ክስተት ሆኖ ነበር፤ በተለየም በሕወሓት እና ደጋፊዎቻቸው የተቆሰቆሰ እና ያደገ ነው በተባለው በዚህ ግጭት አትራፊ ሳይኖር ሁለት አማሮች በብሄር ንቆራ መጋደላቸው አቶ ገዱ አንዳርጋቸው እንዳሉት "ዓላማ ቢስ" መገዳደል ነው።

ከዚህ ግጭት የሚያተርፍ አካል ግጭቱን ለመጠቀሚያነት የሚያውል ብቻ ነው በማለትም በሁለቱ ማህበረሰብ መካከል እርቅ ተካሂዶ ነበር። ይኸው ህዝባዊ የሰላምና የእርቅ ጉባኤ በአማራ እና ቅማንት ማህበረሰቦች መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት መፍትሄ ለመስጠት የተከናወነ ሲሆን የተካሄደውም በጎንደር ከተማ ነበር።

የጉባኤው ዓላማ በክልሉ በተለይ በማዕከላዊና ሰሜን ጎንደር ዞኖች የተከሰቱ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለዘለቄታው መፍታት ነው ተብሏል በጊዜው። በእርቅ ጉባዔው ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በመድረኩ ባደረጉት ንግግር የሁለቱም ማህበረሰብ ሕዝብ ተዋልዶ አብሮ የኖረ መሆኑን ገልጸው ለታላቅ ሃገር እና ተስፋ ለሰነቀ ሕዝብ ይህ ግጭት አይመጥንም ነበር ያሉት። ያም ሆኖ ግን የሁለቱ ህዝቦች መገዳደል በከፋ ሁኔታ ቀጥሎ ለገላጋይ ግራ አጋብቷል።

እንዲህ የመሳሰሉ እርቆች በየቦታው ተካሂደዋል። የቡራዩ ግጭት ላይ የጋሞ አባቶች ሰላም ካወረዱ በኋላ ከኦሮሞ አባ ገዳዎች ጋር በጋራ ሆነው የሁለቱን ሕዝቦች ተወካዮች ሰብስበው አስታርቀዋል። በኦሮሚያ ምዕራብ ወለጋ የኦነግን ተዋጊ ኃይል ወደ ሰላሙ ማእቀፍ ማስገባት የቻሉት አባገዳዎች እንዲሁ ከመንግስት እና ካአካባቢው ሕዝብ ጋር አስታርቀዋል። በሃገር አቀፍ ደረጃ የእርቅ ፕሮግራም እየተዘጋጀ ብዙ ተጥሯል።

በቅርቡ በሂልተን ሆቴል በአማራ እና ትግራይ ክልሎች መካከልም የተካሄደው የሰላም ድርድርም የዚሁ እርቅ አካል ነው። ትልቁ ጥያቄ ከሰላም ስምምነት እና እርቅ በኋላ በኢትዮጵያ ጸብ እና ግጭት የሚያገረሽበት ምክንያት ምንድነው የሚለው ነው።

ለዚህ የሰላም ጽንሰ ሃሳብ ተንታኞች እርቅ ብቻውን ሰላም እንደማያመጣ ይናገራሉ፤ በተለይም በሂደት ላይ በሚገኝ ፖለቲካ የሚደረስ ስምንነት ከሁኔታዎች መቀያየር አንጻር የመተው ወይም የመጣስ እድል ይገጥመዋል፤ ይህም ለሰላም መደፍረስ እና ለእርቅ መዘንጋት ምክንያት ይሆናል።

## ሰላም መቼ ይመጣል?

በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ የብዙኃኑ ነው። አሁን ባለው አያያዝ የኢትዮጵያ የጸጥታ ሁኔታ አስፈሪ መልክ እያያዘ መጥቷል የሚሉ ወገኖች መሬት ባለው እውነት ሰላም ሳይሆን ቂም መወጫ ቀንን መጠበቅ በብዙዎች ዘንድ የሚስተዋል ይመስላል በማለት ግምታቸውን ያስቀምጣሉ። ለዘለቂ ሰላም አለመኖር የለውጡ አዲስነት እንዲሁም አያያዝን አለማወቅ በምክንያትነት ሲጠቀስ ብዙዎች በሃይለኛ ተስፋ የተወሰኑ አካላት ደግሞ በጥርጣሬ የሚያስተውሉት ሰላም በምኞት ብቻ እንደማይመጣም ምሁራኑ ይናገራሉ ። ለዚህ ደግሞ ከየትኛውም ሳይንሳዊ የሰላም ማምጫ ትንታኔዎች በላይ ሃገሪቱ ያላት የግጭት አፈታት እና እርቅ መንገድ የበለጠ መድኃኒት ነው። የሰላም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል እንዳሉት ሰላምን ለማምጣት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትም ይሁን ትልቁ ኃላፊነት ያለባቸው የሃይማኖት አባቶች እና የሃገር ሽመግሌዎች ናቸው። ይህን ማክበር የሚችል እና በዚሁ መስመር ተጉዞ የሃገሩን ሰላም መጠበቅ የሚችል ትውልድ ያጣነው ያለፈው ዘመን ለእርቅ የነበረው የስላቅ አተያይ ትውልዱ ከግጭት ባለፈ ብዙ ሳያይ እንዲያድግ ስላደረገው ነው። ያም ሆነ ይህ የዚህች ሃገር ሰላም በእጇ ባለው እርቅ እና ሰላም ማምጫ መንገድ አንጂ በማናቸውም አካላት ጣልቃ ገብነት የሚረጋገጥ አይደለም። በፖለቲካ ፓርቲዎች በኩል ቅንጅት ፈጥሮ ለሰላም መታገል እና የፖለቲካ ስራውን ለጊዜው ገታ አድርጎ ሁሉን አቀፍ ሰላም አንደሚመጣ ንቅናቄ ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው መፈትሄም ነው። ቀኑ ባይታወቅም ተባብረው ለጠሩት እለት ሰላም ጓዙን ጠቅልሎ መምጣቱ አይቀሬ ነው። ከግጭት የሚያተርፉ በግጭት ውስጥ ለመኖር በራሳቸው ላይ የፈረዱ አካላት ብቻ ናቸውና።

# አንደበት

## ለዛ



"እኔ እንደምገምተው አዲሱ አመራር ኢትዮጵያ በቻይና ላይ የነበራትን ጥገኝነት መቀነስ ፈልጓል:: የምዕራቡ ዓለም በኢትዮጵያ ጅምር ለውጦች ዙሪያ ከፍተኛ ፍላጎት አድሮበታል:: የዓለም ባንክን ጨምሮ በርካታ የአውሮፓ መንግሥታት የፋይናንስ ድጋፍ ለመስጠት ቃል እየገቡ ነው::"


**አቶ ጌድዮን ገሞራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ተመራማሪ**
**ሪፖርተር ጋዜጣ ጥር 5 ቀን 2011**



"በትግራይ ለተፈፀሙ ወንጀሎች በሙሉ ሕወሓት ኃላፊነቱን ይወስዳል፤ ብአዴን ለአማራ ክልል ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት:: እኛኮ ትግራይ ላይ እስካሁን የፖለቲካ እስረኞች አሉን:: ያለ አግባብ በግፍ የታሰሩ፣ አካላቸው የጎደሉ ሰዎች አሉን:: ጥያቄው ሀገር አቀፍ ነው፤ ስለዚህ መፍትሔውም በግንባር አቀፍ ደረጃ ነው መሆን ያለበት::"

**አቶ ገብሩ አስራት**
**አዲስ አድማስ ጥር 4 ቀን 2011 ዓ.ም**

"በእኔ አመለካከት፣ ከኢሕአዴግ አመራሮች የኦሮሞም፣ የአማራም፣ የደቡብም "ከደሙ ነጻ ነኝ" የሚል አንድም የለም:: ሁሉም ተነክረውበታል:: አንዱን ከአንዱ ማበላለጥ የሚለው ነገር ጨርሶ አይዋጥልኝም:: ስለዚህ እንደ ጲላጦስ እጅን ታጥቦ "እነ እከሌ ነጻ ናችሁ፣ እነ እከሌ ወንጀለኛ ናችሁ" የሚለው ነገር አያስኬድም:: ሕዝብ ያውቃቸዋል::"



**ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ**
**ኢትዮጲስ ጋዜጣ ጥር 5 ቀን 2011 ዓ.ም**

"የእኛ ሕገ መንግሥት እና ሌሎች ሕጎች ከአሜሪካ እና ከአውሮፓውያን የተቀዱ ናቸው:: ይሁንና ታሪካችንም ሆነ ባህላችን የሚያሳየን ሥልጣን በኃይል ሲያዝ ነው:: የኢትዮጵያ ታሪክ የልጊቃን ጨዋታ ነው:: ዴሞክራሲን ከየትም ልናመጣ አንችልም፣ አልተማርንም፤ መንግሥትንም የምንቆጣጠርበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም"




**አቶ ሙልጌታ አረጋዊ**
**አዲስ ማለዳ ጋዜጣ ጥር 4 ቀን 2011 ዓ.ም**



"እንዳልኩህ እኛ የሙያ ሰዎች ነን ፣የፓለቲካ ሰው እውነት ነው፣ሰበብ ይኖረዋል ወይ ደግሞ የሆነ ነገር ከእሱ አገኛለሁ ትላለህ::ስለተማሪ ሽሮ እና ጤንነት እንጂ ስለፓለቲካ የማይመለከተኝ ሰው ነኝ::እንዳልኩህ ስለ ተማሪው ደህንነት እንዲሁም ስል ትምህርት ጥራት ቀኑን ሙሉ የሚያወራ እና እሱንም ማድረስ የማይችልን ሰው እንዲህ ማድረግ እኮ አይገባም:: "

**ዶ/ር ደላሳ ቡልቻ በኦነግ ታጣቂዎች ታፍነው የነበሩት የደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት**



"ምርጫው መራዘም የለበትም በሚል ከሚያነሱት ወገኖች አንዱ የሚቀርበው ምርጫው ከተራዘመ ለአምባገነንነት መንገድ ይከፍታል የሚል ጥርጣሬ ነው:: እኔ እስካስተዋልኩት ድረስ የለውጥ ኃይሉ አምባገነናዊ ስሜትና አዝማሚያ የለውም:: ይልቁንም እጅግ አደገኛ በሆነና ለውጡ እውን እንዳይሆን፣ ተስፋዎቹ እንዲመክኑ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉ አካላትን በተቃራኒው አይተናል::"

**ፕ/ር አቻምየለህ ደባላ**
**ጉለሌ ፖስት መጽሔት ጥር 2011 ዓ.ም**

## ጠቅላላ እውቀት

- ኪዊ የኒዊዚላንድ ብሔራዊ አርማ ናት:: ይህች ወፍ ጭራ የላትም:: መብረር አትችልም:: አርቃ ማየትም አትችልም:: ከአንድ ሥፍራ እምብዛም አትንቀሳቀስም:: በዓመት የምትጥለው አንዲት እንቁላል ብቻ ነው:: እንዲህም ሆኖ ግን ዝርያዋ ሳይጠፋ ከ70 ሚልየን ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ ኖራለች:: ግዙፉ እና ኃይለኛው ዳይኖዘር ከዛሬ 60 ሚልየን ዓመት በፊት ከምደረ ገጽ ሲጠፋ ምስኪኗ ኪዊ ግን እስከ ዛሬ ድረስ ሕያው ሆና መቆየቷ ያስገርማል::
- ከእንስሳቶች ሁሉ እጅግ በጣም ቂመኛ የምትባለው ግመል ናት:: ግመል አንድ እንስሳ ወይም ሰው ቢተናኮላት ለሰባት ዓመት ያህል ቂም ትይዛለች:: በዚህ መሐል በዳያዋን ካገኘች ከመበቀል ወደ ኋላ አትልም::
- አያድርስ እንጂ የኒውክሌር ቦምብ ፍንዳታ ቢከሰት ጨረሩን ተቋቁሞ በአካባቢው መትረፍ የሚችል ብቸኛ ፍጡር በረሮ ነው::
- ታይላንድ በተባለችው አገር ውስጥ የሚወለዱት ድመቶች በሙሉ ነጭ ናቸው::

| ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ /1887-1974/ | | |
|---|---|---|
| የወንድ ልጅ ኩራት ስለ ሃገር መሞት | ሥነ-ግጥም | 1927 ዓ.ም |
| ግራ መንግሥት በኢትዮጵያ | | 1937 ዓ.ም |
| ክብረ-ነገሥት | ሥነ-ግጥም | 1938 ዓ.ም |
| ብልጽግና በግብርና | | 1941 ዓ.ም |
| ከሥራ በኋላ ስትፈቱ እንቆቅልሽ ተጫወቱ | ኢ-ልብወለድ | 1943 ዓ.ም |
| የዓለም ጠባይ ኃሜትና ብካይ | » | 1948 ዓ.ም |
| ሥነ - ምግባር | | 1943 ዓ.ም |
| የባልና ሚስት ጭውውት በእንካ ሰላምታ | | 1949 ዓ.ም |
| አምስት መንገደኞች | | 1954 ዓ.ም |
| አትስረቅ | | 1957 ዓ.ም |
| ታሪክ አይሙት እንዲያጫውት | | 1957 ዓ.ም |
| የእስማኤል ቁጥቁጦ | | 1959 ዓ.ም |
| አግአዚ | ልብወለድ | 1961 ዓ.ም |

### የስኬታማነት መርሆዎች ዴኒዜል ዋሽንግተን

1. ሕልሞችህ ዓላማ ይኑራቸው
2. ምኞቶችህ ልዩነትን የሚፈጥሩ ይሁኑ
3. ለደካማ አስተያየቶች ቦታ አትስጥ
4. ከዓላማዎችህ ላይ ዓይንህን አትንቀል
5. ህልሞችህን ሕይወት ዝራባቸው
6. ስጦታዎችህን አካፍል
7. ጠንክረህ ሥራህን ሥራ
8. ወደፊት ብቻ ተመልከት
9. ጠቃሚ ነገሮችን ለመውሰድ ሞክር
10. የምትናገራቸው ታላላቅ ታሪኮች ይኑሩህ

## ለፈገግታ

### በጭራሽ አያጨስም

ሁለት ተሳፋሪዎች ባስ ውስጥ ተቀምጠው ስለ ልጆቻቸው እያወሩ
አንደኛው አባት፡- በጣም ጥሩ የሆነ ልጅ አለኝ!!
ሁለተኛው አባት፡- ያጨሳል?
አንደኛው አባት፡- ኧረ በጭራሽ አያጨስም::
ሁለተኛው አባት፡- መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ አምሽቶ ይገባል?
አንደኛው አባት፡- ኧረ አይጠጣም አያመሽም::
ሁለተኛው አባት፡- በእውነት የተባረከ ልጅ አለህ ልትኮራበት ይገባል:: የኔ ልጅ አሁን የጠየኩህን ሁሉ ያደርጋል:: ለመሆኑ ዕድሜው ስንት ነው?
አንደኛው አባት፡- 1 አመት ከ6 ወር

### ከአፌ ልተፋህ ነው

ምን ዐይነት ጨለማ ነው
ልባችንን የከበበው?
ምን ዐይነት ድንዛዜ ነው
ሕይወታችንን የወረረው?
ምን ዐይነት ድንዳኔ ነው
መንፈሳችን ላይ የሰለጠነው?
ምን ዐይነት ተራራ ነው
ለዘመናት የጋገርነው?
እንዴት ዐይነት ልብ ነው፣
ማንስ ተብሎ ይጠራ?
መኖር የማይደፍር!
መሞት የሚፈራ!

*አርነት የወጡ ሃሳቦች በዳዊት*
*ፀጋዬ 2002 ዓ.ም*



# ኦነግ የማን ነው?

## “የኦሮሞ ብሔርና ኦነግ ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው”

## “ኦነግ መሰንጠቅ ከጀመረ እረጅም ጊዜው ነው”

## አቶ ሌንጮ ለታ

*ከአርባ ዓመት በፊት የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን (ኦነግ) የምስረታ ሂደት ዕውን ካደረጉት አራት የኮሚቴ አባላት መሀል አንዱ ናቸው። አቶ ሌንጮ ለታ የግንባሩ ሊ/መንበር በመሆንም ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል።*

*ባለፉት ሀያና ሰላሳ ዓመታት ኦነግ ሲነሳ አብሮ ስማቸው የሚጠራው አቶ ሌንጮ ለታ “ኦነግ በያዘው የትግል መንገድ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፤ አዲስ ስልት መንደፍ አለበት” የሚል አቋም በመያዛቸው ከድርጅቱ አባላትና አመራር ጋር ውዝግብ ውስጥ እንዲገቡና ዘግየት ብሎም እንዲባረሩ አድርጓቸዋል።*

*ከጥቂት ዓመታት በፊት ከኦነግ የተለየ አቋም የያዘ (ኦዴግ) የተሰኘ አዲስ ድርጅት የመሰረቱት አቶ ሌንጮ ለታ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረውን ለውጥ ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት ከገቡ ወራት ተቆጥረዋል። አሁን ባለው የኦሮሚያ ፀጥታ ጉዳይና በአጠቃላይ የፖለቲካ ታሪካቸው ዙሪያ የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ አነጋግረቸዋል። መልካም ቆይታ*

**ግዮን፡- ለመነሻ ያህል የትውልድ ሥፍራዎንና የልጅነት ህይወትዎን ይንገሩን?**

**ሌንጮ፡-** ወለጋ ነው የተወለድኩት፤ ደምቢዶሎ ከተማ:: አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ የተማርኩት ሚሲዮን ውስጥ ነው:: ከዛ በኋላ ወደ አሜሪካን ሀገር ሄጄ ነው የመጀመሪያ ዲግሪዬን የሰራሁት::

**ግዮን፡- ወደ ፖለቲካው ዓለም በመግባት፣ ትግል የጀመሩት መቼና እንዴት ነበር?**

**ሌንጮ፡-** የመጀመሪያ ዲግሪዬን አሜሪካ እንደሰራሁ ነው ወደ ሀገሬ የተመለስኩት:: በተማሪዎች ንቅናቄም ሆነ በሜጫና ቱለማ እንቅስቃሴ ውስጥ ባልኖርም፣ የሁለቱን እንቅስቃሴ ግን ውጭ እያለሁ በንቃት እከታተል ነበር::

ሀገር ቤት እንደተመለስኩ የነበረው የአፄ ኃይለ ስላሴ መንግስት ሥርዓት በጣም የሚያናድድ ነበር፤ ምን ያህል ኢትዮጵያ ኋላቀር እንደሆነች የተገነዘብኩት በተለይ ለትምህርት ወደ ውጭ ከወጣሁ በኋላ ነው:: እንዴት ይሄን ያህል ወደ ኋላ እንቀራለን? የሚል ንዴትና ቁጭት ነበረኝ:: የነበረው አስተዳደር “ሽማግሌና ያረጀ” ስለሆነ ነው ዕድገት እንዳይመጣ ያደረገው የሚል ዕምነት እንጂ፣ ከእሱ የባሰ መንግስት ይመጣል ብለን አልጠበቅንም ነበር:: በዛ መንገድ እንቅስቃሴ ጀምረን ነው ቀስ በቀስ ኦነግን የመሰረትነው::

**ግዮን፡- ኦነግን ከመሰረቱት መሀል የመጀመሪያው ሰው እርስዎ ኖት ይባላል፣ ኦነግን መቼናስንት ሆናችሁ ነው ያቋቋማችሁት?**

**ሌንጮ፡-** በደንብ አላስታውሰውም ቁጥሩን፤ ግን ያኔ ኦነግን የመሰረትነው ሰዎች ከ20 በላይ ነን:: የምስረታውን ሁኔታ ይመራ የነበረው ኮሚቴ ግን ሶስት አራት ሰዎች ነበርን::

**ግዮን፡- ማን ማን ነበራችሁ?**

**ሌንጮ፡-** ዲማ ነገዎ አሁን ያለው፣ ባሮ ቱምሳ (አምባሳደሩ)፣ ኑሩ አብዶና እኔ ነበርን፤ ኮሚቴ ሆነን የኦነግን ምስረታ የመራነውና በዋነኝነት ድርጅቱን ያቋቋምነው::

**ግዮን፡- ድርጅታችሁን ኦነግ ብላችሁ የሰየማችሁበት ዋነኛ ምክንያት ምን ነበር?**

**ሌንጮ፡-** Oromo liberation front በሚል እንግሊዘኛ ስያሜ ነበር በዛን ጊዜ የምንጠቀመው:: በኦሮሞ ህዝብ መቆርቆር ላይ የተመሰረተ ድርጅት ነው:: የኦሮሞ ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን ማስቻል ነበር ዕቅዱ:: ▶

**ግዮን፡- ያን ጊዜ በህቡዕ ነበር የተደራጃችሁት? ወይስ በወቅቱ ፓርቲ መመስረት ይቻል ነበር?**

**ሌንጮ፡-** በይፋ ፓርቲ መመስረት አይቻልም፤ እንቅስቃሴያችን ሁሉ በምስጢር ነበር:: በህቡዕ ተደራጅተን እየተንቀሳቀስን ብዙም ሳንቆይ ሜዳ መሄድ (ጫካ መውጣት) ግዴታ ሆነ::

**ግዮን፡- ወደ ትጥቅ ትግል የገባችሁት በስንት ዓመተ ምህረት ነበር? ትክክለኛ አማራጩስ እርሱ ነበር? ሌሎች መንገዶችስ አልተሞከሩም?**

**ሌንጮ፡-** አማራጮች አልነበሩንም:: እኛ ወደ ሜዳ ወይም ጫካ ለትግል ስንገባ እ.አ.ኤበ 1978 ንጉሱ በደርግ ተተክተው ነበር:: የግዴታ ጠመንጃ ይዘህ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነበር፤ ሌላ የተሻለ አማራጭ ፈፅሞ አልነበረንም::

**ግዮን፡- እርስዎ በበረሃ ትግል ውስጥ ለስንት አመት ቆዩ?**

**ሌንጮ፡-** ከላይ በጠቀስኩልህ መንገድ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ78—91 ባለው አስራ ሶስት ዓመት ያህል ከኦነግ ጦር ጋር በረሃ ነበርኩ::

**ግዮን፡- በእነዛ 13 ዓመታት ከነበረው አጠቃላይ እንቅስቃሴ አንፃር፣ ምን ያህል ውጤታማ ነበርን ብለው ያስባሉ?**

**ሌንጮ፡-** ብዙ ነገር አላደረግንም:: አንደኛ ሐረርጌ የነበረው የእኛ ሜዳ ሁለት ጠላት አጋጠመው፤ ከፊት ደርግ ከኋላ ደግሞ በሱማሌ የታጠቁ ኃይሎች:: ይሄ ነገር የእኛ ትግል በወቅቱ እንዲቀጭጭ አድርጎታል:: ከዚህ ለማምለጥ ወለጋ ውስጥ ትልቅ ትግል ጀመርን፤ በሱዳን ድንበር አካባቢ ማለት ነው:: እዛም ብዙም ሳይቆይ ከፊት ደርግ ከኋላ ደግሞ ኤስ ፔ ኤል ኤ የሚባል ኃይል አጋጠመን፤ ያም እንዲሁ ትግሉ እንዲቀጭጭ አደረገ:: ለዛ ነው በፈለግነው ያህል ማደግ ያልቻልነው::

**ግዮን፡- በ1983 ዓ.ም ደርግ ሲወድቅ፣ እናንተም በሽግግር መንግስቱ ለመጠቀም ወደ ሀገር ገብታችሁ፤ ተመልሳችሁ ወደ ትግል ወጥታችኋል፤ ያኔ በእድሉ ሳትጠቀሙ በመውጣታችሁ የሚፀፅታችሁ ነገር አለ?**

**ሌንጮ፡-**በፍፁም:: ምንም አይፀፅተንም:: በሰዓቱ መውጣታችን ትክክል ነበር:: ምርጫም አልነበረንም፤ ግን በዛች አጭር ጊዜ ውስጥ የኦሮሞን ህዝብ ለማነቃቃት የተሰራው ሥራ ከባድ ነው:: ጥለን መውጣታችን ግን ትክክለኛ ውሳኔ ነበር:: መቼም አይፀፅተንም::

**ግዮን፡- በጊዜው በሽግግር መንግስቱ ምስረታ ላይ ኦነግ (እናንተ) የመገንጠል ሀሳብን ይዛችሁ በመነሳታችሁ ነው ከኢህአዴግ ጋር ልትስማሙ ያልቻላችሁት ይባላል?**

**ሌንጮ፡-** አይደለም:: በጊዜው የፈለግነውን አጀንዳ ብንቀርፅም ከወያኔ ጋር መቆየት አንችልም ነበር፤ እነሱ ራሳቸው ኦህዴድ የተሰኘውን ድርጅት ፈብርከው አምጥተዋል:: እኛን ለማጥፋት ውሳኔ ላይ የደረሱት ገና ሥልጣን ሳይዙ ሜዳ እያሉ መሆኑን ያሳያል:: ይሄ ብዙም የሚገርም ነገር አይደለም::

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁን ሰዓት የብሔር ፌደራሊዝም ችግር እየፈጠረ ነው ይባላል:: እርስዎ የብሔር ፌደራሊዝም ያዋጣል ይላሉ?**

**ሌንጮ፡-** ሌላ ምርጫ የለም:: ማፍረስም አይቻልም:: አሁን ያለውን የብሔር ፌዴሬሽን አፈርሳለሁ ካልክ ኢትዮጵያን ነው የምታፈርሰው:: ስለዚህ ይሄን ጉዳይ በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል::

**ግዮን፡- ከወያኔ ጋር ተጣልታችሁ ኦነግ ከሀገር እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ እርስዎ ወዴት ሄዱ?**

**ሌንጮ፡-** እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም ከሽግግር መንግስቱ እንደወጣን እኔ ወደ እንግሊዝ ሀገር ነው የሄድኩት:: እዛ ትንሽ ቆየሁና ወደ ካናዳ ሄድኩ:: ካናዳ ግን ብዙ ዓመት ኖርኩኝ::

**ግዮን፡- ካናዳ እያሉ ነበር ቤተሰብ የመሰረቱት?**

**ሌንጮ፡-** ቤተሰብ የመሰረትኩት ወንበዴ ሳልሆን ነው:: ወደ ትግል ጫካ ወይም ሜዳ ሳልወጣ ማለት ነው::

**ግዮን፡- በዚህ አጋጣሚ ቤተሰብዎን ቢያስተዋውቁን?**

**ሌንጮ፡-** ሶስት ልጆች አሉኝ፤ ሁለት ሴትና አንድ ወንድ ናቸው:: ልጆቼ ወግ ማዕረግ በማየታቸው እኔም አያት ሆኛለሁ:: …. ባለቤቴም ታጋይ ነች:: ደርግ ወደ አስር አመት ያህል አስሯታል፣ ማርታ ጉግሳ ትባላለች፤ አሁና ካናዳ ውስጥ በሚገኝ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ ነች::

**ግዮን፡- ከልጆችዋ የእርስዎን የፖለቲካ መንገድ የተከተለ አለ?**

**ሌንጮ፡-** ማንም የለም:: ትልቋ ትንሽ ወደ ፖለቲካ ይነካካታል፤ ሁለቱ ግን ጨርሶ ወደ ፖለቲካ አይቀርቡም:: ፍላጎቱም የላቸውም::

**ግዮን፡- ከወያኔ ጋር ተጣልተው ከወጡ በኋላ አንድ የእናንተ ሰው በመታሰሩ፣ እርስዎ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የታሰሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: እስኪ ያንን አጋጣሚ ያጫውቱኝ?**

**ሌንጮ፡-** በ1994 (እ.ኤ.አ) መጀመሪያ ላይ አንድ ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ ተጠርቶ ነበር፤ ኢብሳ ጉተማ የሚባል ሰው ቀደም ብሎ ሲመጣ እሱን አሰሩት፣ ወያኔ ይሄንን የእኛን ሰውዬ ማሰር አይገባውም በማለት ተጣልቼ ብወጣም ቀጥ ብዬ ወደ ሀገር ቤት መጣሁ::

በራሴ ውሳኔ ግለሰቡን ለማስፈታት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቴ ድርጅቱ (ኦነግ) ከኃላፊነቴ አነሳኝ:: እኔም ውሳኔውን ተቀብያለሁ:: እዚህ እንደመጣሁ ወያኔዎቹ ያዙኝና ለአንድ ሳምንት ያህል አሰሩኝ::

**ግዮን፡- እንዴት ሊለቀቁ ቻሉ?**

**ሌንጮ፡-** ከመለስ ጋር ከተወያይን በኋላ በጉዳዩ ላይ በመተማመናችን እንድንለቀቅ አደረገ::

**ግዮን፡- ከመለስ ዜናዊ ጋር በጣም ትቀራረባላችሁ ሲባል ይሰማል ፤ይሄ ነገር ትክክል ነው?**

**ሌንጮ፡-** ከመለስ ጋር በምንም አንግባባም:: ሁሌም በጣም ነው የምንጨቃጨቀው፤ ግን የእርሱን የአዕምሮ ችሎታ አደንቃለሁ:: ስለዚህ መጨቃጨቁ ጠቃሚ ነበር ለእኔ:: ይቀራረባሉ ወይም ይግባባሉ የሚለው ፈፅሞ የተሳሳተ ነው::

**ግዮን፡- የእሳቸውን ሕልፈተ ህይወት ሲሰሙ ምን ተሰማዎት?**

**ሌንጮ፡-** ምንም የተለየ ስሜት አልተሰማኝም::

**ግዮን፡- ከኦነግ አባልነትም ሆነ ከፍተኛ አመራርነት መቼ ነው የወጡት?**

**ሌንጮ፡-** እኔ አልወጣሁም፤ አባረሩኝ እንጂ :: በፈረንጆቹ 2011 ዓ.ም አካባቢ ይመስለኛል ፤ አሁን ርግጠኛ ባልሆንም:: ከሽግግር መንግስቱ ከወጣንና ከወያኔ ጋር ከተጣላን በኋላ፣ እኔ ኦነግ ስትራቴጂውን መልሶ እንዲመረምር ነበር የፈለግሁት:: ሀሳብም አቀረብኩኝ ለድርጅቱ:: በአመራር አካል ውስጥ እያለሁም ሆነ ከዛ በኋላ የተለያዩ ሀሳቦችን አቀረብኩ፤ ግን አልተቀበሉትም::

በመጀመሪያ መጽሐፌ ላይ ይሄን ፌዴሬሽን ተቀብለን እሱን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ እንታገል የሚል አቋም ያዝኩ፤ አልወደዱትም:: እንደዛም ሆኖ ከኦነግ ጋር እየሰራሁ ሀሳቤን እንዲቀበሉ ለማድረግ ለመታገል ወሰንኩ:: ሀያ ምናምን ዓመት በዛ መንገድ አሳለፍኩ:: በመጨረሻ የእኔን ንትርክ መቋቋምና በሀሳብ መብለጥ አቅቷቸው ራሳቸው አባረሩኝ::

**ግዮን፡- ኦነግን በሊቀ/መንበርነት ያገለገሉት እስኪባረሩ ድረስ ነው?**

**ሌንጮ፡-** እኔ በ94 (እ.ኤ.አ) ከኃላፊነት ከተነሳሁ በኋላ ሁለተኛ ወደ ኃላፊነት አልተመለስኩም:: እንደ ተራ አባል ሆኜ ነው ስታገል የቆየሁት:: በ2011 (እ.ኤ.አ) ከድርጅቱ በገለፅኩት መንገድ እስክባረር ድረስ ማለት ነው::

ያኔ እነርሱ ሲያባርሩኝ ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ጭንቀት ደረሰብኝ:: ምን ልሆን ነው? ህይወቴን በሙሉ በፖለቲካ ውስጥ አሳልፌያለሁ፣ ምን ማድረግ አለብኝ ? በሚል አስቤ ተመሳሳይ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን (ኦዴግ) መሰረትን::

**ግዮን፡- አዲስ ያቋቋሙት ኦዴግ በርካታ ዘመናት ከታገሉለት ኦነግ በምን ይለያል?**

**ሌንጮ፡-** አንደኛ ነገር ይሄ ፌደሬሽን ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን መታገል፣ ይሄንንም ለማሳካት ሰላማዊ መንገድን ብቸኛ አማራጭ ማድረግ፣ ሶስተኛ በኢትዮጵያ ደረጃም ራዕይ እንዲኖረን ስለ መስራት በሚሉት ነጥቦች ከኦነግ ሙሉ በሙሉ እንዲለይ ያደርገዋል::

**ግዮን፡- ማን ማን ሆናችሁ ነው ድርጅቱን የመሰረታችሁት?**

ሌንጮ፡- 2013 ይመስለኛል የተመሰረተው:: ዲማ ነገዎ፣ ሐሰን፣በያን፣ሁሴንና ሌንጮ ባቲ

**ግዮን፡- የእናንተ ኦዴግ የተሰኘው ድርጅት የመገንጠልን ዓላማ በመተው፣ ከኦነግ ሙሉ በሙሉ ልዩ አያደርገውም?**

**ሌንጮ፡-** እሱ ብቻ አይደለም:: ኦነግ በነበርኩ ጊዜ እኛ ያመጣነው አሰራር ነው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጉዳይ:: የኢህአዴግን ሀሳብ ወስዶ አድጎ መቃወም ትክክል አይደለም:: እውነት ነው ፌደሬሽኑ ዴሞክራሲያዊ አልነበረም፤ ዴሞክራሲያዊ ማድረጉ ግን ኦሮሞን ይጠቅማል፤ ለኢትዮጵያ ህዝብም ይጠቅማል የሚል ዕምነት ነው የያዝነው እኛ::

ይሄንን ለማድረግ ደግሞ ብቸኛው መፍትሄ በሠላማዊ መንገድ መታገል ብቻ ነው:: እሱን

ተቀብለን፣ ሀገር ቤት ገብተን፣ በሥነ ሥርዓቱ ተመዝግበን፣ በህጋዊ መንገድ ለመታገል ነበር የወሰንነው:: ይሄንንም ለማሳካት ከመንግስት ጋር ብዙ ጊዜ ግንኙነት አድርገን ሳይሳካ ቀረ:: መጨረሻ ላይ ይኸው መጥተናል::

**ግዮን፦ በእኛ አቆጣጠር 2006 ዓ.ም ላይ ከረዥም ጊዜ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር፤ ሶስት ቀን ቆይተው ነው የተመለሱት:: የአመጣጥዎ ምክንያት ምን ነበር?**

**ሌንጮ፦** ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ውጪ እንገናኝ ነበር፤ እኛ ሀገር ቤት ተመልሰን ለመታገል እንደምንፈልግና ይሄንን እንዲያሳኩልን ጠይቀናቸው ነበር:: እስከ ጠ/ሚኒስትሩ ድረስ ነው በዚህ ላይ ውይይት ያካሄድነው::

በመጨረሻ ላይ አቶ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ “ኢትዮጵያ ብትመጣ ለአንተ ምንም ችግር አይኖርም፣ የሴኩሪቲ ሁኔታ አያሳስብህ፤ እንደውም ጥበቃ በማድረግ ዋስትና እንሰጥሃለን” አለኝ:: አስቀድመን ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ያደረግነው ውይይት ምንም አይነት ውጤት ሊያመጣ ስላልቻለ እዛው ሄደን እንወያይ በሚል ወደ እዚህ መጣን::

አዲስ አበባ በገባን በሁለተኛው ቀን ልጆች ልከው ተመልሰን በሌላ ጊዜ እንድንመጣ ነገሩን:: በዛ መሰረት በሶስተኛው ቀን ወደ መጣንበት ተመለስን::

**ግዮን፦ ከእርስዎ ጋር ለድርድር አብረዎት የመጡት እነማን ነበሩ?**

**ሌንጮ፦** አብረን የመጣነው እኔና ደራራ ማቲ የሚባል ሰው ነበር፣ እንዲሁም አንድ ቀድሞን እዚህ ገብቶ የነበረ ሌላ አባላችን በአጠቃላይ ሶስት ነበርን::

በርግጥ ኢህአዴጎች እንድንመጣ አልጋበዙንም፤ራሳችን ነን የመጣነው:: ሀገራችን ስለሆነ ለመምጣት ማስፈቀድ አይጠበቅብንም:: ግን ከመጣን በኋላ ሊያናግሩን ስላልፈለጉ እንድንወጣ ነው ያደረጉት::

**ግዮን፦ እናንተ የመጣችሁበት ወቅት የኦህዴድ 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል ለማክበር ድርጅቱ ዝግጅት ላይ የነበረበትና እናንተን ሆን ተብሎ ሀገር ቤት ከገባችሁ በኋላ ያለ ስሚ ተመልሳችሁ እንድትወጡ አስቀድሞ የታቀደ መሆኑ ሲነገር ቆይቷል::**

**ሌንጮ፦** እኛ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ወደ ሀገር ቤት በህጋዊ መንገድ ገብተን፣ ድርጅታችን አስመዝግበን፣ በሠላማዊ መንገድ ለመታገል ነበር አላማችን እንጂ፣ እንደሚባለው ከኦህዴድ ምስረታ በአል፣ ምናምን ጋር ፈፅሞ የሚያገናኘው ነገር የለም::

**ግዮን፦ የኦሮሞ ህዝብ ስቃይ ስደትና እንግልት አሁንም መቆም አልቻለም፤ እርስዎ በዚህ ላይ የተለያዩ መጻሕፍትን እንደማዘጋጀትዎ መፍትሄው ምንድን ነው ይላሉ?**

**ሌንጮ፦** አንደኛ መታወቅ ያለበት አሁን የሽግግር ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው:: ይሄ ደግሞ ብዙ ችግሮችን ብዙ ኢንስተብሊቲ ይፈጥራል:: ይሄ ኢንስተብሊቲ በመገኘቱ መገረም የለብንም:: የባሰ እንዳይመጣ መጠንቀቅና ባለው ለውጥ ላይ መትጋት ነው የሚያስፈልገው::

አሁን እየተካሄደ ያለውና ለውጥ የሚመስል ዓይነት ለውጥን ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዚህ በፊት አካሂዳ አታውቅም:: ከዚህ በፊት የማፈናቀል አይነት ለውጥ ነው የነበረው፤ አሁን ግን የጥገና ለውጥ ነው እየተካሄደ ያለው:: በጥገና ለውጥ ደግሞ ለውጡን ደጋፊም ተቃዋሚም ሀገር ቤት ውስጥ፣ ገገርው ፓርቲው ውስጥም አሉ::

ከዚህ በመነሳት አንዱ ሌላውን ለማደናቀፍ የሚያደርጉትን ተከትሎ የሚነሱና የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን መገመት ይቻላል:: ለመፈናቀልና ለፀጥታ ጉዳዮች መነሻ የሆኑ ችግሮችን የሚፈጥረው ጉዳይ ይሄ ይሆናል የሚል ዕምነት ነው ያለኝ::

**ግዮን፦ ኦነግን ከመሰረቱ ሰዎች መሀል በቀዳሚነት ተባረው የመጡት እርስዎ ኖት?**

**ሌንጮ፦** እኔ የመጀመሪያው አይደለሁም:: ኦነግ መሰነጣጠቅ ከጀመረ ረዥም ጊዜው ነው በጣም ቆይቷል:: እኔ አሁን ስለ ኦነግ ማውራት አልፈልግም:: የድርጅቱ ሰዎች እዚህ ስላሉ እነርሱን ፈልገህ አግኝተህ ማነጋገር ትችላለህ:: …. እኔ አሁን ኦነግ አይደለሁም::

**ግዮን፦ ኦነግስ የማን ነው?**

**ሌንጮ፦** ሶስት ኦነግ አለ:: ሶስቱም ባለቤት አለው:: እነርሱን ፈልግና ጠይቃቸው::

**ግዮን፦ የኦሮሞ ህዝብ በተለየ ሁኔታ እንደ እራሱ የሚቆጥረውንና እንደ አርማ ሁልጊዜ የሚጠቀምበት ድርጅትና እንቅስቃሴውን በተመለከተ፣ በዚህ የችግር ሰዓት እናንተ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ሰዎች በገሃድ አደባባይ ወጥታችሁ አንድ ነገር ማለት አለባችሁ ስለሚባል ነው ይሄንን ነገር ያነሳነው::**

**ሌንጮ፦** እኛ ዝግጁ ነን:: እኛ ብንጠራ ማንም አይቀበለንም፣ ብንጠራ ግን እንሄዳለን:: ችግሮቹን ቀርፎ ወደ ፊት የሚያይ አንድ ጥሩ ነገር እንዲፈጠር ከተፈለገ መቼም ይሁን መቼ እኛ ያንን ለማድረግ ዝግጁ ነን::

**ግዮን፦ በአሁኑ ሰዓት የገላሳ ዴልቦ ኦነግ፣ የዳውድ ኢብሳ ኦነግ፣ የአባነጋ ኦነግ አለ፤ እናንተ ከነዚህ ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ የመነጋገር ፍላጎቱ የላችሁም? …… ከተቻለ አንድ የኦሮሞን ህዝብ የሚወክል ድርጅት ለመፍጠር?**

**ሌንጮ፦** እኛ እንፈልጋለን:: ግን እነዚህን ቡድኖች የሚያቀራርብ፣ የሚያደራድር አካል ያስፈልጋል::

እዚህ ሀገር እንደተመለስን ይሄንን ሥራ እንዲሰራ ለአብኮ (ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ) ጥሪ አቅርበንላቸዋል:: ቢሆን የምፈልገው ነገር ስለሆነ እስካሁን ድረስ እንግዲህ የእነሱን ምላሽ እየጠበቅን ነው ያለነው:: ባለኝ መረጃ መሰረት ኃላፊነቱ የተሰጣቸው አካላት እነዚህን ድርጅቶች ከእኛ ጋር ለማገናኘትና ለማወያየት እየሞከሩ ነው፣ እንቅስቃሴ ጀምረዋል::

**ግዮን፦ በዚህ ወቅት በወለጋ አካባቢ ከኦነግ ጦር ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን ግጭትና ውጥረት ለማርገብ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ሌንጮ፦** አሁን የሆነው ነገር ፈፅሞ መፈጠር የሌለበት ሁኔታ ነው:: ማቆምም ይቻላል:: ለማቆም ደግሞ የዳውድና የለማ መገርሳን መስማማት ብቻ ነው የሚፈልገው:: በእኛ በኩል ይሄን ቶሎ እንዲፈፅሙት ነው የምንፈልገው:: ለማንም ስለማይጠቅም::

**ግዮን፦ አቶ ለማ መገርሳና አቶ ዳውድ ኢብሳ የሚሰጧቸውን ምልልስና ማስጠንቀቂያ አዘል መግለጫዎች እንዴት አዩዋቸው? በተለይ “ትጥቅ ፍታ፣ አልፈታም” የሚለው:: በሠላማዊ መንገድ ወደ ሀገር ቤት የገባ ኃይል ትጥቅ መፍታት የለበትም?**

**ሌንጮ፦** እዚህ ላይ መናገር አልፈልግም:: ሁለቱም ቡድኖች መጀመሪያ ምን እንደተስማሙ አላውቅም::

**ግዮን፦ ሠላማዊ ትግልን ተቀብያለሁ ማለቱ ራሱ ኦነግን ከመሳሪያ ውጭ እንዲሆን አያስገድደውም?**

**ሌንጮ፦** ልክ ነው:: ሁለቱን አንድ ላይ ማስኬድ አትችልም:: ሠላማዊ ትግልን ከመረጥክ የትጥቅ ትግልና መሳሪያ ይቀራሉ ማለት ነው::

**ግዮን፦ እርስዎና ጓደኞችዎ ከ40 ዓመት በፊት “ኦነግ” የሚለውን ስያሜ አውጥታችሁ ድርጅቱን በመመስረት ለኦሮሞ ህዝብ መብት ስትታገሉ እንደ መቆየታችሁ መጠን፣ እርስዎ ዛሬ ላይ በዚህች ሀገር ምን ቢሆን ይመኛሉ? ህልሞዎስ ምን ነበር?**

**ሌንጮ፦** በኢትዮጵያ አሁን ያለው ፌደሬሽን ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ካሳካን በኋላ በድህነት ላይ መዝመት ያስፈልጋል:: ድህነት እዚህ ሀገር ከአባት ለልጅ እየተወራረሰ፣ የበለጠ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ እየመጣ ነው ያለው:: ይሄንን የሚቀይር ሥርዓት ያስፈልጋል::

**ግዮን፦ ኢትዮጵያዊነት በእርስዎ እንዴት ይገለፃል?**

**ሌንጮ፦** የእኔ ኢትዮጵያና የአንተ ኢትዮጵያ አንድ ላትሆን ትችላለች:: እኔ ኦሮሞም ሆኜ ኢትዮጵያዊ ለመሆን እፈልጋለሁ:: የአንዳንዶቹ ኢትዮጵያዊነት ግን ኦሮሞነትን አያካትትም:: ይሄን አይነት ኢትዮጵያዊነት አልቀበልም::

ሲዳማው ሲዳማም ሆና ኢትዮጵያዊ እንዲሆን፣ ሶማሌውም እንደዛው:: ትግሬዎቹም ትግሬ ሆነው ኢትዮጵያ እንዲሆኑ፣ እኔም እንደ ኦሮሞነቴ ኦሮሞ ሆኜ ኢትዮጵያዊ እንድሆን ከተቻለ ይሄንን ሙሉ በሙሉ እቀበላለሁ::

**ግዮን፦ ኦነግ ኢህአዴግ ሀገሪቷን በተቆጣጠረበትና በሽግግር መንግስቱ ጊዜ አግኝቶ ያጣውን ዕድል፣ አሁንም ከዓመታት በኋላ በሠላማዊ መንገድ ወደ ሀገር ቤት በመግባት ያገኘውን ዕድል በድጋሚ ሊያጣ ከጫፍ ደርሷል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች በርካታ ናቸው:: እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ሌንጮ፦** ኦነግ እንደተባለው ዕድሉን ሊያጣ ይችላል:: የኦሮሞ ህዝብ ግን ሊያጣ አይችልም፣ አይገባምም:: የኦሮሞ ብሔርና ኦነግን ለያይተን ማየት አለብን:: የኦሮሞ ህዝብ ዕድል መጥቷል፤ አሁን ይሄን ለማሳካት ሁሉም የኦሮሞ ድርጅትና ግለሰብ ኃላፊነት አለበት::

**ግዮን፦ የኦሮሞ ህዝብ ከራሱ አብራክ የወጣ ሰው መሪ ሆና ማየት ይመኝ ነበር፣ አሁን በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ይህ ዕውን የሆነ ይመስለኛል:: ስለዚህ ህዝቡ ከእሳቸው ጎን በመሆን ድጋፍ መስጠት የለበትም?**

ቀሪውን ቃለ ምልልስ በ ገጽ 23 ይመልከቱ


ደረጀ ይመር

# በሁለት ሲኦሎች መካከል ገነት አለ

## “ኢትዮጵያ ቀብረናታል ያሏትን ኃይሎች እየቀበረች የኖረች ሀገር ናት ”

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ

### ጽንሰሐሳባዊ ትንታኔ

ታላቁ የጀርመን ፈላስፋ H@ ግል የዕድገት ሕግጋትን ለመተንተን አንብሮ (thesis)፣ ተቃርኖ (anthithesis) እንዲሁም በሁለቱ ፍጭት ¾T>¨KÅ¨<” ›Ç=e ነባራዊ ሁኔታ አስተጻምሮ (sythesis) አማካኝነት ዘመን ተሸጋሪ እሳቤውን አኑሮ ማለፉ ይታወቃል::ይህ ሕግ በወቅቶች መፈራረቅ፣በዘመን መቀያየር፣ዝንፍ የማይል ጎያው መርህ እንደሆነ ከጠቢቡ አስተምህሮት እንረዳለን::የሄግል ዲያሌክቲካል ትንታኔን የወቅቱን የፓለቲካ ትኩሳትን እያሰናሰሉክ ለመግለጽ እጠቀምበታለሁ::የፈላስፋውን ዲያሌክቲካል ጭውውት በቁንጹሉ እንደምነካካሁ ግን አንባቢው ከወዲሁ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ::

ዲያሌክቲካል ትንታኔውን ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ስናዛምደው፣ አንብሮ ሕወሓት ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ሲጠቀምበት የነበረውን ትርክት የሚመለከት ሲሆን ይህን ትርክት በብርቱ ሲታገል የነበረው ተቀናቃኝ ኃይል ተቃርኖ እንለዋለን፤ በማሳረጊያው በሁለቱ ፍጭት የተፈጠረው አዲሱ የመደመር መርህን ደግሞ አስተጻምሮ ብለን ልንፈረጀው እንችላለን::

በሁለት ገሀነም Sካከል ገነት አለ::ይላሉ UY^nዊያን K=nውንቶች::ገሀነሞቹ u}ለያየ lSና ዳር እና ዳር የቆሙ ናቸው::በአንድ Lይ } kይጠው Sኖር አይችሉም::አንዱ ku] K?Lው }kv] SJን አለበት::በአንዱ TgKw K?Lው ዕድሜውን ይቀጥላል::በሁለቱ ተጻራሪ ጫፎች ፍትጊያ የሚወለደው ግን የጎለበተ፣ ወደፊት እንደ keት የሚወነጨፍ ነው::

ፋሺስታዊው የሕወሓት ቡድን ሀገራችንን ላለፉት 27 ዓመታት በመዳፉ ጨብጦ ሁሉን ፈቃጅ፣ሁሉን ከልካይ ሆኖ በማንአልበኝነት ጫንቃችን ላይ ሲጨፍር ከርሟል::መቼም የሕዝባችን ጫንቃ ምን ያህል ደንዳና እንደሆነ የምንረዳው ሕወሓትን የመሰለ አጥፊ ቡድን ለዚህ ሁሉ ዘመን ተሸክሞ የቆየበትን ኹነት መለስ ብለን ስናጤን ነው::ይህ አናሳ ቡድን ሲሸርበው የኖረው ሴራ የገሀነሙ አንድ ጫፍ ነበር::የገሀነሙ ጫፍ ግን በሌላ ጠርዝ ያለ ተገዳዳሪ ኃይል፣ማለትም ከውስጥ እና ከውጪ በተቀጣጠለ ሕዝባዊ ንቅናቄ፣ከሥርዓቱ ውስጥ ድንገት ብቅ ባለው ተራማጅ ቡድን አጋዥነት ድባቅ ሊመታ ችሏል::የገሀነሞቹ ጫፎች በአጥቂ እና በተጠቂ መልክ የሚሳሉ ናቸው ::አማካኙ ወይም ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ አርስቶትል “ዘጎልደን ሚን” እያለ የሚክበው እውነታ የመደመር መርህ ይሆናል::መደመር አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፣በሁለት ገሀነም ጫፍ ያሉት ኃይሎች ወደ አማካኝ መጥተው በአንድ ማእድ እንዲቋደሱ የሚጋብዝ ፍትሓዊ አውድ ነው::

> የመደመር መርህ በቀባሪው እና በተቀባሪው መካከል በተፈጠረ ግብግብ የተወለደ ተራማጅ መርህ ነው፡፡ የቀባሪው እና ተቀባሪው የእብራክ ክፋይ ቢሆኑም ቅሉ ተፈጥሮው በተቃርኖ መልክ ማዶ ለማዶ ከተሰለፉት ኃይሎች ጋር በፍጹም አይገጥምም፡፡ መርሁ ተሸናፊ እና አሸናፊ በሌለበት፣ሁሉንም አቃፊ በሆነ አውድ ውስጥ ነው ገቢራዊ የሚሆነው

> “የአማራ እና የኦሮቶዶክስን አከርካሪ ሰብረነዋል”
> ስብሀት ነጋ

በሕወሓት/ኢሕአዴግ ላለፉት 27 ዓመታት ሲቀነቀን የነበረው ፀረ አማራ ትርክት ነፍስ ዘርቶ፣ ሥጋ ለብሶ፣ ለዓይን ወድሎ፣ የማይጋፉት ባላጋራ መስሎ ነበር::ያለ አበሳው በተጨቋኝነት የተፈረጀው ሕዝብ ከቅድመ አያቱ አንስቶ እንደ ርስት የሚቆጥረውን ቀዬውን፣ጥሎ በግፍ መፈናቀልን የግል ውርሱ አድርጎት ቆይቷል::ይህ ለአማራ የተሸረበው ሴራ በተዋረድ ሌሎች የሀገራችን ሕዝቦች ቀስ በቀስ ዳፋው ሲተርፋቸው እየታዘብን ነው ::ወደ አንደ ሚሊየን የሚጠጋ ኦሮሞ ከሶማሌ ክልል፣ ክልልህ አይደለም ተብሎ ተፈናቅሏል::በደቡብ ክልልም ይኸው ክልሌን ለቀህ ውጣ የሚለው አባዜ የተመለደ ክስተት ሆኗል::

የሕወሓት ዘረመል በቁስ ሰቀቀን፣በግለኝነት እና በአውዳሚነት የተጠመቀ ነው::ይህ አናሳ ስብስብ የሚሸርበው ሴራ ዕድሜ መቀጠያው ሆኖ አገልግሎታል::ሀገራዊ ምልክቶችን በማዳከም፣ ሁሉም በየሰፈሩ የሚሰባሰብበትን ወጥመድ በማበጀት፣ የዘር ፓለቲካ እንዲጎመራ Lይ ታች ባዝኗል::

አማራውን እና ኦሮቶዶክስን አከርካሪውን ሰብረነዋል የሚለው ቀረርቶ በሕወሓታዊያን መንደር በብርቱ ሲቀነቀን ነበር::ይህንንም ሁሉም ካድሬ ሳያላምጥ እንዲውጠው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስም ተጠምቆ አምኖ እንዲቀበል መደረጉ ፀሐይ የሞቀው ገበና ነው::

አናሳው ቡድን በብዙኃን ላይ አውራ ሆኖ ያሻውን የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለማንበር ሀገራዊ ትስስርን መበጣጠስ ነበረበት::የሀገራችን ሕዝቦች በጋራ ወድቀው የተነሱባቸው ታሪካዊ ኹነቶችን ጥላሸት መቀባት የሴራው ዋናው አስኳል ነው::ከትስስር ታሪክ ይልቅ መናኛ ጥቃቅን ልዩነቶች ላይ ያተኮረ ትርክት ለሕዳጣኑ ቡድን ልእልና ትልቅ ድርሻ ተጫውቷል::

ሕወሓት ከበረሀ ጀምሮ በሴራ ፓለቲካ የተካነ አውዳሚ ድርጅት ነው::ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ያቆማትን አከርካሪ ለመስበር የጥፋት እጁን ሰብስቦ አያውቅም::ይህ የጋራ ባህል፣ታሪክ፣ሃይማኖት እና ሰንደቅ ዓላማ የትሥሥሩ ዘረመል እንደሆነ ቢታወቅም የአብሮነቱን ካስማ ፋሽስታዊው ቡድን ላለፉት 27 ዓመታት እስኪበቃው ቀልዶበታል::ከእኛ አልፎ የመላው ጥቁር አፍሪቃ ኩራት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ በጨርቅ ደረጃ አውርዶ አራክሶታል:: በሺህ ዘመናት ስትጠብ እና ስትሰፋ የኖረችውን የነጻይቱ ሀገርን ታሪክ ወደ 100 ዓመት ዝቅ እንዲል ተደርጎ ነበር::ከግልገል እስከ ቱባ ሹማምንት ይህንን ከፋፋይ ትርክት ከአጽናፍ እስከ አስጽናፍ አስተጋብቷል::

ሀገር በመመሥረት ሒደት ውስጥ የተፈጠሩትን ጥቁር ጠባሳዎች ሕዳጣኑ ቡድን ለፓለቲካ ንግድ ሲጠቀምበት ነው ▶

የኖረው::ኢትዮጵያን በአማራ ፊታውራሪነት በሌሎች የሀገራችን ሕዝቦች የበይ ተመልካችነት የተቀለሰች ኢምፓየር እንደሆነች ነበር የተሰበከው ::አማራ በሀገሪቱ የዘውግ ማኅበረሰቦች ላይ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ፣ ሁሉም ብሔሮች ምንም ሳይነካኩ በታአምር እንደ አበባ ፈክተው በተድላ እና ፍስሀ ይኖሩ ነበር፤ የሚል ልብወለድ ሊግተን በብርቱ ተውተርትሯል::እንግዲህ የሕወሓት ዲስኩርን በእዝነልቦናቸው የተቀበሉትን የሀገራችን ብሔረሰቦች በዚህ ትብታብ ሴራ ዐይናቸው ተጋርዶ፣ የአንድነት ምልክቶችን ለማፈራረስ ለጥፋት ኃይሉ ድንጋይ ለማቀበል ተገድው ነበር::

ሀገር በማዋሀዱ ሒደት ላይ የተከሰቱት ታሪካዊ ምስቅልቅሎች በሕወሓት መዝገበ ቃላት ትርጉማቸው ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን:: ሀገር የማቆሙ ታሪካዊ ኃላፊነት በምኒልክ ፋንታ ከኦሮሞ ወገን ከተገኘ የጦር አበጋዝ ጆቴ ወይም ከትግራይ ማሕጸን ከወጣ ሐጎስ ላይ ወድቆ ቢሆን ኖሮ ከኃይል አማራጭ ውጪ ምን አይነት ታአምር ይጠቀም ነበር?ብለን ብንጠይቅ ቂሱም ዝም መጽሐፉም ዝም ይሆናል::

ታሪክ የሚነግረን ሐቅ ማንኛውም ሀገር የተመሠረተው በአፈሙዝ ኃይል ነው::ለዚህም ነው ታላቁ ጀርመናዊው ቢስማርክ “The wheel of history never moves without blood and iron” ያለው::የትኛውም ሀገር በድርድር ወይም በማማባበል አልተፈጠረም::ሀገራችን ያለፈችበት የታሪክ አሻራ ሒደት በሌላው ዓለም ፊት ፀጉረ ልውጥ ሊሆን አይችልም ::የእኛን የተለየ ያደረገው በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ያልዳበረ ማኅበረሰብ ለዘመናት መፍጠር ተስኖን እንደ ተርኪስ ባቡር ቆመን መቅረታችን ነው::

እንግዲህ ይህ ተጨባጭ እውነታ ላለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት የፓለቲካ ንግድን ለማጧጧፍ እንደ ኹነኛ ሲሳይ ተቆጥረው ቆይተዋል:: ሕወሓት የአንድነቱ ካስማን ለመስበር በጨቋኝ ተጨቋኝ ተረክ የሀገሪቱን ዘውግ ማኅብረሰቦች ንቃት ለመስለብ ችሏል::ይህ እኩይ አላማው ፍሬ አፍርቶ ሀገር ምድሩን እንደሞላ በተረዳ ጊዜ ፣ስለአከርካሪ አሰባበር ሴራ መደሱኮሩን ሙያ ብሎ ተያያዘው::

ድርጅቱ የሀገሪቱን አንድነት አከርካሪ ለመስበር ከተጠቀመባቸው መዶሻዎች አንዱ የ1987ቱ ሕገመንግሥት በዋንኛነት ይጠቀሳል:: ሰነዱ ሀገራዊ ቀለሞችን ለአንድ ሕዝብ እና ሃይማኖት ጠቅልሎ በማሸከም ሌላው ሕዝብ የተብሰልሳይነት ወይም የባይተዋር ገዳም ውስጥ ራሱን ጨምሮ ለቂምበቀል እንዲያደባ ፈርዶበታል::ብሔሮች ድንበሬን ገፋህኝ በሚል በቀበሌ ፣በጎጥ እርስ በርስ መናከስ ከጀመሩ ሁለት ዐሥርተ ዓመታት አለፉ:: ይህም እርስ በርስ መናቆር ለደደቢቱ የጥፋት ቡድን አዱኛ ሆነለት:: ማእከሉን ያለተቀናቃኝ አጥብቆ በመያዝ ያሻውን ሲዘርፉ፣ግፍ ሲፈጽም ኖሯል::

ሕወሓት የሀገራችን ብሔሮች ከአራቱም ማእዘን ተጠራርተው ፋሽስት ኢጣሊያን ድባቅ የመቱበትን አንጸባራቂውን የአደዋ ድልን ጭምር እንደወረደ አይቀበልም::ለሴራ ዓላማው በሚመች መልኩ ቀድዶ መልሶ ይሰፋዋል::

ሌላው የአብሮነት ወይም የትሥሥራችን አትብት ሰንደቅ አላማችን እደሆነ ይታወቃል::በዚህም የነጻነት አርማ ላይ ብዙ በደል ተሰርቷል::ሰንደቅ ዓለማው የአተንኩኝ፣የአልበገር ባይነት፣የነጻነት ምልክት ነው::በዚህ ባንዲራ ሥር ተሰልፈው ደም እና አጠንታቸውን የከሰከሱት ጀግኖች አባቶቻችን አጽም ተራክሷል::የዚህን ሰንደቅ አላማ አልባሌ ለማድረግ ለክልሎች ጨርቅ መትሮ እንደራሽን በማከፋፈል ሀገራዊ ትስስሩን አደጋ ላይ ለመጣል ተሞክሯል::

የሕወሓቱ ቁንጮ ሹማምንት አማራውን እና ኦርቶዶክስን አከርካሪውን ሰብረነዋል::እያሉ ለመታበያቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሴራዎች ፍሬ እንዳፈሩ እርግጠኛ በመሆናቸው ነበር::ሴራው ግን ሾተላይ መታው::ድንገት በተፋፋመ ውርጃ ተደናቀፈ::አንብሮው ከተቃርኖ ብርቱ ፈተና ገጠመው::እንዴት?

## “ኢትዮጵያ ቀብረናታል የሚሉትን ኃይሎች እየቀበረች የኖረች ሀገር ናት” ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ

ሀገራችን ኢትዮጵያን ከትቢያ ሊቀላቅሏት በብርቱ ሲገዳደሯት የነበሩ ኃይሎችን ስናታስተናግድ ኖራለች::ግብጾች አባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር የከፈተቱን ጦርነት አጼ ዮሐንስ ከአንድም ሦስት ጊዜ አሳፍረው መመለስ ችለዋል::ኢትዮጵያን ታሪክ ለማድረግ ጦር ሰብቆ የመጣውን ፋሽስት ኢጣሊያን አደዋ ላይ አይቀጡ ቅጣት ተቀጥቷል::የፋሽስቱ ወራሪ ኃይሎች በኢትዮጵያ አፍር ላይ ተቀብረው ቀርተዋል::

ፋሽስት ኢጣሊያ ከታሪክ ሳይማር ከአርባ ዓመት በኋላ ዳግም ለወረራ በመጣ ጊዜ ይጠቀምበት የነበረው ትርክትን ሕወሓት በቁሙ ነው የተቀበለው::ጣሊያን አርባ ዓመት አድብቶ ነጻይቱን ሀገር በመዳፉ ለመጨበጥ እንደመጣ ፀረ የሸዋ አማራ አገዛዝን በመስበር ሌሎች ብሔሮችን ነጻ ለማውጣት እንደመጣ በይፋ አውጆ ነበር::

ፋሽስታዊው የደደቢት ፍሬ የወራሪው የጣሊያን የግብር ልጅ ነው::ገና ከመሬት ብቅ ሳይል አማራ ላይ ጦርነት አወጀ::ከውልድት እስከ ጉልምስናው ይህንን አቋሙን መከለስ አልቻለም:: ከማኒፌስቶው አንስቶ እስከ ሕገመንግሥታዊ ሰነድ ድረስ ኢትዮጵያን ለመቅበር ብዙ ዳገት ዘሏል፣ብዙ አቀበቶችን ቧጥጧል:: ነገር ግን ኢትዮጵያ ቀባሪዎቿን የመቅበር ምስ አላት እና የጥፋት ኃይሉ እንደወጣ እንዲቀር በሦስትዮሽ ወይም ፒራሚዳዊ በሆነ ቀለበት ከፍተኛ የጥቃት ዘመቻ ተከፈተበት:: አንብሮው (ፀረ አማራ ወይም ፀረ ኢትዮጵያ }[ኰ) K?L የሚገዳደረው ኃይለኛ ወጀብ መጣበት::አከርካሪውን የመሰበር ዘመቻውን የሚያጣፋ ሌላ ተቃርኖ ከወዲያኛው ጥግ ብቅ ብቅ ማለት ጀመረ::

ፀረ ኢትዮጵያዊው ኃይል ግበዓት ቀብር ለመፈጸም በፒራሚድ መልክ ሦስት ማእዘን ግንባር የፈጠሩት ኃይሎች በትራቸውን ማሰራፍ አሀዱ ሲሉ የእምቧይ ካብ የሆነው ሥርዓት እንደ ዐይን ጥቅሻ ፈጥኖ መፈረካከሱን ተያያዘው::

የፒራሚዱ ታችኛው ጫፍ ላይ መሬት አንቀጥቅጥ የነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄ በአንድ ወገን ተሰልፏል::ሕዝባዊው ንቅናቄ በሁለቱ የሀገሪቱ ትልልቅ የዘውግ ማኅበረሰቦች ኦሮሞ እና አማራ ላይ መሠረቱን መጣሉ ደግሞ ሳይውል ሳይደር ፍሬ እንደሚያፈራ የሚጠበቅ ነበር::በአንድ ገበታ መቀመጥ አይችሉም፣ እሳት እና ጭድ ናቸው ተብለው የተፈረጁት ሕዝቦች ለገዢው ቡድን ቅኔ ሆኑበት::

ይህ እንደ እሳተ ጎመራ ድንገት የፈነዳው የተቀውሞ ኃይል የሕወሓትን እብሪት መቃበር ከማወረድ ወደኋላ እንደማይመለስ ፍንጮች ገና እንደታዩ አከርካሪውን ለመስበር የተነሳው ክንድ መስነፍ ጀመረ::የሕወሓት መርዛማ ቀስቶቹ ኢላማቸውን እየሳቱ መከኑ::

ሕዝባዊ ንቅናቄ በሌላኛው የፒራሚድ ጫፍ ሆኖ እገዛ ያደረገው በባህር ማዶ የተቀጣጠለው ሁሉን አቀፍ የትግል ስልት ነበር::ሕወሓት ወትሮም ቀልቡ የማይወደው ዲያስፓራው የጎን ውጋት ሆነበት::ከተከታታይ የተቀውሞ ሠልፎች እስከ ዶላር እቀባ ድረስ የዘለቀው ትግል ሀገር ቤት ለተቀጣጠለው አመጽ ግርማ ሞግስ ሊያላብሰው ችሏል:: የዶላር እቅባው በቋፍ ላይ የነበረውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የበለጠ ማጥ ውስጥ ጨምሮታል::በዚህም የተነሳ ዘረኛውን ሥርዓት በማይትኩስበት ባላንጣ ተገዝግዞ ተግዝግዞ ከመቃብር አፋፍ ላይ ሊቆም ችሏል::ይህንን መቃብር ላይ የቆመ ሥርዓት ገፍትሮ ለመጣል ሕዝባዊው ንቅንቂ እምብዛም አላዳገተውም::ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመገናኛ ብዙኃን እና የማኅበራዊ ሚዲያ ሚና የሚናቅ አልነበረም:: በተለይ በዚህ ረገድ ኢሳት በዋንኛነት የሚጠቀስ የሚዲያ ተቋም ነው::

የፒራሚዱ ዳር እና ዳር ትግልን በስኬት እንዲገባደድ፣ በፒራሚዱ ጫፍ ላይ ያለው ኃይል ወሳኝ ሚና ተጫውቷል:: ከኢሕአዴግ ማሕጸን ውስጥ ሰብሮ የወጣው ቲም ለማ እና ቲም ገዱ የተቃውሞውን መዳረሻ ለማሳየት በትር ሆኖ አገልግሏል:: በኢሕአዴግ ውስጥ የተከሰተው የለውጥ ኃይል ልክ ሌኒን የላብአደሩን መሬት አንቀጥቅጥ አብዮት ግቡን ይመታ ዘንድ በፓለቲካ አመለካከታቸው የበቁ ኢሊቶች የተሰባሰቡበት ቫንጋርድ ፓርቲ ያስፈልጋል ካለው አስተምህሮት ጋር ይመሳሰላል:: የቲም ለማ እና የቲም ገዱ ስብስብ ለነበረው መሬት አንቀጥቅጥ አመጽ እንደ ቫንጋርድ ፓርቲ ሆኖ ማሳረጊያው እልቂት ከመሆን ይልቅ ብሩህ ተስፋ የሚንጸባረቅበት ሥርዓት እንዲወለድ የድርሻቸውን ተወጥተዋል::በዚህም አዲሱ የለውጥ አስተዳደር እንደ እንቁላል ከውስጥ ሰብሮ በመወጣት በእግሩ የሚድህ፣ የሕዝብ ወገንተኝነት ያልራቀው ትኩስ ኃይል ለመሆን ችሏል::

መደመር (አስተጻምሮ)

የመደመር መርህ በቀባሪው እና በተቀባሪው መካከል በተፈጠረ ግብግብ የተወለደ ተራማጅ መርህ ነው::የቀባሪው እና ተቀባሪው የአብራክ ክፋይ ቢሆኑም ቅሉ ተፈጥሮው በተቃርኖ መልክ ማዶ ለማዶ ከተሰለፉት ኃይሉች ጋር በፍጹም አይገጥምም::መርሁ ተሸናፊ እና አሸናፊ በሌለበት፣ሁሉንም አቃፊ በሆነ አውድ ውስጥ ነው ገቢራዊ የሚሆነው::በቀባሪው እና በተቀባሪው ወይም በሁለቱ ጋሀነሞች መካከል እውን የሆነ ገነት ነው::በአስተጻምሮ መልክ የተከሰተው አዲሱ ነባራዊ ሁኔታ በቀባሪውም፣በተቀባሪውም ዘንድ ያልተመለደ እንግዳን ባሕሪን ስለተላበሰ ደርሶ ለጠብ አይጋበዝም::ለሰይፍ የተነሳውን ክንድ በይቅርታ እና በፍቅር ያርዳል::

በመደመር መርህ የዋጅች ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ወያኔ ማን ነው?

አብዛኛው ሰው ወያኔ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው በተሳሳተ መንገድ ነው:: የቃላቱ አመጣጥና ትርጉም ትግርኛ-አማርኛ መነሻ (root) ሲሆን "ወያኔ" ትርጉሙ ወየነ፣ወገነ፣ ሸፈተ፣ አመፀ፣ እምቢአለ ማለት ሲሆን:: ሲተነተን ደግሞ አብዮት አነሳ:: በአምባገነኖች አልገዛም አለ ማለት ነው:: ወገነ ሲል ደግሞ ለተበደሉት ነጻ ሊያወጣ ከነሱ ጎን ተሰለፈ ማለት ሲሆን፤ ሸፈተ ሲል ደግሞ ከፀረ ዴሞክራቶች እና ከአምባገነኖች ጋር ለመግጠም ወደ በርሀ ገባ፤ ለመታገልም ቆርጦ ተነሳ የሚል ስያሜ ያለው ነው:: እምቢ ማለት ደግሞ ዴሞክራሲን የሚጨፈልቅ አምቢ አልገዛም፤ከሕዝብ ሀብትና ንብረት ላይ ሙስና የሚበሉትን አትዘርፉም፤ ፀረ ሕዝብ አምባገነኖችን እስከ መጨረሻው ድረስ መታገል የወያኔዎች ጽኑ መርህ ነው:: ወያኔ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ከትግራይ ሕዝብ ትግል ጋር አብዝቶ ቢያያዝም፤የአማራ የጎጃም አመፅ፣ የኦሮሞ የባሌ አመፆች የመሳሰሉት ሕዝባዊ የእምቢተኝነት ትግሎች በአላማና በስያሜ አንፃር ሲታይ ከወያኔነት ጋር በቅርበት የሚገናኙ ናቸው:: ምክንያቱም በኢትዮጵያ የነበረውን የፊውዳል ሥርዓት ለመቃወምና ሥርዓቱን ለመጣል የተደረጉ ትግሎች ማሳያ ስለነበሩ::

> ስለእውነት ብለው የታገሉት አሁንም ድረስ በእውነት ላይ የቆሙትን እውነተኛ ወያኔዎች ናቸው

በዚህ ጽሑፌ ወያኔ የሚለው የቃል ትርጓሜ በትክክል እየተጠቀምንበት ስላልሆነ ይህን ማረም ተገቢ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ:: እስኪ ወያኔነትን ከሕወሓት ትግል ጋር አያይዘን እንመልከተው፤ በርካታ የትግራይ ወጣቶች ወይነው ወደ ትግል በመውጣት ለሕዝብ የነበራቸውን የሚጠቅም ዓላማ አንግበው አንድያ ሕይወታቸውን ያለ ድርድር ሰጥተዋል:: ለምሳሌ ሕወሓት አዲስ አበባ እስኪቆጣጠር ድረስ በትግሉ የተሰለፉ ከስድሳ ሺህ በላይ ወጣት ታጋዮች (ወያኔዎች) መስዋእትነት ከፍለዋል:: እነዚያ እውነተኛ የሕዝብ ልጆች፤መተኪያ የሌላትን አንድ ሕይወታቸውን ቤዛ በማድረግ መስዋእትነት የከፈሉት ለሕዝብ የገቡትን በአላማ በፅናት ያነገቡት ሕዝብ በነፃነት እንዲኖር፤ ሕግ ሁሉንም እኩል እንድታይ፤ማንም ኃይል ከሕግ በላይ እንዳልሆነ፤ማንም ሳይሸማቀቅ ያሻውን ሐሳብ በነጻነት እንዲናገር፤አገርና ሕዝብ እንዲበለጽግ ፤ረሀብ ከሰው ልጆች ጨርሶ እንዲርቅ፤ዴሞክራሲ በመላው ሀገር እንዲስፋፋ …ወዘተ ነበር የእነዚያ እውነተኛ ወያኔዎች አላማቸውና የተሰውለት ፅኑ መርህ::

እነዚያ እውነተኛና ለአላማቸው የፀኑ ወያኔዎች ለሕዝብ ነጻነት ታግለዋል:: ለሕዝብ እኩልነት ሲባል ቆስለዋል:: ለሕዝብ ሰላምና ዴሞክራሲ ሲባል ደምተዋል:: ለሕዝብ እኩልነት ሲባል አካላቸውን አጉድለዋል:: ለሕዝቦች አንድነት ሲባል ላባቸውን፣ ጉልበታቸውን ሳይሳሱ ሰጥተዋል:: እነዚያ አንዷን ሕይወታቸውን ሳይሳሱ የሰጡ እውነተኛ ወያኔዎች ሙስና አያውቁም:: ትግላቸው ለሙስና ለዝርፊያ አልነበረም:: ▶

በሰው ልጆች ላይ የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንዲፈፀም አልነበረም:: ለዚያም አልታገሉም:: በሕዝብ ላይ በደል አልሠሩም:: እንዲህ ዓይነት ክፉ ድርጊት በሕዝብ ላይ ለመፈፀም ለትግል አልወጡም:: በሕዝብ ላይ የሰብኣዊ መብት ጥሰት እንዲቆም ታገሉ እንጂ እንዲፈፀም አልተሰውም:: የእውነተኛ ወያኔዎች አላማና ምኞታቸው ለሰው ልጆች ሰብኣዊ ክብርና በሕግ መጠበቅ፤ ድህነትን ማጥፋት፤ዴሞክራሲን ማስፋፋት ነበር:: እውነተኛ ወያኔዎች ስልጣን ለሕዝብ ለመስጠት ተሰው እንጂ ፤ሥልጣን በማጭበርበርና በአምባገነንነት ለመያዝ አልነበረም:: እውነተኛ ወያኔዎች ሥልጣን ለሕዝብ አገልግሎት ማገልገያ እንጂ ከሥልጣን ጥቅማ ጥቅም ለመልቀም አልነበረም::

በቅርቡ ትግራይ በሄድኩበት ወቅት ከአንዲት እናት ጋር ስለ ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ ተጨዋውተን ነበር:: እሳቸው ሁለት ልጆቻቸውን ለትግል ልከው ሁለቱም ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ከመግባቱ ቀደም ብለው በትጥቅ ትግሉ መስዋእት ሆነዋል:: በአሁኑ ሰዐት ሁለት ልጆቻቸውን ያጡት እናት ብቻቸውን በችግር ውስጥ ይኖራሉ:: እና በጭውውታችን መሀል እንዲህ አሉ:: «አሁን እንደምንሰማው ከሆነ በመሀል አገርና በአማራ ክልል ያሉ አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወያኔ ወያኔ እያሉ ሁሉንም በጅምላ ስለ ወያኔ መጥፎ ነገር በስፋት እየተነገረ ነው:: በአሁኑ ሰዐት ወያኔ ማለት የመጥፎ ሥራ ማዛመጃ ሲሆን ይታያል:: ወያኔና ሌብነት፤ ወያኔና ዝርፍያ አንድ አካል አንድ አምሳል፤የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ሆኖ በስፋት እየተሳለ ነው:: እኔ ደግሞ እንዲህ ሆኖ ስሰማና ስመለከት ሐዘኔ እጥፍ ሆኗል:: ስለ እውነት ብለው መስዋእትነት የከፈሉት ሁለቱ ልጆቼ ማታ ማታ ይታዩኛል:: የታገሉለት ትግል በአንዳንድ ዘራፊዎች ምክንያት ወያኔነት በተቃራኒው ሲተረጎም ማታ ማታ ብቻዬን ሆኜ አለቅሳለሁ::" አሉኝ:: እኔም የእኚህን ምስኪን እናት በሀዘን የተሞላ ንግግር ውስጤን ተሰማኝ:: እውነታውና አሁን ያለው ሁኔታ አሳዘነኝ::

ሁለት ልጆቻቸው ወደ ትግል ልከው በድህነት የሚገኙት እናትን እኛ ትክክለኛ ትርጓሜ ባልሰጠነው የተሳሳተ አነጋገር እውነተኛ ወያኔዎችና ዘራፊ ወያኔዎችን በአግባቡ ሳንለይ ወይም ስያሜ ሳንሰጥ በምናደርገው ተስማሚ ያልሆነ አገላለፅ፤ እኚህን ምስኪን እናት ከድህነታቸው በላይ ማታ በሰላም እንዳይተኙ እንቅልፍ እየነሳናቸው ነው:: ይህን ምሳሌ በአንዲት እናት አቀረብኩት እንጂ፤ ለትክክለኛ ዓላማ መስዋእት የሆኑት የስድሳ ሺህ እናቶችን፤ አባቶችን፤ ወንድሞችን፤ እህቶችን፤ አክስቶችና አጎቶችን ከችግራቸው በላይ ባልተገባ ትርጓሜ ምሽት በሰላም እንዳይተኙ እያደረግን እንደሆነ ምን ያህሎቻችን ተረድተናል:: እባካችሁ ስንፅፍም ፤ስንናገርም ቃላቶች በሚገባ እንምረጥ:: ያጠፋን ለመገሰፅ ብለን ምንም ያላደረገውን ሀጥያተኛ አናድርግ፤

ካሁን ወዲያ ሌቦችን፤ ዘረኞችንና ጠባብ ብሔርተኞችን ወያኔ ብላችሁ አትጥሩ:: እነሱ ወያኔዎች አይደሉም:: ሌቦችና ዘራፊዎች፤ቀማኞችና ዘረኞች ናቸው:: ስለዚህ አካፋን አካፋ ማለት እንጂ የማይገባ ስያሜ ልንሰጥ አይገባም::

እነዚያ እውነተኛ ወያኔዎች መቐሌ በሚገኘው የሰማእታት ሀውልት ሥር መልእክታቸው እንዲህ ይላል "ክቡር ሕይወታችን የከፈልነው የማንንም ቀንበር ላንሸከም፤ ቀንበራችንንም በማንም ላይ ላለመጫን ነው" ይሉናል:: እነዚያ እውነተኛ ወያኔዎች የታገሉትና መስዋእት የሆኑት አገር ለመዝረፍ አይደለም:: መስዋእት የሆኑት ኢትዮጵያ የተሻለች አገር ለማድረግ ነው:: ማንም ጉልበተኛ ተነስቶ በሕዝብ ላይ ቀንበር እንዳይጭን ነበር:: እነዚያ እውነተኛ ወያኔዎች መስዋእት ሲሆኑ ለቀሪው አደራ ሰጥተው አልፈዋል:: አደራ መስጠትና መቀበል በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ክንውን ነው:: አደራ የተሰጣቸው ሰዎች አደራውን (ቃል ኪዳኑን) ጠብቀው አዘለቁት ወይም አደራው ተበላ ብሎ መጠየቅ ደግሞ የአባት ነው::

ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ ዓለም ከተፈጠረ በኂላ በፈጣሪና በፍጡር እንዲሁም በፍጡራን መካከል ቃልኪዳን ነበረ፤ ይላሉ የሃይማኖት ሊቃውንት:: ቃልኪዳን ማለት አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የሚፈፀም ቃለ መሀላ ሲሆን ውጤቱም በጥብቅ ሥነ ምግባር የሚመራ ነው:: መልካም ሥነ ምግባር ከመልካም ጠባይ ጋር ቁርኝት ያለው ይልቁንም በምንኖርበት ማኅበረሰብ እና የአኗኗር ሥርዓት ቃልኪዳን መጠበቅ እና አክብሮ ማድረስ የማኅበረሰባችን ትልቁ እሴት ነው:: በመስዋእትነት የታጀበ የአደራ አድርስልኝ ቃልኪዳን መዘንጋትና አደራን መብላት የማኅበረሰቡን ዕሴቶች ከአለማክበር ጋር ይያያዛል::

> "ሁሉንም ሰው ጥቂት ጊዜ ማታለል ይቻላል፤ጥቂት ሰዎችን ደግሞ ሁሉጊዜ ማታለል ይቻል ይሆናል፡፡ ሁሉንም ሰው ሁሉጊዜ ማታለል አይቻልም፡፡" ስለዚህ ካሁን ወዲያ በእውነተኞቹ ወያኔዎችና በዘራፊዎቹ ወያኔዎች መካከል ትልቅ የልዩነት ግንብ ሊገነባ ይገባል

መስዋእትነት የተከፈለበት አደራ ክቡር ነው:: በሀገራችን አደራ የበላ ሰው አገር መምራት ቀርቶ ለዋስትና አይበቃም፣ ለሽምግልና አይጋበዝም፣ በማኅበር የክብር ቦታ አይሰጠውም፣በእድር እንኳን ለመሪነት ቦታ አይታጭም። ይህ የቆየ የኢትዮጵያውያን ባህል ነው። አደራ አክባሪ ይከበራል ፣ሽማ ተደርቦለት የፊት ረድፉን እንዲመራ ይጋባዛል፣ ይመርቃል፣ ያስማማል፣ ያስታርቃል በኅብረተሰቡም ሆነ በመንግሥት ደረጃ የክብር ሥፍራን ያገኛል።


አደራው ታዲያ ከግለሰብ አልፎ የሕዝብ አደራ ከሆነ ሸክሙ በጣም ከበድ ይላል። ራስን ካላወቁ፣ የሚሰሩትን ነገር ካልተገነዘቡ፣ ሕዝብን ካልናቁ በስተቀር መስዋእትነት ከከፈሉ ወጣቶች የተቀበሉትን አደራ የትም አራግፎ መሄድ ዳፋው በቀላሉ የሚለቅ ዓይነት አይሆንም። የጀግኖች ሰማእታት ቃልኪዳን እና አደራ በአግባቡ አለመጠበቅ፤ ጠብቆ ከዳር አለማድረስ ሁሌ ከህሊና ጋር መጋጨት ይሆናል:: በእውነተኛ ወያኔዎች ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የፈሰሰው ደም ዛሬም የቃል ኪዳን ምላሽ አላገኘም። ሀገሬን፡ ሕዝቤን ብሎ ሕይወቱን፤ ደሙን ለሕዝብ መብትና ሥልጣን ሲል ያፈሰሰው እውነተኛው ትውልድ ምንጊዜም ሊታወስ፡ ሊዘከር ይገባዋል። ይህ ደግሞ ሁሌ ከንፈር እየመጠጡ ለማዘን ሳይሆን ማስተማሪያነቱ መቅደም ይኖርበታል። በተሰውት እውነተኛ ወያኔዎች ስም ዛሬ መቀለድ ሊቆም ይገባል:: ቃልኪዳናቸው ተቀብላችሁ አደራቸውን ዳር ካላደረሳችሁ በሰማይም በምድርም ትጠየቃላችሁ::

ስለዚህ ለብዙ ዘመናት ወያኔ በሚለው አሰያየም ላይ ሰፊ ልዩነት እንዳለ ዕያየን ቆይተናል:: በምግባርና በተግባር ወያኔዎች ሳይሆኑ ወያኔዎች ነን ሲሉ ህዝቡም አሜን ብሎ ቃልኪዳን ጠባቂዎች አደራ አድራሾች ናቸው ብሎ እስከ አሁን ተቀብሏቸዋል:: አብርሀም ሊንከን እንዲህ ይላል፡ "ሁሉንም ሰው ጥቂት ጊዜ ማታለል ይቻላል፤ጥቂት ሰዎችን ደግሞ ሁሉጊዜ ማታለል ይቻል ይሆናል:: ሁሉንም ሰው ሁሉጊዜ ማታለል አይቻልም::" ስለዚህ ካሁን ወዲያ በእውነተኞቹ ወያኔዎችና በዘራፊዎቹ ወያኔዎች መካከል ትልቅ የልዩነት ግንብ ሊገነባ ይገባል:: ስለእውነት ብለው የታገሉት አሁንም ድረስ በእውነት ላይ የቆሙትን እውነተኛ ወያኔዎች ናቸው:: ነገር ግን እነዚያ የሕዝብ ሀብት የዘረፉ ፤ሕዝብን ያሰቃዩ፤ የገደሉ ያሰደዱ፤ አካል ያጎደሉ ወያኔዎች አይደሉምና ሌላ ስያሜ ይፈለግላቸው:: በምግባርም በተግባርም ወያኔ ያልሆነውን ወያኔ እያልን ወያኔ የሚለውን ስያሜ የክፋት መገለጫ አድርጎ ማቅረብ የእውነተኛ ወያኔ እናቶችን እንቅልፍ መንሳትና ማስለቀስ ስለሚሆን ከዚህ እንጠንቀቅ እላለሁ::

ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር

# ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ

## የሚሺን 101 ዋና አዛዥ በኢትዮጵያ



ብሩክ መኮንን



ከግራ ወደ ቀኝ ውንጌት ኃይለሥላሴ እና ሳንፎርድ

በ1928 ዓ.ም የኢጣልያን ወረራ ተከትሎ በወገኖቻችን የደም መስዋዕትነት ሕይወታቸውን ከፍለው ካረጋገጡት ጥቂት የውጭ ሀገር ዜጎች ውስጥ አንዱ እንግሊዛዊው ብርጋዴር ጄነራል ሳንፎርድ ናቸው፡፡

እንግሊዛዊው ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ በጁን 1882 ዓ.ም በአንግሊዝ ታዋቂው የአዴንብራ ካቴድራልን በሊቀክህነት ከሚያገለግል ቤተሰብ የተገኙ ፣ከልጅነታቸው አንስቶ የእንግሊዝ ጦር ኃይል ባልደረባ በመሆን በተለያዩ የአለም ክፍሎች ያገለገሉ የጦር መኮንን ናቸው፡፡

ገና የአንደኛው የአለም ጦርነት ሳይፈነዳ ከሀገራቸው ወደ ኤዢያና አፍሪካ በመጓዝ፣ በሕንድና በሱዳን በተለያዩ የስራ ኃላፊነቶች ተመድበው ያገለገሉት ዳንኤል ሳንፎርድ በ1907 ዓ.ም ነበር ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ የመጎብኘት ዕድል የገጠማቸው፡፡

ከሰባት አመት በኋላ በ1914 ዓ.ም በኢትዮጵያ የብሪታኒያ ሌጋሲዮን ቆንስላ በመሆን ተመድበው ለአንድ አመት ያህል ሀገራቸውን ያገለገሉት ዳንኤል ሳንፎርድ፣ የአንደኛው የአለም ጦርነት መቀስቀስን ተከትሎ ወደ እንግሊዝ የጦር ኃይልን ደግሞ ተቀላቅለው እንዲዘምቱ በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት፣ በምዕራብ ፈረንሳይ ይካሄድ በነበረ ጦርነት በፌብሩዋሪ 1915 ጀምሮ በግዳጅ ላይ  ተሰማርተው፣ በሜይ በ1916 በሻለቃነት ማዕረግ አግኝተው፣ የ94ኛው ሻለቃ አዛዥ በመሆን ፣እስከ ጦርነቱ ማብቃት ድረስ በግዳጅ ላይ ቆይተዋል፡፡ ከሴፕቴምበር 1918 ድረስ በሠራዊቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ኃላፊነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ራሳቸውን ከሰራዊቱ በማግለል ወደ ምስራቅ አፍሪካ በማምራት ከ1920 ጀምሮ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ አማካሪ በመሆን የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀጣሪ በመሆን አገልግሎ ይሰጡ ጀመር፡፡

ለቀዳማዊ ኃይለስላሴ አማካሪ በመሆን በተለይ ደግሞ በምዕራብ ኢትዮጵያ በስፋት ይስተዋል የነበረውን ሕገወጥ የዝሆን ጥርስ ንግድና አደን እንዲሁም የባሪያ ንግድን ለማስቆም በተደረገ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ የነበራቸው ዳንኤል ሳንፎርድ ኢጣልያ በ1928 ዳግም ኢትዮጵያን እስከወረረችበት ወቅት ድረስ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት አማካሪነት ሥራቸውን ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ የጦርነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠባባሰ መምጣትን ተከትሎ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

የማይጨው ጦርነትን ተከትሎ ኢትዮጵያን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገው የኢጣልያ ፋሽስት ጦር በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል ለአለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማጋለጥና በስደት የዲፕሎማሲያዊ ትግል ለማድረግ ወደ እንግሊዝ የተሰደዱት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን በስደት በሚኖሩበት ባዝ የተባለ ስፍራ በመሄድ አግኝተዋቸው በተለያዩ መንገዶች የኢትዮጵያና ሕዝብዋ ከኢጣልያ የግፍ አገዛዝ ለመላቀቅ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማገዝ ፈቃደኝነታቸውን ገለፁላቸው፡፡

በኦገስት 1939 ተቀማጭነታቸውን በካይሮ ያደረጉት የእንግሊዝ ጦር የመካከለኛው ምስራቅ ዋና አዛዥ ጄነራል ስር አርኪባልድ ዌቭል ዳንኤል ሳንፎርድ በኮሎኔልነት ማዕረግ በምስራቅ አፍሪካ ወታደራዊ ደህንነት ክፍልን በአዛዥነት እንዲመሩ መደባቸው፡፡

ኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድ ከእንግሊዝ ወደ ካይሮ በማምራት በምስራቅ አፍሪካ በተለይ በኢትዮጵያና በአጎራባች ሀገሮች በኢጣልያና በአጋርዋ በጀርመን የጦር ኃይል የበላይነት አሸናፊ ሆና የምትወጣበትን መንገድ ለማመቻቸት ሊወስዱ የሚገባቸውን እርምጃዎችን በዝርዝር ለማጥናት ተልዕኮን ተቀብለው ወደ ሱዳን አቀና፡፡

ኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድ በምስራቅ አፍሪካ ያደረገውን ጉዞ አጠናቆ ሲመለስ ለአለቆቹ ባቀረበው ጥናት ኢትዮጵያን በኃይል የያዘው የኢጣልያ ጦር ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ኢትዮጵያውያን የሽምቅ ተዋጊዎችን ማስታጠቅ እንዲሁም አደራጅቶ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ማድረግ ተገቢነቱን አስገነዘበ፡፡

ይህንን መሰሉን የሽምቅ ውጊያ ለማካሄድ ብቁ ናቸው የተባሉ ኢትዮጵያውን አርበኞች ካቀፉ ቡድኖች ጋራ ግንኙነት መፈጠር እንዲሁም ለነዚህ በሽምቅ ተዋጊነት የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን ለማስታጠቅ ፣ለማደራጀት፣ እንቅስቃሴያቸውን ለማቀናጀት፣ ሚሺን 101 የተባለ በአንግሊዝ ጦር ኃይል አመራር የሚሰጥ ተልዕኮ ሊቋቋም ሥራ ሊጀምር ይገባል የሚል ድምዳሜን የያዘ ምክረ ሃሳብ አቀረበ፡፡

በመረጃ ባለሙያነቱ በጦር ስልት አዋቂነቱ የሚተማመኑ የእንግሊዝ ከፍተኛ የጦር አዛዦች ኮሎኔል ሳንፎርድ ያቀረበውን ምክረ ሀሳብ በመቀበል ይህ ሚሽን 101 የተባለው ቡድን በራሱ አመራር ስር እንዲዋቀር በአስቸኳይ ስራ እንዲጀምር ያደርግ ዘንድ መመሪያ ሰጡ፡፡

ዊንስተን ቸርችልና የጦር ሚኒስትር አድርገው የሾሙትአንቶኒ ኤን ከጀርመን ጋራ ያበረችው ፋሺስት ኢጣልያ፣ ጦሯ ተሸንፎ ከምስራቅ አፍሪካ እንዲወጣና በስዊስ ካናል እና በባቤል መንደብ መተላለፊያ ሰርጥ ሙሉ ለሙሉ በእንግሊዝ እና በአጋሮቿዋ ቁጥጥር ስር መውደቅ አለበት የሚል አቋም ያራምዱ ስለነበር ለኮሎኔል ዳንኤል ሳንድ ፎርድን ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቶ በአስቸኳይ በሥራ ላይ እንዲውል  ይወተውቱ ጀመር፡፡

ወደ ሰዳን ያመሩት ኃይለ ስላሴ በጊዜው በሱዳን ጠቅላይ ገዢ ሰር ስቲዋረ ሳይመንስ ተገቢውን አቀባበልና ትብብር ነፈገዋቸው በወዲ ሐልፋ በተባለ ስፍራ የእንግዳ ማቆያ እንዲያርፍ መደረጉን የሰማው ኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድ ጊዜ ሳይፈጅ ሌት ተቀን ተጉዞ በወዲ ሐይፋ በማምራት ለቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ያለውን መልካም ምኞት ገለፀ፡፡

ኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድ በወዲ ሰልፍ ከንጉሰ ነገስቱ ከሎሬንሶ ትዕዛዝ መብራቱ ከአዛዥ ከበደ ተሰማ (በኋላ ደጃዝማች) እና ከሌሎች የንጉሱ ተከታዮች ጋራ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከመከረ በኋላ በራሱ አዛዥነት የሚመራው ‹‹ሚሺን 101›› የተባለውን ተልዕኮ እና የዘመቻ መርሃ ግብርን በተመለከተ ሰፊ የሆነ ገለፃ አደረገላቸው፡፡

በወቅቱ የነበረውን ስሜት በተመለከተ ከጦርነቱ በኋላ ስለሁኔታው የተጠየቀው አንድሪው ቻፕማን አንድሪውስ ‹‹ የእንግሊዝ መንግስት ኢትዮጵያን ከኢጣልያች ነፃ ለማውጣት ለሚካሄደው ዘመቻ ማካሄጃያ የመደበው የጦር መሳሪያ ጥይቶች እና ፀረ ታንክና የአየር መቃወሚያ መትረየሶች ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና በእርጅና ለብልሽት የተዳረጉ የመሆናቸው ሪፖርት ሲሰሙ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከለንደን ወደ ሱዳን የመጡበትን አጋጣሚ ሲረግሙና እንደተሳሳቱ ለማሰብ ተገደው ነበር ›› ብሏል፡፡

ኮሎኔል ዳንኤል ሳንድፎድ የጠላትን አጠቃላይ አቋም ስትራቴጂ ለማጥናት በጎጃም እና በዙሪያዋ ያሉ አርበኞችን ለማበረታትና ለኢጣልያ አድርገው የነበሩ ባንዳዎች ጣልያን ከድተው ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋራ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ አዛዥ ከበደ ተሰማ ሎሬንሶ ትዕዛዝ መብራቱ ጋራ ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ጋራ በመሆን በድብቅ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቀው በመግባት እጅግ አደገኛውን ተልዕኮ አንድ ብለው ጀመሩ፡፡

ዳንኤል ሳንፎርድ፣ ከነሎሬንሶ ትዕዛዝ መብራቱ ከነአዛዥ ከበደ ተሰማ ጋራ በሕዕቡ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በአስቸጋሪ መልክአምድር የተሸፈነውን የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያን ግዛት ሲዘልቅ ግንኙነት ለመመስረት ከቻሉ ኢትዮጵያውያን አርበኞች፣ የንጉሰ ነገስቱ በእንግሊዝ መንግስት ድጋፍ ወደ ሀገራቸው በነፃ አውጭነት ለመፋለም የመምጣት ዜና የሰሙ ወገኖች በሙሉ መልካም መስተንግዶ ያደረጉለት ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥም የኢጣልያን ጦር የግንኙነት መስመሮች ማቋረጥ የስንቅና ትጥቅ ማከመቻ መጋዘኖች ማጋየት፣ በጦር ሰፈር ላይ ድንገተኛ ማጥቃት ተልዕኮችን ግዳጅ ተቀብለው በስራ ላይ እንዲውል አደረጉ፡፡

ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ የያኔው ኮሎኔል በጎጃም ጠቅላይ ግዛት የሚንቀሳቀሱት ከኢትዮጵያውን አርበኞች ጋራ ለመመስረት ያቀዱት ግነኙነትን ሀ ብለው የጀመሩት ከፊታውራሪ አየለ መኮንን ጋራ ሲሆን በመቀጠል ከደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ጋራ ነበር፡፡

ፊታውራሪ አየለ መኮንን የሚሽን 101 ግብረሃይልን እንቅስቃሴ ለመግታት  የዘመተው የኢጣልያ ጦር ላይ ከጀርባ ጥቃተ በመሰንዘር ለኮሎኔል ዳንኤል ሳንድፎድ የተመራው የ101 ሚሽን ግብረ ሃይል ከጥቃቱ አምልጦ ጉዞውን እንዲቀጥል ሲያደርጉ ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ የሚታዘዘው የጎጃም አርበኞች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ለሞት የተዳረጉ የግብረ ሃይሉ መጓጓዣ የሆኑ በቅሎዎች ፈረሶችን እንዲሁም አጃቢና መንገድ መሪ ኃይል በመላክ በኢጣልያ ጦር ላይ የተጀመረውን የነፃነት ትግል የመጀመሪያ ምዕራፍ አስተማማኝ ደረጃ ላይ አንዲደርስ አድርጓል፡፡ ሲሉ የኮሎኔል ሳንፎርድ ባለቤት The Lion of Judaj Hath preuailed ስለ ባለቤታቸው እና የቤተሰባቸው እና የቤተሰባቸው ታሪክ ላይ ያተኮረ መፅሀፍ ላይ ባለቤታቸውን በመግለፅ አስፍረዋል፡፡

የኮሎኔል ዳንኤል ሳንድፎድ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጎጃም አርበኞች ማዕከል ያለውን የአለመግባባት እልባት እንዲያገኝና በአንድነት በጠላት ጦር ላይ እንዲዘምቱ ለማስተባበር ያደረጉት ጥረት ወዲያው ነበር ውጤታማ የሆነው፣ በወቅቱ በዚሁ ግዳጅ ላይ ለተሰማራው የእንግሊዝ ጦር እና የሚሺን 101 ግብረ ሃይል ቀለብ እና የሥራ ማስኬጂያ ገንዘብ እጥረት ሲከሰት ከአርበኛው ከደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ የ3ሺህ ማርያ ትሬዛ የመቀበል አመኔታ እና ቀረቤታ ለመመስረት ያስቻለችው ወዳጅነት እንግሊዛዊው ኮሎኔል አፍርተው ነበር፣ ሲሉ ስለ ወቅቱ ሁኔታ የሚያወሱ መዛግብት ይመስክራሉ፡፡

ኢትዮጵያን ከኢጣልያን ወረራ ነፃ ለማውጣት የተጀመረውን እንቅስቃሴ ለማቀላጠፍ የጌዲዮን ጦርን በዋና አዝማችነት እየመራ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ኦርድ ዊንጌት አጠቃላይ የጦር እንቅስቃሴውን ማስተባበር ለኢትዮጵያውን አርበኞች የትጥቅ የስንቅ እንኳ በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአርበኞች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ አመራር መስጠት ሲጀምር ኮሎኔል ዳንኤል ሳንፎርድ በብርጋዴር ጄነራልነት ማዕረግ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት የፖለቲካ አማካሪ ሆነው እንዲሰሩ ተመደቡ፡፡

በፀረ ፋሽስት ትግሉ ወቅት ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ በወቅቱ ኢትዮጵያ አገዛዝ ነፃ ብትወጣም በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ስር መቆየት አለባት እንጂ ከስደት የተመለሱት ንጉሰ ነገስቱ የሚመሩት የሚቆጣጠሩት መንግስት ስልጣን ሊይዝ አይገባም የሚል አቋም የሚያራምዱ እንግሊዛውያን ሹሞችን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ሲሞክሩ በተደጋጋሚ ከአዛዥ ከበደ ተሰማ ከአቶ ጌታሁን ተሰማ ከሎሬንሶ ትዕዛዝ መብራቱ ጋራ አለመግባባትና ቅራኔ ያበቃቸው እንደነበር ይህ አቋም ግን ወደ ኋላ መቀየራቸውን በጊዜው የነበረውን እውነታ የሚያወሱ መፅሐፍጽና መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ እንደ ዊንጌት፣ እንደ ጆርጅ ስቲር፣ ኤሪክ ቨርጂን ሁሉ ኢትዮጵያን ከፋሽስት አገዛዝ ለማላቀቅ በተደረገ የነጻነት ትግል ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ስማቸውን በሀገራችን ታሪክ ምዕራፍ ውስጥ  ያሰፈሩ የሀራችን ባለውለተኛ እንግሊዛዊ የጦር መኮንን ናቸው፡፡

በሚያዚያ 27 ቀን 1933  ኢትዮጵያ ከኢጣልያን ጦር ቁጥጥር ስር ነፃ ስትወጣ እንደ ደብረማርቆሱ ኦሜሮላ ሁሉ በአዲስ አበባም ከቀዳማዊ ኃ/ስላሴ  ጋራ በመሆን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በክብር ኮራ ብሎ እንዲውለበለብ በተደረገበት ስነ ስርዓት ላይ ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ ከሌሎች ኢትዮጵያውን አርበኞች ጋራ የነፃነትን ዋጋ ውጤት ለማየት ችለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ነፃነት እውን ከሆነ በኋላም ከእንግሊዝ ጦር ከእንግሊዝ መንግስት ባልደረባነት ራሳቸውን በጡረታ ያገለሉት ብርጋዴር ጄነራል ሳንፎርድ በተለያዩ መንግስታዊ ኃላፊነቶች ተመድበው የኢትዮጵያን መንግስት አገልግለዋል እስከ 1951 እ.ኤ.አ ጊዜ ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዳይሬክተር ጄነራል በመሆን ያገለገሉት ዳንኤል ሳንፎርድ ከኢትዮጵያ መንግስት ሥራ ጡረታ በመውጣት ቀደም ሲል በቀ.ኃ.ስ የተሰጣቸው የነበረው ከአዲስ አበባ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ደርባ ላይ በሚገኝ ስፍራ የወተት ላም ርቢ እንዲሁም በተለያዩ የእርሻ ዘርፎች፣ በቡና እና በአትክልትና ፍራፍሬዎች እርሻ ሥራ ላይ በመሰማራት የግል ሥራቸውን ሲያካሄዱ ቆይተዋል፡፡

በባለቤታቸው በክርስቲን ሳንፎርድና በሌሎች የቤተሰብ አባላት ይተዳደር የነበረውንና መጀመሪያ በብሪቲሽ ካውንስል ትምህርት መስጠጥ የጀመረውና በኋላ ላይ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት በመባል የሚጠራው የግል ትምህርት ቤት አቋቁመዋል፡፡ ይህ ትምህርት ቤት በዚህ ዘመንም በኢትዮጵያ አሉ ከሚባሉ የአለም አቀፍ ማኅበረሰብ ልጆቹን ከሚያስተምርባቸው ምርጥ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ በመሆን አገልግሎትን እየሰጠ ይገኛል፡፡

ብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ ገና በወጣትነት ዘመናቸው ጎብኝተዋት በወደዷት እና ሕይወቴንም ቢሆን እሰጣታለሁ ሲሉ በተደጋጋሚ ይናገሩለት በነበረችው በኢትዮጵያ በ1972 ዓ.ም በዘጠና አመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለዩ፡፡

ከአመታት በኋላ የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት በደርግ መንግሥት በወሎ የሚገኘውን የብርጋዴር ጄነራል ሳንፎርድ የወተት ከብቶች እርባታን በዚያ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ወርሶ ለመንግስት አድርጎት የወተት ላሞች እርባታውን ለመቀጠል ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል፡፡

አሁን ከአመታት በኋላ ለአንድ የሆላንድ ኩባኒያ በአበባ እርሻ ልማት ማካሄጃያ የተከራየው የብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ የእርሻ መሬት ላይ የሚገኘው ዕድሜ ጠገቡ ቤት የቀድሞ ይዘቱን ሳይለቅ በመታደስ ላይ ይገኛል፡፡

ግዮን መጽሔትም ለአያሌ አመታት ኢትዮጵያውያንን እና ኢትዮጵያውን ያገለገሉ ባለ ውለታ የውጭ ሀገር ዜጎች ተርታ የሚመደቡትን ከብርጋዴር ጄነራል ዳንኤል ሳንፎርድ የዘከርንበትን ዳሰሳ እዚህ ላይ አበቃን ቸር እንሰብት፡፡

# አነግ የማን . . .

*ከገጽ 16 የዞረ*

**ሌንጮ:-** ዶ/ር ዐቢይ የኢትዮጵያ መሪ ነው:: የኢትዮጵያ መሪ በመሆኑ የኦሮሞ መሪ ብቻ እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ትክክል አይደለም:: የኦሮሞ መሪ አሁን ለማ ነው:: ለማ መገርሳ ደግሞ በእኔ ዕይታ ጥሩ እየሰራ ነው:: ሥራ ይበዛበታል፣ ዕንቅፋቶቹ ብዙ ናቸው ግን ጥረቱ የሚደገፍና የሚደነቅ ነው::

ሁላችንም ይሄንን ጥረትና ለውጥ ደግፈን ሁኔታዎችን የበለጠ በማሻሻል ከድህነት እንድንወጣ ማድረግ ይጠበቅብናል:: እዚህ ላይ መረባረብ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ::

**ግዮን:- ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ከአማራ፣ ከደቡብና ከአዲስ አበባ ሙሉ ድጋፍ ሲያገኙ ከኦሮሞ ህዝብ አብላጫውን ድጋፍ ያላገኙት በምን ምክንያት ይመስልዎታል?**

**ሌንጮ:-** ይሄን ለማለት ጥናት አካሂዳሃል ?.... በምን አውቀህ፣ ርግጠኛ ሆነህ ለመናገር ቻልክ?

**ግዮን:- ጠ/ሚ/ሩ የተለያዩ የኦሮሞ ሽማግሌዎችንና አባገዳዎችን ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት በጠቀሷቸው የኦሮሞ ክልል ቦታዎች ላይ ቢሄዱ ለመገደል ሊበቁ እንደሚችሉ ጭምር በግልፅ ያለውን እውነታ ማንፀባረቃቸው የሚያመለክተው እኮ ብዙ ነገር አለ::**

**ሌንጮ:-** ያን ጊዜ በርግጥ እንዳልከው ዓይነት ነገር ቢናገሩም ማን ለህይወታቸው እንደሚያሰጋቸው ግን ግልፅ አላደረጉም:: ጥቃቱ ከብዙ አቅጣጫ የሚሰነዘር ሊሆን ስለሚችል፣ በደፈናው እንደዛ ዓይነቱ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይከብዳል::

**ግዮን:- ቀጣዩ የምርጫ ጊዜ መራዘም አለበት ይላሉ ወይስ ሀገሪቷ እንዲህ ባለ ግጭትና ግርግር ውስጥ ሆና ምርጫው መካሄድ አለበት ብለው ያምናሉ?**

**ሌንጮ:-** ይሄን በተመለከተ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጠቅላላ እየተወያዩበት ነው ያለው:: አንደኛ ነገር እኔ ብቻዬን ስለማልወዳደር ፓርቲዎች የሚደርሱበት የትኛውም ውሳኔ ይስማማኛል:: ይሄ ሁሉንም ፓርቲ የሚመለከት ጉዳይ ነው::

**ግዮን:- እርስዎ በምርጫ የማይወዳደሩት ለምንድን ነው?**

**ሌንጮ:-** እኔ ጡረታ ወጥቻለሁ:: ከኦዴግ (ኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር) ኃላፊነት ለቅቄያለሁ:: ማድረግ ያለብኝን ሁሉ አድርጌ አሁን በአባልነት ነው እየተንቀሳቀስኩ ነው::

**ግዮን:- በኦሮምያ ዙሪያ በሚፈጠሩ ችግሮች ላይ እንደ እናንተ ዓይነት አንጋፋ ሰዎች ፊት ለፊት ወጥታችሁ ድርጊቱን ስትቃወሙ አስተያየት ስትሰጡ አትታዩም ለምንድን ነው?**

**ሌንጮ:-** ብዙ ጊዜ መልዕክት አስተላልፈናል:: ከለውጡ በኋላ::.... በኦሮምኛ ስለሆነ አትከታተልም ማለት ነው::

**ግዮን:- እንግዲያው በዚህ አጋጣሚ በአማርኛ መልዕክትዎን ለአንባቢያ ያድርሱልን?**

**ሌንጮ:-** ኢትዮጵያ በአሁን ሰዓት በጣም ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ላይ ትገኛለች:: በሌላ መልኩ ደግሞ ካየነው በጣም አስጊ ሁኔታ ላይ ነው የምንገኘው:: አሁን ተጋግዘን ወደ



ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምንሸጋገርበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው፤ ማንም ኢትዮጵያዊ ተግቶ እንዲሰራ ነው በዚህ አጋጣሚ መልዕክቴን የማስተላልፈው::

**ግዮን:- የሕወሓት መንግስት ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ ምን ጥሩ ነገር፣ ምን መጥፎ ነገር ሠራ? ይሄን ቢገልፁልን?**

**ሌንጮ:-** በእነዛ ሀያ ሰባት ዓመታት ውስጥ ጥፋትም ተሠርቷል፤ ደህናም ነገር ተሰርቷል:: በሙስና ባይጨማለቅ ኖሮ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል የተደረገው ሥራ ጥሩ ነበር፤ ት/ቤቶች መስፋፋታቸው፣ ኢንቨስትመንት መስፋፋታቸው የሥርዓቱ አዎንታዊ ጎን ነው ብዬ ነው የማምነው::በአሉታዊ ጎኑ ደግሞ የሙስና ከመጠን በላይ መንሰራፋት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝሮ አያልቅም::

**ግዮን:- በእነዛ አመታት የአንድ ብሔር የበላይነትና ተጠቃሚነት ነበር ማለት ይቻላል?**

ሌንጮ:- የአንድ ብሔር የበላይነት ሳይሆን የአንድ ድርጅት የበላይነት ነው የነበረው፤ ሕወሓት በኢህአዴግ ላይ የነበረው ተፅዕኖ በጣም ከፍተኛ ነበር:: ሌሎች ሶስቱ ድርጅቶች (ብአዴን፣ ኦህዴድና ደህዴን) እሱ የፈጠራቸውና በሚመቸው መልኩ ያዘጋጃቸው ስለነበሩ የሆነው ነገር በሙሉ የሚደንቅ አይደለም::

**ግዮን:- ሕወሓት በኢትዮጵያ ውስጥ ካመጣው ለውጥ ገለል ካለ በኋላ ትግራይን እንደ ሀገር ይዞ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ያዋጣዋል ይላሉ?**

**ሌንጮ:-** ትግራይን እንደ ሀገር ማየታቸውን እኔ አላውቅም:: ከሕወሓት መሪዎች ጋር በአሁኑ ሰዓት እነጋገራለሁ፣ እንደዛ ዓይነት ዕቅድ እንዳላቸው ግን አልነገሩኝም:: በዚህ ላይ የተለየ ሀሳብ የለኝም::

**ግዮን:- ሕወሓቶች እኮ ለውጡ ላይ የሉበትም፣ የሚያደርጉትም እንቅስቃሴ ዓላማ እና ሀሳባቸውን የሚገልፅ ነው::**

**ሌንጮ:-** ለውጡን የሚቃወሙ ወይንም ለውጡን የሚደግፉ በአራቱም የኢህአዴግ ድርጅቶች ውስጥ አሉ:: ሕወሓትን ልዩ የሚያደርገው ነገር ለእኔ እዚህ ላይ የለም::

**ግዮን:- ብዙ ጊዜ "ሕወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ ናቸው" እያለ ድርጅቱ የሚያናፍሰውስ እንዴት ይታያል?**

**ሌንጮ:-** ይሄ ስህተት ነው:: በፍፁም እኔ ይሄን አልቀበለውም:: እንደውም አደገኛ ነገር ነው፣ የትግራይ ሕዝብ በጣም አደገኛ ነው:: እንደዛ ባይሉ ይሻላል::

**ግዮን:- ከኤርትራ ጋር የተፈጠረውን ስምምነት ተከትሎ የሕወሓት ተሸናፊነትና የሻዕቢያ አሸናፊነት ይታያል፤ ሁለቱ ድርጅቶች ሥልጣን ላይ ቢቆዩ ኖሮ እርቀ ሰላሙ አይፈጠርም ነበር ይባላል::**

**ሌንጮ:-** አንደኛ ነገር በሁለቱ ሀገሮች መሀል መጠላቱ መፈጠር አልነበረበትም:: ሁለተኛ የአልጀርሱን ስምምነት መከተል የኢትዮጵያ ኃላፊነት ነበር:: የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ እስከተቀበሉ ድረስ:: ያንን ሥራ ላይ ማዋል ነበረባቸው:: ብዙ አመነቱ፤ መጨረሻ ላይ ኢህአዴግ ራሱ ወስኖ ባድመን ለኤርትራ ሰጥቶ ሠላም ወርዷል::

ይሄ ሠላም በዚህ ብቻ መቆም የለበትም:: ሥርዓት እንዲሟለለት፣ ሁለተኛ ድንበር ከመገንባት ህብረት መፍጠሩ ይሻላል:: ኢትዮጵያንና ኤርትራን የሚያገናኛቸው የታሪክ፣ የአኗኗር፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል ጉዳዮችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ የበለጠ የተሻለ ግንኙነት እንዲኖር ተግተን ከሰራን ሁለቱ ህዝቦች አብሮ ለመኖር ፈፅሞ ችግር የለባቸውም::

**ግዮን:- ከኤርትራ መገንጠል በፊት አማራጭ ወደቦች የነበሯት ኢትዮጵያ አሁን ወደብ አልባ ሀገር መሆኗ በቀጣይ ሂደት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ምንድን ነው?**

**ሌንጮ:-** ይሄ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው:: የግዴታ ወደቡን እንደገና በሆነ ሁኔታ ማግኘቱ ሳይሆን አንዱ ያለውን ጥሩ ነገር እንዴት ባለ መልኩ ልንጠቀምበት እንችላለን? የሚለውን ነው ማየት ያለብን:: ይህ ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ ኢንተግሬት በማድረግ መፈታት የሚችል ጉዳይ ይመስለኛል::

ለምሳሌ አንዳንዶች ወደቦች በቂ አገልግሎት ስለማይሰጡ ለሌላ መሸጥ ተጀምሯል:: ለሌላ ከሚሸጥ እዚሁ እኛ የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች አዋጥተን፣ የጋራ የሆነ ኮርፕሬሽን ተፈጥሮ በዚያ በኩል ማኔጅ እየተደረገ ለሁሉም ክፍት ቢሆን ይሻላል:: ይጠቅማልም የሚል ዕምነት አለኝ::ይሄ ነገር የፖለቲከኛ ሥራ አይደለም፤ ከዛ ውጪ ነው፣ በሽምግልና ኮሚቴዎች የሚሰራ ነገር ነው::

**ግዮን:- አሁን ከኦዴግ አመራርነት ጡረታ ወጥተዋልና ከዚህ በኋላ በምንድን ነው የምናገኝዎት?**

**ሌንጮ:-** ቁጭ ብዬ ልጆችን መምከር ነው የእኔ ሥራ የሚሆነው:: በፖለቲካው ዘርፍ ማድረግ ያለብኝን ነገር ሁሉ አድርጌ የምችለውን ሠርቻለሁ::

**ግዮን:- እናመሰግናለን::**

# “የኢትዮጵያዊነት እንጂ. . .

ከገጽ 10 የዞረ

ኢትዮጵያ ሲባል ያንዘረዝረዋል:: የተለየ ስሜትና ፍቅር ነው ያለው:: ድህነቱ አይደለም ትዝ የሚለው፣ ማንነቱ ነው ትዝ የሚለው:: የአሁኑ ግን አንደኛ ኢትዮጵያ የሚለውን ነገር ከኢኮኖሚ ጋር ያይዛል፤ ሌሎች ሀገሮች በቴክኖሎጂ በልፅገዋል፣ አድገዋል፣ በፍትህ፣ በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር በመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ የተመቸ ሥርዓት ፈጥረው በተለይ በኢኮኖሚው ከፍ ብለዋል:: ይህቺ ሀገር ግን በኢኮኖሚው ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰባት ነው የሄደችው፣ ስለ እዚህ ድህነቷ የገዘፈ፣ ሠርቶ የማይቻልበት ሀገር ስለሆነች፣ በሱዳንም ያስኬደው በምንም መሰደዱን ነው የሚመርጠው:: ወንዱም፣ሴቷም::

ይሄ ትውልድ ኢኮኖሚውን ብቻ ነው የሚመለከተው፣ የኋላ ታሪክ፣ ማንነቱን ፈፅሞ አያይም:: ሁለተኛ ደግሞ የተሰራበት ስራ ነው:: ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያዊነቱን እንዲያውቅ ሳይሆን የተደረገው፣ የብሔር ማንነቱን እንዲያውቅ ብቻ ነው በጥልቀት የተሰራበት:: የኦሮሞ ወጣት ኦሮሞነቱን ብቻ እንዲያስብ፤ ያ ወጣት አስቀድሞ ያንን ነገር ከወሰደና ከተቀበለ፣ ለእሱ ኢትዮጵያዊነት ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የአማራው ወጣት አማራነቱ፣ የትግሬውም ወጣት ትግሬነቱን ብቻ እንዲያተኩር ካደረግክ ኢትዮጵያን በምን ሊያውቃት ይችላል?

ሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በትክክል ኢትዮጵያን አጉልቶ የሚያሳይ ነገር አለ? ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት ማለት ነው:: ስለዚህ ብሔሩንና የተወሰኑ የአካባቢ ማንነቱን ብቻ እንዲያውቅ ተፅዕኖ የተደረገበት መንገድና ኢትዮጵያዊነት ምንም ትርጉም የማይሰጠው መሆኑ በራሱ ትልቅ ችግር ነው:: ከዛ ውጭ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ የሚያደርጉ ነገሮች እየወደቁ፣ እየወደቁ መሄዳቸው ሌላው ዋነኛ ችግር ነው:: ባለፉ 27 ዓመታት እኔም አንተም ኢትዮጵያ ያልንበትን አጋጣሚ እንውሰድ እስኪ፤ አትሌቶቻችን ሲያሸንፉ፣ ስሜት ይዞን ያኔ የሚመጣልን ኩራት የተለየ ስለሆነ ነው በእነዛ ወቅቶች ብቻ ኢትዮጵያዊነትን የምናስበው::

ከዛ ውጭ ብንመለከት ኢትዮጵያዊነትን ከፍ የሚያደርግ ቴአትር የለም:: በሙዚቃውም ብትስወድ አልፎ አልፎ የሚችሉትን ደፍረው የገቡ ናቸው ኢትዮጵያዊነትን ሲያቀነቅኑ የነበሩት:: በሲኒማ፣ በሥነ ስዕልና መሰል ዘርፎች ይህቺ ሀገር አልተንፀባረቀችም:: ይህ በሆነበት መልኩ የዘመኑ ትውልድ በምን ይወቃት? ኢትዮጵያዊነት አንዲት ሹራብ ወይም ነጠላ ለብሶ ‹‹ኧረ ና ዳኘው!›› እያሉ መዝፈን አይደለም:: የክልል ሰንደቅ ዓላማ አይነትን በጥበብ አጊጠህ ለብቻህ መጨፈር አይደለም ዋናው ነገር፣ አንድ የሚያደርገንን ነገር ስነ ጥበቡ ረስቶታል::

**ግዮን፡- የማህበራዊ ድህረ ገጾችስ እዚህ ላይ አስተዋፅኦ የላቸውም?**

**ረ/ፐ/ር አበባው፡-** በደንብ አላቸው:: በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚወጡት ጽሑፎች አንዱ አንዱን እንዲጠራጠር አድርጎታል:: በብሔር መከፋፈሉ እንዲንሰራፋና በፍጥነት እንዲረገብ አይነተኛ ሚና ተጫውቷል::



**ግዮን፡- ከብሔር ልዩነት ብንነሳ ዞሮ ዞሮ አንድ የሚያደርገን ኢትዮጵያዊነቱ ነውና “የነፃ ደም” አለ? ኦሮሞ ብቻ ወይም አማራ ብቻ የሚባል ነገርስ አለ?**

**ረ/ፐ/ር አበባው፡-** በምንም ተዓምር የለም:: ግልፅ ለማስቀመጥ እንውሰድና አደሬ አካባቢ ስትሄድ ከሃይማኖትና ትንሽም ከባህል ጋር ተያይዞ “ከሌላ አልጋባም፣ ከራሴ ዘር ወይም ነገድ ጋር ነው የምጋባው” የሚል ነገር አለ:: እንደዛም ሆኖ እኮ ጥሶ ይወጣል:: ከዛ ውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ግን በመሳፍንቱ ዘመን እንኳ ብንወስድ፣ የተንቤን ደጃዝማች ከሆነ ወደ አጋሜ ሄዶ ያገባል፣ ሰቆጣ ወይንም ሰሜን ጎንደር አቻውን ፈልጎ ይጋባል:: አቻነቱን ነው እንጂ የሚያየው ደሙን አይደለም የሚቆጥረው::

ለምሳሌ ነገስታትን ውሰድ:: ሰለሞናውያን የአማራ ስርወ መንግስት የምንለው ከየት ነው የሚጋቡት? አፄ ዮሐንስን ብናይ አንደኛዋ ሚስታቸው ወ/ሮ ሐሊማ ነች:: ወ/ሮ ሐሊማን ከአፋር ነው የወሰዷት:: በሃይማኖቱ በኩል ክርስቲያን አድርገው ያገባሉ፤ ባላባቶችን እንኳን ብንወስድ በስም የተንቤን ገዢ፣ የወገራ ገዢ ፣ትላለህ እንጂ በደም እያንዳንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰረ ነው:: ንፁህ ደም የለም::

ባላገሩን እንውሰድ ያው አማራ የሚኖርበት አካባቢ ያለው ትንሽ ለየት ይላል እንጂ፤ የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ወታደር ሆኖ በየሀገሩ በየቦታው እየተጋባ፣ ዘር ሲባዛ አይደለም እንዴ የኖርነው? ደም ሲቀላቀል አይደለም ወይ የነበረው? ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት በብሔር ተመርኩዞ ንፁህ ደም ተብሎ፣ አንዱ ተነጥሎ በጭራሽ ሊገለፅ የማይቻል ነገር ነው:: የኢትዮጵያዊነት እንጂ የኦሮሞ፣የአማራ፣የትግሬ የሚባል ደም የለም::

**ግዮን፡- ወጣቱ “እኔ የአክሱም ባለቤት የጀግና ልጅ ነኝ” ብሎ መመፃደቁ ብቻውን ኢትዮጵያዊ ያስብለዋል?**

**ረ/ፐ/ር አበባው፡-** ብዙ ጊዜ በአክሱም ጊዜ የተሰሩ ሐውልቶች፣ የላልይብላ ውቅር አብያተ ክርስቲናት፣ ጎንደር፣ ጢያ፣ ሐረር ምልክቶቻችን ናቸው ብለን መግለፅ እንወዳለን:: እነዚህ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ናቸው የሰሩት:: ወጣቱ ምንድን ነው የአንተ ምልክት እንበለው፤በተለይ ዘመናዊ ትምህርት ከመጣና ከተስፋፋ በኋላ ወጣቱ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናው ዳብሮ መደራጀት ከጀመረበት ከ50ዎቹ እንጀምር::

በ1950ዎቹ የነበረው ትውልድ ከዛ ቀጥሎ የመጣውና አሁን ያለው ትውልድ ምንድን ነው ለዚህች ሀገር ያደረገው አስተዋፅኦ ምን ምልክት አለ? ስንል ምንም ነገር የለም:: ይበልጡን ትኩረት የተደረገው የፖለቲካ ቁርቁስ ላይ ነው:: ያ የፖለቲካ ቁርቁስ ደግሞ እየለያየን፣ እየለያየን ነው የመጣው:: አንደኛ የባዕድ አይዶሎጂ እናመጣለን:: የባዕድ ርዕዮት አለም ይዞን በኢትዮጵያዊነት ላይ ለውጥ ማምጣት አልቻልንም:: እነዛ እኮ ይሄን ይሄን ሰርተን እናልፋለን ብለው አድርገው አልፈዋል:: የአሁኑ ትውልድ ግን አንድም ምልክት የለም::

ቀደም ሲል አባቶቻችን ያወረሱንን ኢትዮጵያዊ እሴት መጠበቅ ራሱ አንድ ነገር ነው፤ አልጠበቅነውም፤ አልቻልንበትም:: የ1950ዎቹ ትውልድ ማለት እኮ እነ መለስ ዜናዊን ይጨምራል፣ እነ አቦይ ፀሐዬና ጓድ መንግስቱን ይጨምራል:: በሐይማኖቱ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚው ሊቅ የሆኑትን በሙሉ ይጨምራል:: እነዚህ ሰዎች ያን እሴት አስጠበቁልን ወይ? ከተባለ አላስጠበቁልንም::

ከዚህ ሌላ በስልጣኔ ረገድ የእዚህ ትውልድ ሚና ይሄ ነው የሚባለውስ ምንድን ነው? ትንሽ የጀመርነው ነገር የአባይ ግድብ ነው፤ የኢትዮጵያ ትልቅ ፈተና የነበረው ይሄ ወንዝ ከሆነ፣ ያን እንኳን መስራት አንድ ነገር ነበር:: መንገድ፣ ሆስፒታል መስራት እኮ ቀላል ነገር ነው:: ከዚህ በመነሳት ካየነው የወደቀ ትውልድ ነው::

**ግዮን፡- ምክንያቱ ምን ይመስልዋታል?**

**ረ/ፐ/ር አበባው፡-** ለዚህ ውድቀት አስተዋፅኦ ያደረገው በዋነኝነት ፖለቲካው ነው:: የ1950ዎቹ ፊል ያደረገው ኢትዮጵያዊ ማንነቱን፣ የኋላ ታሪኩን ትቶ፣ በሶሻሊዝም በማርክሲስትና ሌኒኒስት አስተሳሰብ ተቃኝቶ፣ የድሮውን እሴት ሁሉ አንድ ላይ ናደው:: የአብነት ትምህርት ኋላ ቀር ነው፣ ማህበራዊ ሥርዓቶች ኋላ ቀርነት ነው፣ ዳዊት አውጥቶ መድገም ኋላ ቀርነት ነው፣ እንደ እሬቻ አይነት የአምልኮ ቦታዎች ላይ ሄዶ ማምለክ ኋላ ቀርነት ነው ብሎ አቋም ያዘ:: እነዚህ ነገሮች ▶

◀እኮ ውርሳችንም ትውፊታችንም ናቸው::

በባዕድ ባህልና አስተሳሰብ ተቃኝተህ ስትመጣ የራስህን ማንነት ትረሳለህ:: ሌላውንም አትሆንም፤ ደግሞ ለመምሰል ነው የምትሞክረው:: አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ የካድሬዎች አለባበስ ሰማያዊ ጨርቅ መሆኑ ማንን እንደኮረጅን ያሳያል:: ራሳችንን መሆን አንችልም ነበር ወይ? በአስተሳሰብም ሌላውን መምሰል ይመጣል:: ከማንነትህ ጋር ስትጣላ ትልቅ የመምሰል ፖለቲካ ውስጥ ትገባለህ::

ሁለተኛውና ከደርግ ውድቀት በኋላ ያለው ደግሞ ማንነትን በጎጥ ብቻ ማስቀመጡ ትልቅ ችግር ፈጥሯል:: ስትነጣጠል እና በዘር ተከፋፍለህ እንደ አንተ ብቻ የምታስብ ከሆነ እንዴት አድርገህ ነው ኢትዮጵያዊነት እሴትን ጠብቀህ የምታቆየው? እንዴት አድርገህ ነው ዘመንህ ምልክት ሊሆን የሚችል አስተዋጽኦ፣ በስልጣኔ ረገድም ሆነ በሌላ መንገድ ልታበረክት የምትችለው? ማዶና ማዶ እንዳትገናኝ ሆነህ በመሀል ላይ ትልቅ ግድግዳ ከሰራህ ማለት ነው::

ሕወሓት /ኢህአዴግ በዚህ መንገድ ትውልዱ እንዳያድግና የራሱን አሻራ የሚያስቀምጥ ኢትዮጵያዊ እንዳይፈጠር፣ አካባቢያዊ ብሔርተኝነት ላይ ብቻ እንድናተኩር አድርገው ነው በስልጣን ላይ በቆዩበት ወቅት የሰሩት:: የእሱ ውጤት ነው የኢትዮጵያዊነት መጥፋት ላይ እንዲህ የሚያነጋግረን::

**ግዮን፡- የኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ድንበራዊነትና ሀገራዊነት ሶስቱ እንዴት መቀናጀት ይችላሉ?**

**ሬ/ፕ/ር አበባው፡-** ያ ከሕገ መንግስትም ጋር ሊገናኝ ይችላል፤ ካለው ስርዓትም ጋር ሊገናኝ ይችላል:: ኢትዮጵያዊነት ድንበር የለውም:: የኢትዮጵያዊነት ወሰንን በሀገር ግዛትና በሌላ መንገድ ከወሰድነው እርሱ ዓለም አቀፋዊ ወሰኑ ነው:: ኢትዮጵያ ተብሎ እውቅና የተሰጠው ማለት ነው:: እዛ ውስጥ ምንም ይሁን ምን የኢትዮጵያዊነት ወሰን የለም::

አባይ በምስራቅ ጎጃምና በሰሜን ኦሮሞያ መሀከል ድንበር ስለሆነ የኦሮሞና የአማራ ድንበር ነው ማለት አይደለም:: ኢትዮጵያዊነት በክልል ወሰን የታጠረ አይደለም:: ችግሩ ክልልን እንደ ባለቤት አድርጎ መውሰድ ነው:: የኦሮሚያ ክልል የኦሮሞ ሕዝብ የሚተዳደርበት ነው፣ ለአስተዳደር ተብሎ ነው የተከለለው:: የሀረሪ ክልል ለአስተዳደር ከግብር ጀምሮ ክፍት ስርዓቱና ከጤና አገልግሎቱ ጋር እንዲመች ተብሎ እንጂ ሐረሪ የፈጠረው ወይም የሰራው አይደለም:: የአማራን ክልል የአማራ ሕዝብ ብቻ አይደለም የሚኖርበት:: በዘመናት ውስጥ ያንን ክልል ያልረገጠ የለም:: በዘመናት አዲስ አበባን ያልረገጠ የኢትዮጵያ ብሔር የለም:: ተዋልዷል፣ አልፏል፣ ኖሯል:: አንዱ ዕትብቱ ተቀብሮበታል፣ አንዱ ተሰድዶ መጥቶ ኖሮበታል::

ይሄ ሲሆን ኢትዮጵያዊነትን ማጉላት ትተን ክልል መሬትና በዛ ላይ ያለው ሀብት "እኛ ኢትዮጵያውያን" የሚለውን አስቀረና "እኛ ኦሮሞዎች ነን፣ አማሮች ነን፣ አፋሮች ነን" ማለትን አመጣ:: ይሄ ከመጀመሪያው ሲታሰብም ስህተት የነበረ ነው:: የአስተዳደር ክልል ተከለለ ማለት የህዝቦችን መስተጋብር መገደብ አይደለም:: የኦሮሚያ ፖሊስ የአማራ ታርጋ የያዘ መኪናን እያየ መቅጣት ኢትዮጵያዊነትን ማቀጨጭ እኮ ነው:: የአፋር ፖሊስ የሶማሌውን ታርጋ ሲያይ ደግሞ እንደ ኤሊየን መቁጠር ተገቢ አይደለም:: የሲራራ ነጋዴዎች እኮ ድሮ ከምፅዋ ከፋ ነበር የሚመላለሱት:: በዛ ላይ አንተ ትግሬ ነህ፣ አማራ ነህ ተብሎ አያውቅም:: አረብ ነህ ተብሎ እንኳን የሚጠየቅ ነጋዴ አልነበረም::

የትኛውም ሕዝብ አሁን የሚኖርበትን ቦታና ክልል ጠፍጥፎ አልሰራውም:: በታሪክ አጋጣሚ መጣበት ኖረበት:: ስለዚህ የኢትዮጵያዊነት ወሰን በክልሎች ድምር አይደለም የሚገለፀው፤ ክልል ተደምሮ ኢትዮጵያን አያመጣም:: ኢትዮጵያዊነት ለአስተዳደር ሲባል ለኦሮሞ ሕዝብ ህልውና የምትሰጠው ኢትዮጵያ ነች፣ አማራ ለምንለው ክልል ህልውናው፣ ለቤንሻንጉል ጉምዝም ሆነ ለደቡቡ ህልውናው ኢትዮጵያ ናት እንጂ፤ ክፍልፋዮች አንድ ሆነው ኢትዮጵያን ይመሰርታሉ የሚለው አስተሳሰብ ጨርሶ የተሳሳተና የወደቀ ነው::

**ግዮን፡- ይህ ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን ተሸክሞ ለመጓዝ አቅሙ አለው? ዕድሉንስ ያገኛል?**

**ሬ/ፕ/ር አበባው፡-** ዕድሉ እየተፈጠረለት ነው:: አሁን በለውጥ መንገድ አስር ወር ሊሞላን ነው፤ ቢያንስ ኢትዮጵያ የሚለው ስሜት ለ27 ዓመታት ብቻ ሳይሆን ላለፉት 40 አመታት ተሸርሽሮ ቆይቷል:: በደርግ ጊዜ "ኢትዮጵያ ትቅደም፣ ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ስለተባለ ኢትዮጵያ ነበረች ማለት አይደለም:: ያ ሁሉ የሀገሪቱ ባህል ድምጥማጡ የጠፋው በዛን ጊዜ ነው:: በኮሚኒዝም ስም ኢትዮጵያ ተሸርሽራለች::

ይባስ ብሎ ጀግኖች ነን የሚሉት በ1983 ዓ.ም ስልጣን ላይ ሲወጡ በነበረው ላይ ጨመሩበት:: አሁን እንግዲህ ካለፈው መጋቢት ወር 2010 ዓ.ም የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መምጣት ጀምሮ ነው ኢትዮጵያዊነትን ዳግም ማቀንቀን የጀመርነው:: በነገራችን ላይ ይሄ በጣም የሚያሳፍር ነገር ነው:: ኢትዮጵያን የሚያህል ሀገር ኢትዮጵያን ፍለጋ እንደገና አይሄድም:: ገንብተን፣ ገንብተን ስንት ሺህ ዓመት ያቆየነውን ነገር ንደን፣ እንደገና በየቴሌቭዥኑ እንደ እኔ ዓይነቱ ምሁር ነኝ ባዩ፣ ፖለቲከኛውም "ኢትዮጵያዊነት ማለት እንዲህ ነው" ሲል መስማት እጅግ አሳፋሪ ነገር ነው::

ኬንያ ትናንትና ከቅኝ ግዛት በኋላ የተመሰረተች ሀገር ናት፤ ግን ሂድና አንዱን ዜጋ "ኬንያዊ ማለት ምን ማለት ነው?" ብትለው "እያላገጥክ ነወይ?" ነው የሚልህ:: ከትውፊቱ፣ ከባህሉ፣ ከታሪኩ በመነሳት ኬንያዊነት ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: እኛ ያንን አጥፍተን አሁን ነው የጀመርነው:: ኢትዮጵያዊነት ከማህበራዊ ነገራችን ጋር የተዋሃደ ስለሆነና በፖለቲካው ደረጃ ጥሩ ትኩረት ስለተሰጠው ትውልዱ ቀና የሚልበት፣ ኮራ የሚያሰኘውን ኢትዮጵያዊነት በደንብ የሚረዳበት ዕድል አሁን ተፈጥሮለታል:: እንዲህ ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅን መሪ ካለ፣ ይሄ መሪ የእኔ ነው፣ ሀገሬን ሀገሬን ማለት ይጀምራል::

በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊነትን ተሸክሞ እንዳይሄድ መሰናከል የሆነው የፖለቲካው ከባቢ ነው:: አሁን ላይ ላዩን ኢትዮጵያ ይባላል፣ ውስጥ ላይ ግን እውነት የፖለቲካው ይዘት ሌላው ነገር ሁሉ ምንድን ነው? ብለን ስንወስድ አሁንም "እኔ ኦሮሞ ስለሆንኩ በኦሮሞነቴ ነው የምደራጀው፣ ለኦሮሞ ሕዝብ እሞታለሁ" የሚል እንጂ ኢትዮጵያ የሚለውን ሀገራዊ ስሜት የማቀንቀን ነገር የለም:: ወደ ብሔር ነው የሚሮጠው:: "እኔ ጀግና አማራ ነኝ" ብሎ ማሰብም አለ፤ ያለፈው ሕወሓት የቆመረው የመለያየት፣ የግጭትና የዘር ኢኮኖሚ አሁንም በግልፅ ፖለቲካው ላይ ሲንፀባረቅ እናያለን::

የፖለቲካ አትሞስፌሩን በኢትዮጵያዊነት ቅኝት ካልቃኘነው ወጣቱን ልንፈርድበት አንችልም:: ኢትዮጵያ የሚለውን ሀገራዊ ስሜት ተሸክሞ ለተተኪው ማስተላለፍ ባይችል ኋላ ላይ ፈፅሞ ልንወቅሰው አንችልም:: ሁለተኛ ይሄ ትውልድ ከ50ዎቹ ጀምሮ ሲተላለፍ የመጣ ውዝፍ ያለበት ነው:: "ተራሮችን ያንቀጠቀጠ" የሚባል ትውልድ የብሔር መብት፣ የመገንጠል እያለ "ተራራ" የሚያህል ጥያቄ አንስቶ ጠጠር የምታህል መፍትሄ ሳያስቀምጥ የሄደ ነው:: ተጨቁኛለሁ ያለውም ስልጣን ላይ ሲወጣ ከጨቋኞች የበለጠ ሆኖ አረፈው:: ሁሉም ውዝፍ እየተወ ነው የሄደው:: ስለዚህ ወጣቱን ማገዝ ከተቻለ ለውጥ ማምጣት ይቻላል::

**ግዮን፡- በዚህ አጋጣሚ ወጣቱ ትውልድ ኢትዮጵያዊነቱን ይዞ እንዲቀጥል ምንድን ነው የሚመክሩት?**

**ሬ/ፕ/ር አበባው፡-** አንድ ነገር የሚጀምረው ሀገር አለኝ ብሎ ከማሰብ ነው:: ሰው የማይታሰርባት፣ የማይገደልባት፣ ፍትህ የሚገኝባት አንዱ የመንግስትና የሕዝብ ካዝና ዘግኖ የሚሄድበት፣ አንዱ ከየትም ብለህ የግድ ካዝናውን ሙላ የሚባልበት፣ ሌባ የሚከበርባት፣ ሥራ የሚሰራ ሰው ደግሞ የሚናቅባት ሀገር ሀገር አለኝ ብሎ አያስብም ነበር::

አሁን ግን ሀገሬ ሀገሬ የሚል ስሜት እየመጣ ነው:: ለመኖር እኮ የትም ትኖራለህ፣ ግን በኩራት የምትኖረው ሀገርህ ላይ ነው:: ይጥማህ፣ ይራብህ ግን የመንፈስ ርሃብ የማይዝህ ሀገርህ ስትሆን ነው:: አሁን እየተፈጠረ ያለውን ይሄን ነገር ወጣቱ ማጠናከር ነው ያለበት:: መጥፎው ነገር ለባዕድ ባህል አለመማለል ነው፤ እነዛ ባዕዳን የደረሱት የሲኒማው፣ የሙዚቃውን ነገር ትቶ ቴኬኖሎጂውን ብቻ እየተጠቀሙ፣ የእነሱን ባህል ከፍ አድርጎ የእኛን ዝቅ ማድረግ ይጎዳል:: ለዘመናት የቆየ ባህላችንን ጠብቆ መያዝ አለመናቅ ያስፈልጋል::

ሌላው ጠያቂና ሰሪ ትውልድ መሆን ይኖርበታል ወጣቱ:: በስራ ይመን:: አሁን ያጣነው ትልቁ ነገር ሰርቶ የሚበላ ሕዝብ ነው፤ ጥሮ ግሮ ማለት ነው:: ተሰርቶ የሚበላባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ፤ ከተመረቁ ሁለት ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ሁሉ ቶሎ የሆነች ነገር መንተፍ ማድረግ ወይንም ደግሞ በሆነ ዘዴ ሀብት ማካበትና በአቋራጭ መክበር ነው የሚፈልጉት:: መጀመሪያ ሰርቶ ለማግኘት የሚጥር፣ ከዛ በኋላ ደግሞ ለመብቱ ጠያቂ የሆነ ወጣት ሊኖር ይገባል:: እነዚህን አጣምሮ ከያዘ ጠንካራ ትውልድ ይኖራል::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

# በኢትዮጵያ የውጪ. . .

ከገጽ 28 የዞረ

የተቀላጠፈ የባንክ ሥርዓት በመዘርጋት ተጠቃሽ ለመሆን ችሏል፡፡ በቱርክ እጅግ ዘመናዊ የሆነ የበጀትና የዕቅድ አሰራሮችን በከፍተኛ ደረጃ ያስተዋወቁት የውጭ ባንኮች ናቸው፡፡

## የውጭ ባንኮች ለዓለም ዓቀፍ ገበያ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ

በራቸውን ለውጭ ባንኮች የከፈቱ አገራት የውጭ ኢንቨስትመንትን በተሻለ ለመሳብና በዓለም የንግድ ተቋማት ተፈላጊነት የማግኘት ዕድላቸው ካልከፈቱት በአንፃራዊነት የተሻለ እንደሆነ ጀርሚዲስ እና ማሾሌት ከላይ በተጠቀሰው ሥራቸው ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ላኪዎች፤ አስመጪዎች እና ትልልቅ ኩባንያዎች የነዚህ ባንኮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ እና የውጪ ገንዘብ (hard currency) በጥልቀት እና በሚፈለገው መጠን እንዲንሸራሸር ዕድል ያመቻቻሉ በማለት ዘርፈ ብዙ ፋይዳቸውን ምሁራኑ ለመዘርዘር ሞክረዋል፡፡ በኮርያ እና በአውስትራሊያ የውጭ ባንኮች ውጤታማ ሥራ እንዲሰሩና በተለይ በፓኪስታን ከ1990- 92 ባሉት ዓመታት ABN Amro የተባለ ባክ ከ100 ሚሊየን ዶላር በላይ የወጪ ገንዘብ በማንሸራሸር አገሪቱን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻለ ያስረዳሉ፡፡

የገንዘብ ተቋማቱ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ብዙ ገንዘብ ይዘው ስለሚመጡ መንግስትም በቀላል ወለድ የተሻለ ብድር ማግኘት ይችላል፤ ከመንግስትም ባለፈም አገር ውስጥ ያሉ ተበዳሪዎች ብድር እንዲያገኙ ሠፊ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ገበያ መር የሆነ የገንዘብ ዋጋ ትመና እንዲኖር በማድረግ የገበያ ኢኮኖሚ እንዲያድግና ውድድር እንዲፈጠር በማድረግ ትመናው በፍላጎትና በአቅርቦት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ዘርፈ ብዙ የኢንቨስትመንት እድል፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር፤የሥራ ባህል በመፍጠር አገራት ኢኮኖሚያቸውን የሚያሳድጉበትን ዕድል እንዲዘረጉ ያስችላሉ  በማለት ምሁራኑ የውጭ ባንኮችን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡

## የውጭ ባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ መግባት አሉታዊ ጎኑ ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ መንግሥት በሩን ለውጭ የገንዘብ ተቋማት እስካሁን እንዳልከፈተ ይታወቃል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሥልጣን በያዙ ማግስት ሌሎች ትልልቅ የመንግስት ተቋማት ላይ ለውጥ እንደሚደረግ እና ለውጭ ባለሀብቶች በከፊል ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሲጠቅሱ የገንዘብ ተቋማት ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ የጠቆሙትም ሆነ የሰጡት አቅጣጫ የለም፡፡ እስካሁን የኢትዮጵያ መንግስት ዓለም አቀፍ ባንኮች በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የፈለገበት የራሱ የሆኑ መነሻዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ በአገሪቱ ያሉትን የገንዘብ ተቋማት ኃላፊዎች ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት የውጭ ባንኮች ይገባሉ አይገቡም የሚለውን  አንስተው  የጊዜ  ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ባንኮቹ ወደ አገር መግባታቸው እንደማይቀር ፍንጭ ሰጥተዋል፡፡ እስከዚያው ባንኮቹ ራሳቸውን እያጠናከሩ እንዲሄዱ እና መንግስት ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ነግረዋቸዋል፡፡

የውጭ ባንኮች ወደ አገራችን መግባታቸው የጊዜና የሁኔታዎች ጉዳይ ካልሆነ የማይቀር ነገር ነው የሚሉት  የዘርፉ ጉምቱ ባለሙያ አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ይናገራሉ፡፡  አገራችን በዚህ ዓለም ካሉት አገራት ተለይታ ብቻዋን የምትኖር አገር አይደለችም፡፡ ከሌሎች አገሮች ጋራ ተገበያይታ የምትኖር አገር ነች፡፡ ይህ እስኪሆን ድረስ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን አመልክታለች፡፡ እስካሁን ድረስ በሃሳብና በወሬ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር እንዳሁኑ የምር የሆነ ድርድር ውስጥ አልገባችም፡፡ አሁን አፍሪካ ውስጥ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ያልሆኑ ከ4 ወይም 5 አገራት አይበልጡም፡፡ በሙሉ አባል ናቸው፤ እኛም ከዚህ ውጭ መሆን አንችልም፡፡ በዚህ ጉዳይ ውይይት፤ ድርድር እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የውጭ ባንኮችን ወደ ሀገር ውስጥ መግባት  በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጊዜ ጉዳይ ብቻ መሆኑ ጠቅሰዋል፤ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ለአገር ውስጥ ባንኮች የዝግጅት ጊዜ ተሰጥቶ፤ እኛም ራሳችንን ወደ ማስተካከል መሄድ ይኖርብናል የሚሉት አቶ ኢየሱስ ወርቅ አሁን ያለነው 16 ደቃቅ የንግድ ባንኮች እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች አለን ማለት አይቻልም፡፡  የእኛ አገር ባንኮች አመሰራረት ግማሹ በሃይማኖት፣ ግማሹ በዜግነት፣ ግማሹ በጎጥ እና በፖለቲካ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ይህንን አስተካክለን ተዋህደን (Merge) መስራት አለብን፡፡ አለበለዚያ ራሳችንንም ሊያደክመን የሚችል መንገድ ነው፤ አሁን እየተከተልን ያለነው በማለት የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ተጠናክሮ፤ ተወዳዳሪ ለመሆን ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

ከምጣኔ ሀብት ትንታኔዎች አንፃር የተቋማቱ ወደ አገር ውስጥ መግባት ጥቅም ያለውን ያህል ጉዳቶችም አሉት፡፡ከጉዳቶች አንዱ የምጣኔ ሀብት ምሁራን የባለብዙ ቅርንጫፍ ተቋማት ተፅዕኖ የሚሉት (multinational Intitutional Effect) ነው፡፡ የገንዘብ ተቋማቱ ዋና መቀመጫቸውን አገራቸው ላይ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ በመክፈት ገንዘባቸውን ከአንዱ ቅርንጫፍ ወደ ሌላው ቅርንጫፍ በነጻ ማንቀሳቀስ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ መንግሥት በግብር እና በሌሎች ክፍያዎች መልክ ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሳያስገባ የሚቀርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል በማለት የውጭ ባንኮች ከሚሰጡት ጠቀሜታ ባሻገር ሊያደርሱ የሚችሉትን የጎንዮሽ ጉዳት ያስረዳሉ፡፡

ሌላው እንደ ሥጋት ሊነሳ የሚችለው የባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ዓለም አቀፍ የሆኑ ችግሮችና የኢኮኖሚ ሥጋቶች ወደ አገሪቱ እንዲገባ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚለው ነው ፡፡ በ2008 በአሜሪካ የተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ የአሜሪካና የአውሮፓ ኢኮኖሚ የተሳሰረ በመሆኑ ቀውሱ ወደ አውሮፓ በቀላሉ ነበር የተሸጋገረው፤ በተመሳሳይ መልኩ ዓለም አቀፍ ባንኮች ለመሰል ችግሮች በሚጋለጡበት ወቅት ኢትዮጵያም የችግሩ ተጠቂ የመሆን እድሏ ይሰፋል የሚል ነው፡፡ በተጨማሪም ባንኮች ደንበኛ ለመሳብ  እና ለመቆጣጠር ሲሉ ፍትሃዊ ያልሆነ ውድድርና ፉክክር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ባለሙያዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ የውጭ ባንኮቹ አቅማቸው የፈረጠመ በመሆኑ አቅማቸው ደካማ የሆኑት የአገር ውስጥ የገንዘብ ተቋማት ውድድሩን ለመቋቋም በሚያደርጉት ትግል ወጪያቸው ጨምሮ ትርፋቸው አንሶ ከገበያ ውጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስጠነቅቃሉ፡፡

## ችግሮቹን ለመቋቋም ምን ይደረግ?

ተቋማቱ ወደ አገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በቅድሚያ ትኩረት መሰጠት ያለበት አንግብጋቢ ጉዳይ እንደሚኖር የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ ባንኮቹ ወደ አገር ውስጥ ገብተው በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት የሚገኙትን ጥቅሞችና ተሳትፏቸው ሊያስከትለው የሚችለውን ጉዳቶች የማመጣጠን ተግባር ነው፡፡ ከነዚህም እርምጃዎች መካከል የገንዘብ ፖሊሲውን ማስተካከል፤ ይህም ሲባል የምንዛሪ የወለድ ተመን አወሳሰን በመንግስት የሚወሰን መሆኑን በመተው፣ በገበያ መር አሰራር ሊተካ ቢችል ፣ችግሩ በተወሰነ መልኩ ሊቀንስ ይችላል፡፡ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት (Regulatory system) በመዘርጋት የገንዘብ ሥርዓቱን ማቀላጠፍ ይገባል፡፡ ይህ ሲባል የውጭ አገር ገንዘብ መጠን ፍላጎትና የዋጋ ግሽበት ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል ፡፡ የአገር ውስጥ ተቋማቱን የመወዳደር አቅም በማስላት ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸትም አስፈላጊ ነው፡፡ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የፋይናንስ ተቋማት ብዛት፤ ይዘውት የሚገቡት የገንዘብ መጠን በተጨማሪም መንግስት ተቋማቱና የአገር ውስጥ ባንኮች ድርሻ ምን ያህል ሊሆን እንደሚገባ መግባባት ከባንኮቹ መግባት ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ችግሮች ለመቀነስ አማራጭ ይሆናሉ፡፡ የገንዘብ ኢንዱስትሪው ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶለት በዚያ መሰረት መራመድ እንዲችል ከተፈለገ ብሔራዊ ባንክ በሚፈለገው ደረጃ መለወጥ አለበት፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ዘርፉን ለመለወጥ መነሳት አስቸጋሪ ሊያደርገው እንደሚችል የፋይናንስ ባለሙያው አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ይናገራሉ፡፡

የእስያ አገራት ደቡብ ኮርያ፤ ታይዋን፤ ጃፓን በ1990ዎቹ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሲያስመዘግቡ ኢኮኖሚያቸው ለውጭ የገንዘብ ተቋማት ክፍት አድርገው ነበር፡፡ እ.ኤ.አ ከ1995 እስከ 2010 በነበሩት ዓመታት 75 በመቶ የሚሆነው የአገራቱ የገንዘብ ፍሰት በውጭ ባንኮች የተያዘ እንደነበር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ አገራት በራቸውን ለውጭ ባንኮች ክፍት በማድረጋቸው ተጠቃሚ ነበሩ፡፡ ይህም ስኬት ሊመዘገብ የቻለው  የተነቃቃና ጤናማ የሆነ ኢኮኖሚ  እና ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግተው በመገኘታቸው ነው፡፡

# የቴዲ ራእይ

ድንቁ ጸሓፊ ተውኔት እና ገጣሚ ጌትነት እንየው "የቴዎድሮስ ራእይ" የሚል ?ሙዚቃዊ ቴያትር ከነ ሙሉ ባህላዊ ውበቱ አሳይቶን አስደንቆንም አነሳስቶንም ነበር። አዎን ጀግና ይወለዳል፣ እንደፈሪም አይቆይም ቶሎ ይሰበራል፣አይበረክትም። ራእዩ ግን ለዘላለም ይኖራል።ብርሀኑ ዘርይሁንም ወደ 19ኛዋ ክፍለዘመን ጎንደር መልሶ ወስዶ በታንጉት ውስጥ የመይሳውን ራእይ ያሳየናል። በምናቡ ጥልቀት ተደምመን ሆ! እስክንል ድረስ። ለቴዲ ውድቀትም አንዱ ምክንያት በየጉራንጉሩ ጭብጥ የማይሞላ ሀሳብ የሚያቶኮትኩ (አሞሌ እንደላሰ በሬ በስሜት እንደሚመራው ጋረድ፣ ለተንኮልና ለሴራ እንደማይሰንፈው ደብተራ አክሊሉ) እንደሆነ ያሳየናል።

እናም... ምን ለማለት ነው...
እንኳን ለጀግናው ልደት አደረሳችሁ
ለቴዲዎችም
ለገብርዬዎችም
ለጋረዶችም
ለአክሊሉዎችም.. ኢትዮጵያ ከሁላችንም በላይ ናትና!

ሰለሞን አፈወርቅ



# ለዘውጌ ብሄርተኞች ይህን ፎቶ ስታሳያቸው

መጀመሪያ ስለ ሰዎቹ ችግር፣ድህነት፣መንከራተት እና ጉስቁልና እንዳይመስልህ የሚያሳስባቸው።
ከየት ክልል ነው ? የት አካባቢ ነው ? የምን ብሔረሰብ ተወላጆች ናቸው ? የሚለው ነው።
በለስ ቀንቶት ከእኔ ከሚለው ቡድን ናቸው ከተባለ
ኡኡኡ
ሀገር ይያዝልን
የጨርቦሌ ብሄረሰብ እንዲህ እየተበደለ ነው።
እሪሪ በይ ጨርቦሌ
እከሌ ይውርድ እከሌ ይሰቀል
በጨርቦሌ ብሔረሰብ ላይ የምትገመድ ሀገር ብትንትኗ ይውጣ

ሰሚር አሊ



## የባልቻ ልጅ

የባልቻ ልጅ ነው ፧
የምኒሊክ ልጅ ፧
የጎበና ልጅ ፧ የመብረቆቹ የነ ጃገማ ፧
ጋሻውን ይዞ ፧
ዘራፍ ይልሃል ፧የሸዋው ኮከብ ታከለ ኡማ!
!!!!!

መንግሥቱ ዘገየ

## ለፈገግታ




ሰኞ ማታ የሕወሓት ሽማግሌዎች በደብረፅዮን ቤት አድረው ነበር። ምክንያት፥ ከኢሳያስ ጋር ያወሩትን ለመጠየቅ! ከጥያቄዎቹ መካከል የተወሰኑቱ:

1. “ኢሳያስ ምን አለ?”
2. “በእጁ ጨበጠህ?”
3. “በሥነሥርዓት አናገረህ?”
4. “ስለ ድንበር መዝጋት ምን አለ?”
5. “እኔንስ አስታወሰኝ?” (ስብሃት ነጋ)
6. “ከሱ ጋር ስትጠጡ የነበረው ሻይ ይጣፍጣል? “ (አባይ ፀሓዬ)
7. “ትምክህተኛው ገዱ ለምን ከናንተ ጋር ሄደ?” (ስዩም መስፍን)
8. ከዐቢይ ጋር ምን ተባባሉ? (ጌታቸው አሰፋ)
9. “ተሰነይ (ኤርትራ) ውስጥም ገባን እኮ! ሴቶችም ነበሩ።” (ደብረፅዮን)

ኤርትራ ፕሬስ

## የዜግነት ፓለቲካ መቼም አይሞትም

በአገራችን የዜግነት ፖለቲካ ተስፋ ከሌለው እንዲሁ በብሔር ተቧድነን ዝንተ ዓለም እየተዳረቅን ልንኖር ነው ማለት ነው። የ 27 ዓመቱ የጐሳ ትርምስ የዜግነት ፓለቲካ ማራመድን ከባድ ቢያደርገውም አሁንም ይህንን ዓይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ለመጀመር የሚያስችል በቂ ማኅበራዊ መሠረት አለ። ችግሩ የአገሪቱ የፖለቲካ ይህንን አይነት አስተሳሰብ ለማራመድ አመች አለመሆኑ ነበር። ጠንካራና በትክክል የዜግነት ፖለቲካ የሚያራምድ አደረጃጀት ከተፈጠረ አሁንም ያልጠፉትን ታሪካዊና ማኅበራዊ እሴቶችን መሠረት በማድረግ ቀስ በቀስ ከትርምሱ የምንወጣበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።

ሰማኸኝ ጋሹ

# ኢትዮጵያዊው ቤተ እስራኤል

"በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ።" ይላል ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 13: 23

ከሆነስ ሆነና መልኩ ሳይቀር ከእነመልካምድሩ በጥንታዊ መጽሐፍ ውስጥ የተካተተለት ኢትዮጵያዊ እስከምን ድረስ የቀደመ መሠረቱን ጠብቆ ቀጥሏል? ነው ወይስ አንዳንዶች እንደሚነግሩን ይህ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? ተብሎ የተነገረለት ሕዝብ ሌላ ሕዝብ ነው? ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ለኢትዮጵያውያን የጋራ ማንነት ፍለጋ የሚያበረክትላቸው አንዳች ፋይዳ ያለው ነገር ይሆን ? የኢትዮጵያ ሰው የጋራ ማንነት የሌለው ግፋ ቢል የመቶ ዓመት የወረራ ታሪክ ያገናኘው ሕዝብ ነው በማለት የብሔር የልዩነት ፖለቲካዊ ፍልስፍናን ሙጭጭ ያሉት ወገኖቻችንንስ ማሳመን የሚችል ነገር ከዚህ ጥንታዊ ታሪክ ውስጥ ተፈልቅቆ ይወጣ ይሆን?

ለመሆኑ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ወደ ተለያየ የጎሳ መጠሪያ ስም ከመከፋፈላቸው በፊት ይጠሩ የነበረው ኢትዮጵያዊ በሚል አንድ ስም ነበር ማለት ነው? በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን ማለት ራሱ ምን ማለት ነው?

ጴጥሮስ አሸናፊ





ተስፋዬ ሽብሩ

# በኢትዮጵያ የውጪ ባንኮች
## የጎንዮሽ ጉዳት እና ጥቅም ሲመዘን

በኢትዮጵያ የባንክ አገልግሎት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ የባንክ አገልግሎት ለአገራት የልማትና የእድገት አቅጣጫ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ባንክ ለአንድ አገር ለልማት ፕሮጀክቶች ፤ለሥራ ዕድል መፈጠር የሚያገለግል ገንዘብ በማመቻቸት፣ የአገሮችን የልማት ጉዞ በማሳለጥ የማይናቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

ኢትዮጵያ በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፎች ለምታካሂዳቸው የልማት እንቅስቃሴዎች አስተማማኝ የሆነ የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልጋታል፡፡ ለዚህ ደግሞ ባንኮች ወሳኙን ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅት ፕሮጀክቶችም ይሁኑ የግሉ ዘርፍ የሚፈልጉት ፋይናንስና የአገሪቱን ባንኮች የአቅም ደረጃ የሚመጣጠን አለመሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ በሌሎች አገራት እንደተደረገው የዓለማችን ታላላቅ ባንኮች ወደ አገሪቱ ገብተው የብድር የእርዳታ እንዲሁም ሌሎች የፋይናንስ አገልግሎቶች ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉበት አሰራር እስካሁን አለመኖሩ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎት በቂ በሆነ መልኩ ተስፋፍቶ አይገኝም፡፡ ጎረቤት አገራትን ጨምሮ በሌላው ዓለም እንደሚታየው የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ የሚያስችል ስርዓት ተግባራዊ ቢሆን ኢትዮጵያ ከዚህ አገልግሎት ምን ታተርፋለች? ምንስ ታጣለች? የሚለው ጥያቄ የብዙ የዘርፉ ምሁራን ጥያቄ ነው፡፡

ባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ ቢገቡ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ተሳትፎ ቢያደርጉ፣ ለመንግሥትም ለግሉ ዘርፍም የሚሰጧቸው ጥቅሞች እንዳሉ የፋይናንስ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ዓለም አቀፍ ባንኮች መጠነ ሰፊ አቅም ስላላቸው የአገሪቱን ዓለም አቀፋዊ ትስስር በማስፋት አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ፡፡ከዓለም ዓቀፍ የፋይናንስም ሆነ መሰል ተቋማት ጋር አገሪቱ የሚኖራትን የአባልነት ተቀባይነትና አመቺነት በማሳካት ረገድ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ ብድርና እርዳታ አሁን ካለው በተሻለ እንድታገኝ እና ከሌሎች አገራት ጋር ያላትን የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ትስስር በማቀላጠፍ ከዓለም ኢኮኖሚ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡



በርክሌ ባንክ

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የአገር ውስጥ የገንዘብ ተቋማት ልምድ እንዲያገኙ ከመርዳት ባለፈ የውጭ አገራት የገንዘብ ፍሰትንና አቅርቦትን በመጨመር እና ኢኮኖሚን በማሳደግ፤ ዘመናዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፤ ለፋይናንስ ሴክተሩ የተቀላጠፈ አሰራር በማስተዋወቅ፤ የተቋማቱን ውጤታማነት በማሳለጥ በባንኮቹ መካከል ጤናማ የሆነ ውድድር በመፍጠር ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ ድርሻ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ጀርሚድስ እና ሚሽሌት የተባሉ የፋይናንስ ምሁራን “International Banks and Financial market in developing Countries” በተሰኘ ሥራቸው ያብራራሉ፡፡

ደቡብ ኮርያ ለተፋጠነ የዕድገት ጉዞዋ የባንኮቹ ሚና የራሱን ድርሻ ተወጥቷል፤ የውጭ ባንኮቹ ለዓለም ዐቀፍ የገንዘብ ግብይት፤ የተቀላጠፈ የአስተዳደር እና በዘርፉ የተሻለ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ አድርጓት እንደነበር እነዚሁ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡እነዚህ የውጭ ባንኮች አዲስ የአሰራር ሥርዓት የማስተዋወቅ ለምሳሌ ክሬዲት ካርድ፣ ስዋፕስ፣ ኦፍ ባላንስ ሽት አካውንቲንግ በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የውድድር አሰራር በመዘርጋት ዘርፉ የሚያድግበትን መንገድ ሊያመቻቹ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ ይህንን የውጭ ባንኮች ልምድ በመጠቀም የአገር ውስጥ ባንኮች የዕውቀት ሽግግር በማድረግ አቅማቸውን ለመገንባት እንደሚያስችላቸው ጆይዲፕ ባቻራይ የተባሉ የምጣኔ ሀብት ምሁር “The Role Of Foreign Bank In Developing Countries: Asurvey Of Evidence” በተሰኘ የምርምር ስራቸው ያትታሉ፡፡በተገቢው መንገድ የተደራጁ ታላላቅ የገንዘብ ተቋማት የዓለም የገበያ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ጠቃሚ መረጃዎችን በመስጠት ዓለም አቀፋዊ የሥራ ግንኙነቶችን በማመቻቸት ምክረ ሀሳቦችን በማቅረብ የንግድ ሥርዓቱ ላይ የበኩላቸውን ድጋፍ ለማድረግ እንደሚችሉ ምሁራኑ ከላይ በተጠቀሰው ሥራቸው ያስረዳሉ፡፡

ዓለም አቀፍ የሆኑት ባንኮች በብዙ አገራት ተጠቃሽ የሆኑ ለውጦች እንዳመጡም እነዚሁ ምሁራኑ ይጠቅሳሉ፡፡ ለምሳሌ በስፔን ባንኮቹ ወደ አገሪቱ መግባት ከጀመሩበት 1978 እ.ኤ.አ ጀምሮ በተለይ “ሚድ ላንድ” የተባለ ዓለም አቀፍ ባንክ በአገሪቱ ኮሜርሽያል ፔፐር ማርኬት እና የመጀመሪያውን የቺካጎ ስዋፕስ የባንኪንግ ሥርዓት በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል፡፡ በቱርክ ደግሞ ስዊፍት ኔትወርክ የተሰኘ

ቀሪውን በ ገጽ 26 ይመልከቱ

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!





+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.faceboook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu

ኢ-ሜይል፡
enqu2013@gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com